በጌቱ ሴማኔ 1
በመስቀል ተሰቅሎ (ሶስና በገና) 1
በጌቱ ሴማኔ (ዘርፉ ደምሴ በገና) 1
ኧረ ስማኝ ሀገሬ (ዘርፉ ደምሴ በገና) 1
ፍቅርና ሰላምን 2
ከደጇ ይፈልቃል (አቶ ታፈሰ በገና) 2
ኧረ ስማኝ ፈጣሪ (ዲ.ታደለ በገና) 2
አባታችን (አቶ አለሙ ኢጋ በገና) 3
እግዚአብሔርም (ዲ.ታደለ በገና) 3
ስለ ሥነ ፍጥረት (አቶ አለሙ ኢጋ በገና) 3
ሰላም ለኪ (አቶ አለሙ ኢጋ በገና) 4
ስለ ልደት (አቶ አለሙ ኢጋ በገና) 4
እመቤቴ (አቶ አለሙ ኢጋ በገና) 5
ስለ ምሥጢረ ሆሣዕና (አቶ አለሙ ኢጋ በገና) 5
አስቀድሞ (አቶ አለሙ ኢጋ በገና) 5
ጲላጦስም (ዘርፉ ደምሴ በገና) 6
የልዳው ኮከብ ደፋር 6
ስለ ዳግም ምፅዓት (አቶ አለሙ ኢጋ በገና) 6
የእመቤታችን ምሥጋና (ዘርፉ ደምሴ በገና) 7
ስለ አዳም መፈጠር (ዘርፉ ደምሴ በገና) 7
ድንግልም (ዘርፉ ደምሴ በገና) 8
እስመ አንተ (ዘርፉ ደምሴ በገና) 8
ስለ ሥነ-ስቅለት (አቶ አለሙ ኢጋ በገና) 8
ማን ይመሥመር (አቶ አለሙ ኢጋ በገና) 8
ማን ይመሥመር (አቶ ታፈሰ በገና) 9
ከቶ አይቀርም ሞቱ (አቶ አለሙ ኢጋ በገና) 9
በስመ ልዑል (ሶስና በገና) 10
ሰላም ለማርያም (ሶስና በገና) 10
አባ ግራኝ ሞተ (አቶ አለሙ ኢጋ በገና) 11
ድንግል ስልሽ (ሶስና በገና) 11
ርግብና ዋኔን (አቶ ታፈሰ በገና) 11
ዋኔን (ሶስና በገና) 12
ስቀለው ስቀለው (ሶስና በገና) 12
ኢትዮጵያ ሆይ ተነሽ (ይልማ ኃይሉ በገና) 13
የብርሃን እናት ነሽና (ይልማ ኃይሉ በገና) 13
አቤቱ ደግ ሰው አልቋልና (ይልማ ኃይሉ በገና) 13
አልፈርድም እኔ (ይልማ ኃይሉ በገና) 13
ኑ እንቅረብ (ሊቀ መዘምራን ኪነጥበብ) 14
ማኔቴቄልፋሬስ (ይልማ ኃይሉ በገና) 14
ድንግል ወላዲተ ቃል (ሊቀ መዘምራን ኪነጥበብ) 14
ሞቼ ስለማልቀር 14
ምድረ ቀራንዮ 15
የአብርሃም አምላክ 15
እንደቸርነትህ 15
በደምህ ተገዛ 15
ስለ ቸርነትህ (ይልማ ኃይሉ በገና) 15
መጸሙን ይጾማል 15
አምላኬ አምላኬ (ይልማ ኃይሉ በገና) 16
በህይወቴ (ይልማ ኃይሉ በገና) 16
ለእኔስ ልዩ ነች (ይልማ ኃይሉ በገና) 16
የእኛ ጌታ (ይልማ ኃይሉ በገና) 17
ኑ ተመልከቱልኝ (ይልማ ኃይሉ በገና) 17
ዳግም ስትመጣ (ዘርፉ ደምሴ በገና) 17
ሙሽራው ሙሽራ (የሠርግ) 17
የሀብ ከዮመ (የሠርግ) (ይልማ ኃይሉ በገና) 17
አሥር አውታር ባለው በበገና (ሶስና በገና) 18
አድነኝ ከሞት (ሶስና በገና) 18
ቸሩ መድኃኔዓለም (ሶስና በገና) 18
ሰማይና ምድርን (የትምወርቅ በገና) 19
በገናዬን ላንሳ (የትምወርቅ በገና) 19
ዐርብ የታረደውን (ዘርፉ ደምሴ በገና) 19
ድጓውን ከተቱት (ዘርፉ ደምሴ በገና) 20
እንመን በስሙ (ዘርፉ ደምሴ በገና) 20
ተወለደልን (ዘርፉ ደምሴ በገና) 20
ማዘን ጨምሩበት (ዘርፉ ደምሴ በገና) 21
የኢየሩሳሌም ቆነጃጅት (ዘርፉ ደምሴ በገና) 21
ኣሓዱ ብሎ ቅዱስ (ዘርፉ ደምሴ በገና) 21
በአዳም በደል (ዘርፉ ደምሴ በገና) 22
አየሁኝ በህልሜ (አቶ ታፈሰ በገና) 22
አቦዬ ጻድቁ (አቶ ታፈሰ በገና) 23
እፎይ ታገስከኝ (ዘርፉ ደምሴ በገና) 23
ሞት እንዴት ሰነበትክ (ዘርፉ ደምሴ በገና) 23
ኪዳነ ምህረት (ዘርፉ ደምሴ በገና) 23
የአዋጅ ነጋሪ ቃል 24
የዓለም መድኃኒት (ሊቀ መዘምራን ኪነጥበብ) 24
እወርዳለሁ ቆላ (ሊቀ መዘምራን ኪነጥበብ) 24
ይህ ቁርባን ከቡር ነው (ሊቀ መዘምራን ኪነጥበብ) 24
ወላዲተ አምላክ (ማኅበረ ቅዱሳን) 24
የመስቀሉ ፍቅር (ይልማ ኃይሉ በገና) 25
ተዋህዶ (ይልማ ኃይሉ በገና) 25
በይስሀቅ ፈንታ (ይልማ ኃይሉ በገና) 25
ውሃ አጠጪኝ አላት (ይልማ ኃይሉ በገና) 25
ኃይልህ ሲገለጥ (ይልማ ኃይሉ በገና) 26
ሥላሴን ከሰማይ (ይልማ ኃይሉ በገና) 26
የጴጥሮስን እንባ (ይልማ ኃይሉ በገና) 26
ያ ድህ ተጣራ (ይልማ ኃይሉ በገና) 26
እውነት ስለሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ (ይልማ በገና) 27
በማዳኔ ቀን ጠራሁህ (ይልማ ኃይሉ በገና) 27
በኃይልና ጥበብ (ይልማ ኃይሉ በገና) 27
ሰዓሊለነ ማርያም (ሲሳይ ደምሴ በገና) 27
ሰላም ተዋህዶ (ሲሳይ ደምሴ በገና) 28
ጽኑ ክርስቲያኖች (ሲሳይ ደምሴ በገና) 28
ክበር ተመስገን (ሲሳይ ደምሴ በገና) 28
በኪሩቤል ላይ ተቀመጠ (አቤል ተስፋዬ በገና) 29
ስምሽ ጉልበት ሆኖኝ (አቤል ተስፋዬ በገና) 29
ስሜ ዳዊት (አቤል ተስፋዬ በገና) 29
ሞትን በሞት ሽረህ (አቤል ተስፋዬ በገና) 29
መች ይረሳል (አቤል ተስፋዬ በገና) 30
የዛሬ ዘመን መኮንን (አቤል ተስፋዬ በገና) 30
በደም ሊታጠብ ኃጢአቴ (አቤል ተስፋዬ በገና) 30
ሠላምህ ይብዛላት (አቤል ተስፋዬ በገና) 30
በደላችንን የተውከልን (አቤል ተስፋዬ በገና) 31
ኧረ አንቺ አለም (ዲ.ታደለ በገና) 31
እማዬን አባዬን (ዲ.ታደለ በገና) 31
ሰቀሉህ (ዲ.ታደለ በገና) 32
ገዳመ ቆሮንቶስ (ዲ.ታደለ በገና) 32
ድንግል (ዲ.ታደለ በገና) 32
እንደ ክቡር ዳዊት (ዲ.ታደለ በገና) 32
ኖኅተ አንቲ (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ) 33
በባዕድ ሀገር (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ) 33
ከበለሷ ፍሬ (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ) 33
ታምኜህ ወጣሁኝ (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ) 34
ሕሙም ስለአዳነ (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ) 34
የአንተ ዜማ (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ) 34
ያቺን የተሰፋ ምድር (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ) 34
ወንጌሉን ያመኑ (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ) 34
የመድኃኒት እናት (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ) 35
ናቄርብ ለከ (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ) 35
የተወደደ ስምሽ ማርያም (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ) 35
ወንበዴ የነበርኩኝ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ) 35
አ ጌታ ሆይ ተሰቀልክ ሆይ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ) 36
ዋኔን (አለሙ በገና) 36
ይበላሃላ /አለሙ በገና/ 36
ወንድሜ ጠፍቶ 36
አዝላው ወረደች(ይልማ በገና) 37
አልዓዛር ይነሳ(ይልማ በገና) 37

በጌቴ ሴማኔ

ቅኝት - ሠላምታ

423 224 542 222

423 115 113 224 542 222

በጌቴ ሴማኔ በአትክልቱ ቦታ /2/
ለእኛ ሲል ጌታችን በዓለም ተንገላታ/2/
አዳምና ሄዋን ባጠፉት ጥፋት /2/
በእኛም ነበረብን የዘላለም ሞት/2/
መስቀል ተሸክሞ ሲወጣ ተራራ /2/
ይገርፉት ነበረ ሁሉም በየተራ/2/
ድንግል አልቻለችም እንባዋን ልትገታ /2/
እያየች በመስቀል ልጇ ሲንገላታ/2/
በአምላክነቱ ሳይፈርድባቸው /2/
እንዲህ ሲል ጸለየ አባት ሆይ ማራቸው/2/
በረቂቅ ስልጣኑ ሁሉን የፈጠረ /2/
በሰዎች ተገርፎ ሞተ ተቀበረ/2/
ፍቅሩን የገለፀው ተወልዶ በሥጋ /2/
ኢየሱስ ጌታ ነው አልፋና አሜጋ/2/

- - - - - - - - - - - - - - - - - - - -

በመስቀል ተሰቅሎ (ሶስና በገና)

ቅኝት - ሠላምታ

423 224 542 222

423 115 113 224 542 222

በመስቀል ተሰቅሎ እንዲያ እየቃተተ
ዓለምን ለማዳን የሚይሞተው ሞተ /2/
ከሞት ሊታደገን በመጣልን ፈጥኖ /2/
መስቀል አሸከሙት ውሊታው ይህ ሁኖ/2/
መከራውን ሳስብ ሳስታውስ ቀኑን /2/
ይቆስላል ይደማል ልቤ በሀዘን /2/
መች ለራሱ ነበር ይህ ሁሉ መከራ/2/
መስቀል ተሸከሞ የወጣው ተራራ /2/
ሲያጎርሱት የሚነክስ ሰው ክፉ ነውና
እውሩን ቢያበራ ጎባጣን ቢያቀና
ጌታዬን ሰቀሉት አይሁድ ጨከኑና /2/
ምነዋ አያሳዝን የአይሁድ ክፋት /2/
የዝናቡን ጌታ ውሃ ሲነፍጉት /2/
በተንኮል በኃጢአት ቀሩ እንደሰከሩ /2/
ሙታን ከመቃብር ተነስተው ሲያስተምሩ /2/
እናታችን ሄዋን ወዮ በይ አልቅሺ
ያንቺን ህመም ታሞ ከሞት ሊያድንሽ
የህያዋን ጌታ ተሰቀለልሽ /2/
አየጉድ አየጉድ ዓለም የኋላሽ /2/
መድኃኒት ክርስቶስ በግፍ ሞተብሽ /2/
በመስቀል ተሰቅሎ ሥጋውን ሲቆርስ /2/
በችንካር ተወግቶ ደሙንም ሲያፈስ
ዋለች በመከራ ድንግል ስታለቅስ /2/
ሰውነትሽ ራደ ሀዘን ከበበሽ
ስቃይ መከራውም ዳግም ፀናብሽ
ተሰቅሎ ሥታይ አንድዬ ልጅሽ /2/
ቢፈስም እንባዬ ሆኖ መንታ መንታ
መች ዋጋ ይሆናል ለአንዲቱ ጠብታ
ላለቀሽው ለቅሶ ድንግል የዛን ለታ /2/
ባለቀሽው ለቅሶ በልጅሽ ህመም /2/
ከኃጢአት ነጻሁኝ ዳንኩኝ ከገሀነም /2/

በጌቴ ሴማኔ (ዘርፉ ደምሴ በገና)

ቅኝት - ሠላምታ

423 224 542 222

423 115 113 224 542 222

በጌቴ ሴማኒ ባታክልቱ ቦታ
ለእኛ ሲል ጌታችን በዓለም ተንገላታ/2/
አዳምና ሔዋን ባጠፉት ጥፋት
እኛም ነበረብን የዘለዓለም ሞት/2/
መስቀል ተሸከሞ ሲወጣ ተራራ
ይገርፉት ነበረ ሁሉም በየተራ /2/
ዓሣ አትብሉ ብሎ ቁሱ ሲራገም
ዓሣማ ይበላል በኩዳዴ ጾም /2/
የተጠበሰ ዓሣ ይሸታል እጃችሁ
ኧረ እናንተ ሰዎች ዓሣማ በላችሁ /2/
መለስ ቀለስ ብላ አየችሁ ቀሚሷን
እረሳችው እና ካፈር መለወሷን /2/
በስምንተኛው ሺ በተልከሰከሰው
በተስኪያን እየሳሙ አይጣሉም ከሰው /2/
ሠርቼ ሠርቼ አዳራሽ ከልፍኝ
በማለቂያው ጊዜ ላፈር ሰው ሆንኩኝ/2/
እስከዛው ድረስ ነው ሲሶ ማረሳችን
እንገባው የለም ወይ በየመሬታችን /2/
ጐድን ከዳዊት ተብትበህ ጥበሰው
እስኪበላ ሞቱን አይውቅምና ሰው /2/
ሰው ከሶኛል አሉ ቆሞ አደባባይ
እውነት ነውር ሆኖ ሊያስቀጣኝ ነው ወይ /2/
ሸንበቆ ግድግዳ ማገር ከመቁረጥ
ማዘን ቤት ይሠራል የማይናወጥ /2/
ሸማኔው ሰውዬ ችግር ሳይገባው
አንድ አርብ ቢኖረው ለሥጋ ሸጠው /2/

- - - - - - - - - - - - - - - - - - - -

ኧረ ስማኝ ሀገሬ (ዘርፉ ደምሴ በገና)

ቅኝት - ሰላምታ

423 224 542 222

423 115 113 224 542 222

ኧረ ስማኝ አገሬ ተው ስማኝ አገሬ ኧረ ስማኝ ሀገሬ /2/
በጌቴ ሴማኔ ባታክልቱ ቦታ
ለኛ ሲል ጌታችን በዓለም ተንገላታ /2/
አዳምና ሔዋን ባጠፉት ጥፋት
እኛም ነበረብን የዘላለም ሞት/2/
መስቀል ተሸከሞ ሲወጣ ተራራ
ይገርፉት ነበረ ሁሉም በየተራ2/
አሳ አትብሉ ብሎ ቁሱ ሲራገም
አሳማ ይበላል በሁዳዴ ጾም /2/
የተጠበሰ አሳ ይሸታል እጃችሁ
ኧረ እናንተ ሰዎች አሳማ በላችሁ/2/
መለስ ቀለስ ብላ አየችው ቀሚሷን
እረሳችው እና ካፈር መለወሷን/2/
በስምንተኛው ሺ በተልከሰከሰው
ቤተክርስቲያን ይስሟል አይጣሉም ከሰው/2/
ሰርቼ ሰርቼ አዳራሽ ከእልፍኜ
በማለቂያው ጊዜ ላፈር ሰው ሆንኩኝ/2/
እስከዚያው ድረስ ነው ሲሶ ማረሳችን
እንገባ የለም ወይ በየመሬታችን/2/

በበገና . . . . . .
ጐድን ከዳዊቱ ፈትፍተህ ጥበሰው
እስኪበላ ሞቱን አያውቅም እና ሰው/2/
ሰው ከሶኛል አሉ ቆሞ አደባባይ
እውነት ነውር ሆኖ ሊያስቀጣኝ ነው ወይ /2/
ሸምበቆ ግድግዳ ማገር ከመቁረጥ
ማዘን ቤት ይሠራል የማይናወጥ/2/
ሸማኔው ሰውዬ ችግር ሳይገባው
አንድ አርብ ቢኖረው ለሥጋ ሸጠው/2/
ኧረ ስማኝ . . . . . .
ጣናን በታንኳ ላይ ሲጓዙ ብታይ
ኧረ አባይን በግር ትጓዛለህ ወይ /2/

- -

ፍቅርና ሰላምን

ቅኝት- ሥላምታ
423 224 542 222
423 115 113 224 542 222

ፍቅርና ሰላምን ታፈራለች ጾም /2/
ፍፃሜ የሌለው እስከ ዘላለም /2/
አዝ.....
የጾምንም ፍሬ ሁላችን አውቀን /2/
ለጸሎት እንትጋ ፍሬው አይለፈን /2/
አዝ.....
አምላክ ተፈተነ በክፉ ጠላት /2/
ጾምን ሊመሰርት ስለኛ ህይወት /2/
አዝ.....
አምላክ ተሸከመ ህማማችንን /2/
የህይወትን ውሃ ከጐኑ ሰጠን /2/
አዝ.....
ህዝቦችህን ጠብቅ ከክፉ ፈተና /2/
ቅዱስ አምላካችን ኃይላችን ነህና /2/

- -

ከደጇ ይፈልቃል (አቶ ታፈሰ በገና)

ቅኝት- ሥላምታ
423 224 542 222
423 115 113 224 542 222

ከደጇ ይፈልቃል ማርና ወተት
አዛኝቷ ድንግል ኪዳነ ምህረት /2/
እስቲ ልናገረው የእመአምላክን ዝና
የኪሩቤል መቅደስ የሱራፌል ጽና /2/
ኤልያስ የጠራት የበራች ደመና
የኢሳይያስ ትንቢት የገብርኤል ዜና /2/
የቅዱሳን ምግብ የእስራኤል ደመና
ለፍጥረቱ አዛኝ ርህሩህ ነችና /ናትና/ /2/
ዘካርያስ ያያት የተቋም ላይ ፋና
መድኃኒት ላለሙ የጽድቅ ጐዳና
የረሃብ መድኃኒት የድውያን ጤና/2/
ስሟ እንቅ እኮ ነው ለሚኼድ ተከፍቶ
ጠግቦ ያድራልና የእርሷኑ ስም ጠርቶ /2/
የረሃብተኞች ምግብ የድኩማን ጽናት
የርህራሄ ምንጭ ነይ ኪዳነ ምህረት /2/
ከደጇ ይፈልቃል ማርና ወተት
አዛኝቷ ድንግል ኪዳነ ምህረት/2/
ስለ ማርያም ብሎ ስሟን ለሚጠራ
የትም ቦታ ኼዶ ይጠግባል እንጀራ/2/
የቅዱሳን ምስጢር ጽላተ ጽዮን
ምስጋና ይድረስን ለሰጠን አንቺን /2/
ስለ ክብሯ ላቅርብ ምስጋና ውዳሴ
በጸሎት በስግደት በመጨነቅ ነፍሴ /2/
የማማለድ ሥልጣን አላት ኪዳነ ምህረት
እራሱን ዝቅ አድርጐ አዝኖ ለለመናት /2/
እሳት ተዋህዷት ሳትቃጠል ደህና
የእግዚአብሔር አብ ቃሉን ወልዳዋለችና/2/
ስሟ ስንቅ እኮ ነው ለሚኼድ ተከፍቶ
ጠግቦ ያድራል እና የእርሷኑ ስም ጠርቶ /2/

- -

ኧረ ስማኝ ፈጣሪ (ዲ.ታደለ በገና)

ቅኝት - ሰላምታ
423 224 1542 222
423 115 113 224 542 222

ኧረ ስማኝ አምላኬ ኧረ ስማኝ ፈጣሪ /2/
አላገኝምና ያለአንተ መሀሪ ኧረ ስማኝ ፈጣሪ /2/

አድነኝ ጌታዬ ኧረ ስማኝ ፈጣሪ
ሁሉንም ትተህ " "
ይቅር በለኝ አምላክ " "
በደሌን ንቀህ " "
ዘወትር ነውና የማስቀይምህ ኧረ ስማኝ ፈጣሪ
በደሌን አውቄ ኧረ ስማኝ ፈጣሪ
ወዳንተ ስጠይቅ " "
በሰራሁት ኃጢአት " "
መንፈሴ ሲጨነቅ " "
ይቅር በለኝ እንጂ ምህረትን አታርቅ ኧረ...
እያወቅሁ አጥፍቼ ኧረ ስማኝ ፈጣሪ
እኔም ብበድልህ " "
ከሥጋ ገበያ " "
ውዴ ባስቸግርህ " "
እስኪ አድነኝ አንተ የምህረት አምላክ ነህ ኧረ...
እስኪ ዛሬስ ይብቃኝ ኧረ ስማኝ ፈጣሪ
ልዙር ወደ ነፍሴ " "
መፈጠሬ የግባኝ " "
በአርአያ ሥላሴ " "
ተቀበለኝ አምላክ ልጅምር ውዳሴ ኧረ....
ለሥጋ እያደላሁ ኧረ ስማኝ ፈጣሪ
ብዙ አጠፋሁኝ " "
አውቄ እንዳላወቅሁ " "
ቃልህም ሻርኩኝ " "
አምላክ ይቅር በለኝ አሁን ፀፀተኝ ኧረ .....
እንድታማልደኝ ኧረ ስማኝ ፈጣሪ
ድንግልን ጠይቄ " "
አለቅሣለሁ እንጂ " "
ከፊትህ ወድቄ " "
የትስ እደርሳለሁ ከመንፈስህ ርቄ ኧረ .....

ይቅር በለኝ ብዬ ኧረ ስማኝ ፈጣሪ
ወዳንተ ሣለቅስ " "
የእባ ዘለላ " "
በጐንጮቼ ሲፈስ " "
ምህረትን ነው እንጂ " "
በደሌን አታስታውስ " "
ፊትህን ወደእኔ እባክህን መልስ ኧረ ስማኝ...

- -

አባታችን (አቶ አለሙ ኢጋ በገና)

ቅኝት - ሰላምታ
4245 313 15423 312 45
4245 313 15442 222

አባታችን በሰማያት ላይ ያለህ
ተለይቶ ይመስገን ክቡር ስምህ
መንግሥትህን የምንፈልጋት ከጥንቱ
በልጅነት ትምጣ ትሰጠን አቤቱ
ፈቃድህም ይህ እንዲደረግ ይሁን
በሰማይ ሞተን ተነስተን ከደይን
እንድንኖር ምስጋናህ ምግብ ሆኖን
ዛሬም በምድር በሥጋ ሕይወት ሳለን
ምግባችንን በየዕለቱ አውቀህ ስጠን
ይቅር በለን የበደልንህን ነገር
ወንድማችን የበደለንም ቢኖር
እንደአቅማችን እኛም እንድንል ይቅር
ከገሃነም ከክፉ ሁሉ መአት
አትጣለን አድነን እንጂ ከሞት
ይህቺን መንግስት የማያገኛት ህልፈት
ጌትነትም ከሀሊነትም ክብርም
ናቸውና የአንተ ገንዘቦች ሁሉም
ለዓለም ወለዓለም ዓለም አሜን፡፡
የተላከው ቅዱስ ገብርኤል ከጌታ
ሰላም ለኪ ብሎ በሰጠሽ ሰላምታ
እኔ ባሪያሽ ልብሴን ስታጠቅ ስፈታ
ሰላም ልልሽ ይገባኛል ጠዋት ማታ
ማርያም ሆይ እመቤቴ ሆይ ድንግል
በሥጋሽም በህሊናሽም ድንግል
የአሸናፊ የእግዚአብሔር እናት ድንግል
እንዳለሽ ቅዱስ ገብርኤል ሰላም
ሰላም ለኪ እንደርሱ ሁሉ እኔም
የሌለብሽ የነፍስ የሥጋ መርገም
ብሩክ ነው የማሕፀንሽ ፍሬም
እንደቀድሞው ብሩክ አምላክ ነው ዛሬም
እግዚአብሔር ወልድ በመጣ ጊዜ ለካሳ
እንበለ ዘር እንደ ንብና እንደ ዓሣ
ከነፍስሽ ነፍስ ከስጋፍ ሥጋ ቢነሳ
ደስ አለሽ ወይ ጸጋን አግኝተሽ ከጌታ
ደስ ይበልሽ በማቀርብልሽ ሰላምታ
ለምኚልን ሳትሰለቺ ጠዋት ማታ
ውድ ልጅሽ እንዲያደርግልን ይቅርታ
ይቅር ብሎ ኃጢአታችንን ሁሉን
እንዲያድነን በአንቺ ተማፅነን አለን
ለዓለም ወለዓለም ዓለም አሜን፡፡

- -

እግዚአብሔርም (ዲ.ታደለ በገና)

ቅኝት - ሰላምታ
4245 313 15423 312 45
4245 313 15442 222

እግዚአብሔርም አዳም ባጠፋው ጥፋት
በተስፋ ቃል አሠናበተው ያን ለት
ለአዳም በገባለት ቃል ኪዳን
አምስት ሺ ከአምስት መቶ ዘመን
ሲፈፀም ያ የተስፋ ቃል ደረሰ
የአዳም የስቃይ ዘመን ፈረሰ
አዳምም በሲኦል ሲኖር ተቀብሮ
አዳነው ሞቱን በሞቱ ቀይሮ
አምላክም ወደዚህ ዓለም ሲመጣ
ቆየችው እመቢታችን ተመርጣ
የሌለባት መርገመ ፍዳ ከጥንት
ጸነሰችው በመልአኩ ቃል ብስራት
ፍቅር ስቦት ወደዚህ ዓለም መጣና
ለአዳም ምን ያልሆነለት አለና
ተወለደና ድንግልናዋን ሳይሸር
ለሰው ልጅ ሲል ተመላለሰ በምድር
በዮርዳኖስ በዮሐንስ እጅ ተጠምቆ
በዲያብሎስ የተጻፈውን ተራምዶ
አጠፋለት ያንን ደብዳቤ ደምስሶ
ከባርነት የሚያላቅቀው ጨርሶ
በመስቀል ላይ በዕለተ ዓርብ ተወግቶ
ከሲኦል በደሙ አነፃው አውጥቶ
እንዲህ አድርጎ ወደ ጥንት ቦታው መለሰው
በምህረቱ ዳግም ገነትን አሣየው
በአባታችን በአዳም ጥፋት በደል
ገብተን ነበር እኛ ሁላችን ሲኦል
በስራችን በኃጢአታችን እኛማ
ሆነን ነበር ከመርገም ግዞት ጨለማ
ግን አዳነን የፍቅር አምላክ ነውና
በትህትና እናቅርብለት ምስጋና
ስብሀት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
ለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ፡፡

- -

ስለ ሥነ ፍጥረት (አቶ አለሙ ኢጋ በገና)

ቅኝት - ሰላምታ
4245 313 15423 312 45
4245 313 15442 222

በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
አሐዱ እምላክ ብዬ ሰላምታ ላድርስ
ለፈጠርከኝ ለሰማዩ ንጉሥ
እንዴት አለህ መጥቼ እስካይህ ድረስ
ያስደንቃል ያኗኗራቸው የጥንቱ
የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ የሦስቱ
ሦስት ናቸው በአካል በገጽ በስም
አንድ ናቸው በትእዛዝ በክብር ፍፁም
ስላሤም እም ቅድመ ዓለም ሲኖሩ
ዓለም መፍጠር አሁድ በሠርክ ጀመሩ
ያን ጊዜውን ሰባት ፈጠሩ በቅጽበት
አስቀድመው ሰማይና ምድር በፊት
አራተኛ መላዕክትና ጽልመት
ሰባተኛ ማይና ነፋስ እሳት
በአርምሞ ይህን ሁሉ ፈጥረው
ተናገሩ ለይኩን ብርሃን ብለው

ሰኞ ጠዋት ውኃን ከፈሉት ከሦስት
አንደኛውን አዘቅት አረጉት ከምድር
ሁለቱን ሰማይ አረጉት ጠፈር
ማክሰኞም አብቅይ አሏት ምድርን
አበቀለች ሳር ቅጠሉን እህሉን
ረቡዕም ረቂቅ ሥራን ሲሰሩ
ከዋክብትን ፀሐይ ጨረቃን ፈጠሩ
ሐሙስም አልተውምና መፍጠር
የሚበሩ ከንፍ ያላቸውን ነገር
የማይበሩ የሚሄዱትን በእግር
በባህርም ዓሣ ጉማሬ ሳይቀር
ዓርብ ጠዋት አዳምን የኛን አባት
ንግበር ብለው በነሱ አምሳል ሠሩት
በሠልስት ሐዋንን ፈጥረው ሰጡት
ትርዳህ ብለው ብቻውን ሆኖ ቢያዩት
የሥላሴ የፍጥረታቸው ፍፃሜ
በሰባት ቀን ዳርቻ ሆነ ቅዳሜ
ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
ለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ፡፡

- -

ሰላም ለኪ (አቶ አለሙ ኢጋ በገና)

ቅኝት - ሠላምታ

4245 313 15423 312 45

4245 313 15442 222

ሰላም ለኪ ማርያም ድንግል ንጽሕት /3/
ያቺን ርግብ ያቺን ወለላ ፍጥረት
በበገና እስኪ ላመስግናት ጥቂት
የአምላክ እናት የሰማይ የምድር ፈጣሪ
የእርሷ አዝማሪ ዕዝራና ዳዊት በባህሪ
ቃል ኪዳኗ የማይፈርስባት ነዋሪ
እልፍ አዕላፍ መላእክት አሉዋት ነባሪ
ያገልግሉሽ ብሎ የሰጣት ፈጣሪ
እኒያን ይዛ ፍጥረት ዓለሙን መካሪ
ወለላዊት ቤዛዊት ዓለም ብፅዕት
ከወተት ውዳሴሽ ጥዑም በእውነት
ከወለላ ተአምርሽ ጥኡም ሲበላ
የብርሃን ዘውድ የብርሃን አክሊል ደፍተሽ
ድረሺልን በሠረገላ ሆነሽ
ይሸሻሉ ኢጋንንት አንቺን ሲያዩሽ
በቤተ መቅደስ ስታገለግል ስትሠራ
ነይ ውጭ አሏት ሊቃውንት መከረው በሴራ
ተመቅኝተው ምናምን ኃጢአት ሳትሰራ
እንደ ፀሐይ ገላዋ እንደ እሳት ሲያበራ
ትሙት ብለው ማየ ዘለፋን ቢያጠጧት
እንደገና ብርሃን መሆኑ ባሰባት
ያንን ግሩም ያንን ደስ የሚል መዐዛ
በንጽሕና ያለ ሩካቤ /ፀንሳ/ አርግዛ
ወለደቸው በቤተልሔም ተጉዛ
ምጥ የለባት በመልአክ እጅ ተይዛ
የታደለች የተባረከች ፍጥረት
የበላውን ሰባ ስምንቱን ነፍሳት
አስገባችው በጥርኝ ውሃ ገነት
ከአድማስ አድማስ ወረቀት ቢሆን መሬት
ቀለም ቢሆን የሦስት ወር ውሃ ከረምት
ብዕር ቢሆን የዚህ ዓለም ሁሉ ዕፅዋት
ቢጻፍ አያልቅም የተአምርሽ ብዛት
ንግበር ብሎ ገና ሲፈጥረን ከጥንት
ፈጥሮ ሰጠን ድንግል ሕሊና ትሁት
በእርስዋ ሰበብ እንገባለን ገነት
ተመልከቱ የእግዚአብሔርን ምህረት
ብንወርድበት መቼ ይወዳል ከእሳት
እኛ ግና በኃጢአታችን ብዛት
እንወድቃለን ከዚያ ጨለማ ክርፋት
አደራሽን ቤዛዊት ዓለም ብፅዕት
በማልቀስሽ በመጨነቅሽ ብዛት
ሑሩ ሲለን እንድታወጪን ከእሳት
ቃል ኪዳንሽ እጅግ ታላቅ ነው ከጥንት
አንቺን አምኖ እንዴት ይጎዳል ፍጥረት
ማጎደሩ የአምላክ ሰማይ እናት
ታይቶ አይጠገብ ሁልጊዜ የልጅሽ ምሕረት
እኛን በቀኝ እንድታቆሚን ያን ዕለት
ለዓለም እስከ ዘለአለም ድረስ፡፡

- -

ስለ ልደት (አቶ አለሙ ኢጋ በገና)

ቅኝት - ሠላምታ

4245 313 15423 312 45

4245 313 15442 222

ድንግልም በምትወልድበት ወራት
በሮም ንጉሥ በአውግስጦስ ቄሳር መንግስት
ሰው ሁሉ ግብር ሊቆጠር ታዘዘ
ዮሴፍም ድንግልን ይዞ ተጓዘ
ከገሊላ ከነበረበት መንደር
ቤተልሔም ወደምትባል ሀገር
ከኤፍራታ ይወጣል ብሎ ንጉሥ
ሚክያስ የተናገረው ሊደርስ
ሳታፋልስ የወላዶችን ሥርዓት
በታኅሣሥ በሃያ ዘጠኝ ዕለት
ከዚያው ሳሉ የምትወልድበት ቢደርስ
ተወለደ ድንግልናዋን ሳይጥስ
ቤት ባይኖራት መጥታለችና ከሩቅ
ከበረት ጠቀለለችው በጨርቅ
ሊፈጸም የኢሳይያስ ነገሩ
እንስሳትም ትንፋሻቸውን ገበሩ
ከዚያ ቦታ ከብት ጠባቂዎች ነበሩ
ያዩ ነበር ካሉበት ቦታ ድረስ
የብርሃን ጎርፍ ከቤተልሔም ሲፈስ
እረኞቹም የብርሃኑን ጎርፍ አይተው
እጅግ ፈሩ ምን ነገር ነው ብለው
መልአኩም ፍርሐታቸውን አርቆ
ነገራቸው ተድላ ደስታሉን አድንቆ
ልዑል አምላክ ለአዳም ብሎ ተዋርዶ
ከድንግል በዳዊት ባሕርይ ተወልዶ
ጨርቅ ለብሶ ከበረት መሐል ተጥሎ
አለላችሁ ሄዳችሁ እዩት በቶሎ
እንዲህ ብሎ ሲናገራቸው በዜና
ከእርሱ ጋራ ብዙ መላእክት መጡና
አቀረቡ ከእረኞች ጋር ምስጋና
ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
ለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ

- -

እመቤቴ (አቶ አለሙ ኢጋ በገና)

ቅኝት - ሠላምታ

4245 313 15423 312 45

4245 313 15442 222

እመቤቴ የፍጥረት ሁሉ አለኝታ
ከብር ለስምሽ ይገባል ላንቺ ሰላምታ
እናታችን አማላጃችን ድንግል
ተስፋችን ነሽ የጽድቅ የብርሃን አክሊል
ማርያም ሆይ አንቺ የገነት መውረሻ
እንኳን ለሰው የምትራሪ ነሽ ለውሻ
ባንቺ አምነው በቃል ኪዳንሽ ተማፅነው
ገነት ገቡ ኃጥአን ስርየት አግኝተው
ባንቺ ምልጃ ባንቺ ልመና ያመኑ
በኪዳንሽ በልጅሽ አምነው የጸኑ
ለክብር በቁ ከዳግመኛ ሞትም ዳኑ
ኑሮው ከፍቶት ደሃ ሲጨነቅ በቤቱ
አይዞህ ብለሽ የምታጽናኚው እናቱ
ሲራብ ጉርሱ ሲዝል ሲደክም ብርታቱ
አንቺ እኮ ነሽ ለችግረኛ ሕይወቱ
ምጽዋት ሰጥተው ስለ ቅዱሱ ስምሽ
ሲደሰቱ ምዕመናን በውል ምልጃሽ
ተለይቼ እንዳልቀር ምስኪን ልጅሽ
ከጌታዬ አማልጂኝ ድንግል እባክሽ
ታውኮብኝ በዓለም ጣጣ ሕይወቴ
ስፍገመገም እጅግ ጠንቶብኝ ጉዳቴ
ታድኚኝ ዘንድ ከሥጋ ወጥመድ ጭንቀቴ
ድርሺልኝ ድንግል ማርያም እናቴ
ሃይማኖቴ ቢታይ ቢመዘን ምግባሬ
ስለሚበልጥ ከክብሬ ይልቅ ነውሬ
በሰንሰለት እጅና እግሬን ታስሬ
በገሃነም ይበዛልና አሣሬ
በምልጃሽ አሁን አድኚኝ ዛሬ፡፡

- -

ስለ ምሥጢረ ሥጋዕና (አቶ አለሙ ኢጋ በገና)

ቅኝት - ሰላምታ

4245 313 15423 312 45

4245 313 15442 222

በስመ አብ ብለን እስኪ ሠላምታ እናድርስ
ለአብና ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ
እስኪ እናስታውስ የሥጋዕናን ትዕይንት
የሆነውን የነበረውን ያን ዕለት
ፋሲካቸው በስምንት ቀን ሲሆን
ከፋሲካ በሚቀድመው ሰሞን
ዘካርያስ የሚባል ነቢይ ካህን
ደስ ይበልሽ ኢየሩሣሌም ጽዮን
ንጉሥሽ ይመጣልና አሁን
በአህያ ላይ እንደ አንድ ደሃ ምስኪን
እንዲህ ብሎ የተናገረው ቃሉን
ለመፈፀም በአህያ ሆኖ መድኅን
ሲመጣ አይታ እርሱ መሆኑን ለይታ
ሀገሪቱ ተቀበለችው በእልልታ
በመንገዱም ቅጠሉን ቆርጠው በእርጥቡ
ልብሳቸውን ያነጠፉ አሉ ከሕዝቡ
ሁለተኛም ዳዊት ልበ አምላክ ነውና
ሲዘመር እያስማማ በበገና
አስቀድሞ ይህችን ዕለት አየና
ሲሰብክልን የዚህች ዕለትን ዜና
አዘጋጀህ ከህፃናት አፍ ምስጋና
ላለው ትንቢት መፈፀሚያ ቀን ናትና
እንዲህ ሆኖ ከቤተ መቅደስ ሲገባ
ሕፃናት እየወረዱ ከጀርባ
በጣታቸው እየጨበጡ ዘንባባ
በእግዚአብሔር ስም የምትመጣው አምላክ
ብሩክ ነህ ለዘለዓለም ብሩክ
የዳዊት ልጅ መድኃኒት የሆንክ ለሁሉ
ሆሣዕና መባል ተገባህ እያሉ
በደስታ በፊት በፊቱ ዘለሉ፡፡
ይህን ሰምተው ፈሪሣውያን ጸሐፍት
ቢናደዱ ቢመላባቸው ቅንዓት
ሕፃናቱን ተው በላቸው አሉት
እንዲህ አለ ሲመልስላቸው ጌታ
ከጠላችሁ የሕፃናቱን ዕልልታ
ድንጋዮቹ የሚገባቸው ዝምታ
ያመስግኑ በእናንተ በሰዎች ፈንታ
በዚህ ጊዜ አምላክነቱን ሊገልጡ
ድንጋዮቹ በፊት በፊቱ እየሮጡ
እንደ ሰዎች የምሥጋና ድምጽ ሰጡ
ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
ለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ

- -

አስቀድሞ (አቶ አለሙ ኢጋ በገና)

ቅኝት - ሠላምታ

4245 313 15423 312 45

4245 313 15442 222

አስቀድሞ ነፍሱ ሳትወጣ በፊት
እናቱን ቆማ ስታለቅስ ቢያያት
ለዮሐንስ አደራ ብሎ ሰጣት
ይርዳሽ ያፅናሽ ይህ ልጅሽ ነው አላት
እርሱንም ቆሞ ሲያለቅስ ቢያየው
ቢወደው ለእናቱ አደራ ሰጠው
ዮሐንስም እያለቀሰ በሞቱ
እናቱን አኖራት ወስዶ ከቤቱ
ሊፈፀም የተናገረው ዳዊት
አይሁድ ጌታን ውሃ ጠማኝ ሲል ሰሙት
መጣጣውን ውሃ ቀላቅለው ሰጡት
ቀመሰና ያን የሰጡትን ሐሞት
ተፈፀመ ትንቢቱ ሁሉ አሁን
ይህን ብሎ ዘለፍ አድርጎ ራሱን
በሥልጣኑ ከሥጋው ለያት ነፍሱን
በነፍስ ወርዶ ነፍሳት ካሉበት አዘቅት
ነፍሳትን የወረዱትን ከጥንት
ከዚያ አውጥቶ ወስዶ አገባቸው ገነት
ተጠራጥሮ አንዱ ሐራዊ ሞቱን
ሞተ ብሎ በጦር ቢወጋው ጎኑን
አፈሰሰ ከውሃ ጋራ ደሙን
አይሁድም እርግጥ መሞቱን አውቀው
ሳያዝኑለት ነገ ሰንበት ነው ብለው
አይደር አሉ ከመስቀል ይውረድ ሥጋው
ኒቆዲሞስ ቀድሞ በሌሊት ያየው
ዮሴፍም በአርማትያስ ያለው
ሞት ሳይፈሩ ከጲላጦስ ፊት ቆመው
ተካሰሱ በድኑን እናውርድ ብለው
ጲላጦስም ጠዋት ስላየው ታግሶ
ትዕግስቱን ጻድቅነቱን አስታውሶ
እንዴት ሞተ ብሎ ጠየቀ መላልሶ
ሞተ ቢሉት እጅግ አዘነ ተከዘ

በድኑን ስጡ ብሎ ጭፍሮቹን አዘዘ
ከመስቀሉ አወረዱና ሁለቱ
ገነዙና በድርብ በፍታ በሽቱ
ከተከል ውስጥ ከአዲስ መቃብር ቀብረውት
መቃብሩን በታላቅ ድንጋይ ገጠሙት
ወልድ ጌታ በተናገረው መሠረት
ተነሣና ህቱም መቃብር ሳይከፍት
ለማርያም ወዶ ተገልጦ ታያት
ረቢ ብትል አይዞሽ ጠንክሪ አላት
እንዲህ ሆኖ ሞቶ ተነስቶ በፍጥነት
አዳምን አገባው ከተድላ ገነት
የአዳም ልጆች አሁን ያላችሁ በመሬት
አመስግኑት ስላወጣችሁ ከእሳት
ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
ለዘላለም ምሥጋናህ ይብዛ ክርስቶስ
ለዓለም ወለዓለም ዓለም አሜን፡፡

- -

ጲላጦስም (ዘርፉ ደምሴ በገና)

ቅኝት - ሰላምታ

4245 313 15423 312 45

4245 313 15442 222

ጲላጦስም ባይቃወመው ቅናት
ጠይቆት ባያገኝበት ሐሰት
የለም ብሎ ከተገረፈ ስቅለት
ያዝኑለታል ይራሩለታል መስሎት
አስገረፈው እስኪታይ ድረስ አጥንቱ
ገርፎ መስቀል አይደለም እና ስርዓት
ከገረፍነው ልቀቁት ይኺድ አላቸው
ቢላቸው እነሱም እንዲኽ አሉት
ይህንን ሰው ካላራቅህልን በሞት
አይደለህም የቄሳር ወዳጅ ከጥንት
ካንተም በቀር የለንም ሌላ ጠላት
ጲላጦስም እኔ ንፁህ ነኝ ብሏቸው
እናንተ ግን ስቀሉት ብሎ ሰጣቸው
ተቀብለው ጭፍሮች ይዘውት ሲደርሱ
በአደባባይ ይዘብቱበት ተነሡ
የእሾህ አክሊል ደፉበት በራሱ
ልብሱን ገፈው ሃር አለበሱት እነርሱ
በቀኝ እጁ አስያዙትና አለት
እንዴት አለህ የአይኑድ ንጉሥ አሉት
በፊቱ ላይ እየሰገዱ ዘበቱ
ብድግ ብለው ምራቅ ተፉበት በፊቱ
የሰጡትን ያቀበሉትን አለት
ተቀብለው አራስ እራሱን መቱት
ገፈፉና ያለበሱትን ሜላት
አለበሱት ያለበሱትን ከጥንት
ርህራሄ ጥቂት የላቸው ለሁሉ
ከገረፍነው እነዴት ይሰቀል ሳይሉ
ሊሰቅሉት በሮማውያን ልማድ
ወሰዱት ግንድ አሸክመው አይኑድ
ለትዕግስቱ የለውምና አምሳል
በአንዲት ሰዓት እነርሱን ማጥፋት ሲችል
የምትሰቅሉኝ በምን ነገር ነው ሳይል
ኼደላቸው ተሸከመና መስቀል
ቀራንዮ እንዲህ አድርገው ወስደው
ሊፈጸም ዳዊት በመዝሙር ያለው
እጁን እግሩን ከመስቀሉ ጋር አብረው
ቸነከሩት እንደ ብራና ወጥረው
ስብሀት ለአብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ
ለዓለም እስከ ዘለዓለም

- -

የልዳው ኮከብ ደፋር

ቅኝት- ሠላምታ

4245 313 15423 312 45

4245 313 15442 222

ለኃያሉ ሊቀ ሰማዕታት ጊዮርጊስ
በተቻለኝ እስቲ ሠላምታ ላድርስ
ሰላም ለከ የልዳው ኮከብ ደፋር
የመስቀሉ የክርስቶስ ወንጌል መምህር
ሲታወስ የቅዱስ ጊዮርጊስ መከራ
ያስለቅሳል በየዘመኑ ሲወራ
ዱድያኖስ የሚባል ኃያል ንጉስ
ነግሶ ነበር በባቢሎን ላይ በፋርስ
የሚያመልከው ጣዖት አቁሞ ነውና
በሣጥናኤል በግብር አባቱ ..... ና
ከርሱ ጋራ ሳባ ነገስታት አብረው
ለጣኦታት ይሰግዱ ነበር አምነው
ይህን አይቶ ፈጣኑ ጊዮርጊስ ተነሣ
ተጋደለ ለሥጋ ህይወቱ ሣይሣሣ
ብዙ ህዝብም በሰማዕቱ ተጋድሎ
ተመለሰ ጠፍቶ የነበር ተቃሎ
የሞቱትም ከብዙ ዘመን በፊት
ተነስተዋል በቅዱስ ጊዮርጊስ ጸሎት
በጀግንነት የተቀበለው ስቃይ
ሣይበግረው ወርቅና ዕንቁ ንዋይ
በልጅነት በወጣትነት እድሜው
ተጋፈጠ ሣያሸንፈው ባህሪው
ሥጋውንም በመንኮራር ፈጭተው
በነበልባል በእሳት ኣቃጥለው ወቅጠው
ደብረ ይድራስ ለነፋስ ሰጡት ወስደው
እሱ ግን ወዲያው ተነሣ ከሞት
በፍጥነት ሕያው ሰው ሆኖ አዩት
ሰባት አመት ግፍ ተቀብሎ ስቃይ
ወረደለት ሰባት አክሊላት ከላይ
እሱን አምኖ ፍጡነ ረድኤት ሲሉት
ከመከራ ከጭንቅ ያወጣል ከእሳት
ስብሓት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
ለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ

- -

ስለ ዳግም ምፅዓት (አቶ አለሙ ኣጋ በገና)

ቅኝት - ሰላምታ

4245 313 15423 312 45

4245 313 15442 222

እንዲህ አርገን ሥራውን ሁሉ አምነን
እናምናለን ዳግም ይመጣል ብለን
ነገር ግን ዳግም ይመጣል ስላልን
ከፃድቃን ከመላእክትም ቢሆን
የሚያውቅ የለም የሚመጣበት ቀኑን
ባላወቅነው ባልመረመርነው ሰዓት
ግሩም ሆኖ ይመጣል እንጂ ድንገት
መጀመሪያ የአዋጅ ነጋሪት ሲመታ
ከያለበት ይሰበሰባል በአንድ አፍታ
አጥንታችን ትቢያ የሆነው አፈር
ጅብ የበላው የተበተነው ከዱር
የራስ ፀጉር የእግር ጥፍራችን ሳይቀር
ተሳስቶ የአንዱ ወደ አንዱ ሳይዞር
በየራሱ ይሰበሰባል ሁሉም

ይመታል የአዋጅ ነጋሪት ዳግም
ነፍስ የሌለው በድን ይሆናል ፍፁም
በሶስተኛው የአዋጅ ነጋሪት ሲመታ
ይነሳሉ መልካም የሠሩ በእልልታ
የብርሃን ልብስ የብርሃን ቀሚስ ለብሰው
እንደ ፀሐይ እንደ ጨረቃ ደምቀው
እግዚአብሔርን ፈጣሪያቸውን መስለው
ይሰሙና በቀኙ ቆመው ፍርዱን
ከማያልፈው ተድላ ደስታ በቀር
ጠግቦ ቁንጣን በተርቦ ስስት ሳይኖር
ጉብቶ መውጣት አግኝቶ ማጣት ችጋር
የሌለባት ደገኛይቱን ሀገር
ይወርሳሉ መልካም የሠሩ በምድር
ኃጥአንም እጅግ ከጭራ ቀጥነው
መልካቸውም እጅግ ከቁራ ጠቁረው
ከላይ ከታች የጨለማ ልብስ ለብሰው
ዲያብሎስን አለቃቸውን መስለው
ይሰሙና በግራ በኩል ቆመው
በመንቀጥቀጥ የሚፈርደውን ሰምተው
ከልቅሶና ጥርስ ማፋጨት በቀር
ተድላ ደስታ የሌለባትን ሀገር
ይወርሳሉ ክፉ የሠሩ በምድር
እንዲህ አርገው መጻሕፍት ሁሉ እንዳሉ
በየሥራው ይከፍለዋል ለሁሉ
ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
ለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ

- -

የእመቤታችን ምሥጋና (ዘርፉ ደምሴ በገና)

ቅኝት -
ሰላም ብዬ እስቲ ልጀምር ምሥጋና
በይባቤ ደስ በሚያሰኘው በገና
ለአምላክ እናት ለሰማይ ለምድር ፈጣሪ
ለእሷ አዝማሪ እዝራና ዳዊት በባህርይ
ቃል ኪዳኗ የማይፈርስባት ነዋሪ
እኛን ይዛ ፍጥረት ዓለምን መካሪ
ወለላዊት ቤዛዊት ዓለም ብፅህት
ከወተት ታምርሽ ጥዑም ትሁት
ከወለላ ታምርሽ ሲበላ
የብርሃን ዘውድ የብርሃን አክሊል ደፍተሽ
ድረሽልኝ በሠረገላ ሆነሽ
ይሸሻሉ ሰይጣናት አንቺን ሲያዩሽ
ያንን ግሩም ያንን ደስ የሚል መአዛ
ወለደችው በቤተልሔም ተጉዛ
ምጥ የለባት በመላእክት እጅ ተይዛ
የታደለች እንደሷ ያለች ብጽህት
የበላውን ሰባ ስምንቱን ነፍሳት
አገባችው በጥርኝ ውሃ ገነት
ከአድማስ አድማስ ወረቀት ቢሆን መሬት
ቀለም ቢሆን የ3ወር ዝናም ከረምት
ቢጻፍ አያልቅ የተአምርሽ ብዛት
ስብሃት ለአብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ
ለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ
የበላኤ ሰብ እመቤት
ነፍሴን አድኛት እባክሽ
ለተራበ ሰው ያላበላ
ለተጠማ ሰው ያላጠጣ
ለታረዘ ሰው ያላለበሰ
6ቱ ቃላት ያልፈፀመ ሰው ወየው
በዚያች ቀን የፍርዱ ለታ
እስኪ ልናገረው የርሱን ልዕልና
የኪሩቤል መቅደስ የሱራፌል ጽና /2/
የዘካርያስ አያት የተቋም ላይ ፋና
የሰሎሞን ሸቶ የዳዊት በገና /2/
የሩሀባን ምግብ የደውያን ጤና
የሙሴ ሐመልማል ያያት ደብረ ሲና/2/
የዳንኤል ጉድጓድ የእንባቆብ ምግብና
የኢሳይያስ ፅንስ የገብርኤል ዜና/2/

- -

ስለ አዳም መፈጠር (ዘርፉ ደምሴ በገና)

ቅኝት - ሠላምታ
ዲያቢሎስን ከሁሉ በላይ አርጐት
በብልጠት አምላክ የሚሆን መስሎት
ፈጠርኩ አለ ይኸንን ዅሉ ፍጥረት
መላእክት ፈጥረኽ አሳየን ቢሉት
ሊፈጥር እጁን ጨመረ ከእሳት
እሳት አውቃ የዲያቢሎስን ትዕቢት
አረገችው እሳት የበላው ጅማት
ተባበሩ መላእክት ሁሉ ሊክዱ
የሰገዱ አብረውት ሲኦል ወረዱ
ጌታም አይቶ የእኩሌቶቹን ሀዘን
እሱ ከዶ ሳያስከዳቸው ሰይጣን
ለማመን ፈጠረላቸው ብርሃን
መላእክትም ይህንን ብርሃን አይተው
ሰገዱለት ቅዱስ እግዚአብሔር ብለው
በኹለት ቀን በተገፖመረ ፍጥረት
ተናግረው ውሃውን ከሦስት
አንዱን ጠፈር አንዱንም ሐኖስ አሉት
አንዱን ብቻ ከናጌብ ወዲያ ዳር ቻ
ሠፈሩበት ሌዋትንና ብሄሞት
በሦስት ቀን በተገፖመረ ፍጥረት
ልታበቅል ምድር ሐመልማል ዘርፈ ቢላት
አበቀለች ከአዝርዕት ጋር አትክልት
በዐራት ቀን እንዳይሠለጥን ጽልመት
ከከዋክብትም ከጨረቃ ጋር ሌሊት
በመዓልትም ፀሐይ ደገኛው ፍጥረት
ተፈጠሩ ለኛ ሊያበሩ በውነት
የጎሙስ ፍጥረት ገና እንደሆነ አይተው
ለታውፅኑ ባህር ዘመድ ዓሣት ብለው
የሚበርን የሚኼደውን በእግሩ
ለአንክሮ ለተዘከሮ ፈጠሩ
ዐርብ ጠዋት አዳም የኛን አባት
ንግበር ሰብ በአርአያ ቢሉት
ተፈጠረ ከመኸለኛው መሬት
ሥራውን በ6 ቀን ፈጽሞ
ዐረፈበት በ7ኛው ዕለት ደግሞ
ሥራችንን በ6 ቀን ሠርተን
እናንተም ከሥራ እረፉ ሲለን
በፈጠሩት በስምንተኛው ዕለት
በሣልስት ብቻውን ሆኖ ቢያዩት
ንግበር ብለው ከጐኑ አንስተው አጥንት
ልትረዳው ሔዋንን ፈጥረው ሰጡት
በአርባ ቀኑ ወስዶ አግብቶታል ገነት
አግብቶትም ወስኖለታል ስርዓት
አትንካ ሲል ከዕፀ በለስ ቅንጣት
ብላ ጠጣ የቀረን ሁሉ ፍጥረት
ከምድር በላይ ከሰማይ በታች ያለው
ፍጥረት ሁሉ ላንተ ይገዛል አለው
ቢቀርብለት ዕፀ በለስን መብላት
ሳይታመም ከህመም በኋላም ሳይሞት
ሊያወርሰው የዲያቢሎስን ርስት

- -

ድንግልም (ዘርፉ ደምሴ በገና)

ቅኝት - ሠላምታ

4245 313 15423 312 45

4245 313 15442 222

ድንግልም በምትወልድበት ወራት
በሮም መንግሥት ባውግስጦስ ቄሳር መንግሥት
ሰው ሁሉ ግብር ሊቆጠር ታዘዘ
የሴፍም ድንግልን ይዞ ተጓዘ
ከገሊላ ከነበረበት መንደር
ቤተልሔም ወደምትባል አገር
ከኤፍራታ ይወጣል ብሎ ንጉሥ
ሚኪያስ የተናገረው ሲደርስ
ሳታፋልስ የወላዶችን ሥርዓት
ከሱጋር ብዙ መላእክት መጡና
አቀረቡ ከጸሎት ጋር ምስጋና
ሊገርዙት እንደ አሪቱ ሥርዓት
ወሰዱት በ8ኛው ዕለት
ስሙን ኢየሱስ ብለው ጠሩት
ደሙ እንዳይፈስ ከዕለተ ዓርብ በፊት
ገረዡ በእጁ የያዘው ስለት . . .
አደረገ በተአምራት ግዝረት
በአርባ ቀኑ ዋኖስ ርግብ ይዘው
በአገር ስምአን የሚባል ነበር
ተጠራጥሮ የድንግሊቱን ነገር
እንደ ትሉ ካልጋ ተጣብቆ ሲኖር
ያን ዕለት ከተኛበት ተነስቶ
በድካሙ በመንፈስቅዱስ ተጽናንቶ
ምኩራብ ገብቶ ከምኩራብ ገብቶ ሕፃኑ
ተቀብሎ ጌታን ቢይዘው ከጭኑ
ታደሰና በዐምስት መቶ ዘመኑ
ወደ ፊት የሚሆነውን ነገር
ተናገረ እጅግ በሚያምር ምስጢር
እንዲደረግ የሰው ሁሉ ድህነት
ተናገረ ነቢያት ሐናም ትንቢት

- -

እስመ አንተ (ዘርፉ ደምሴ በገና)

ቅኝት -

እስመ አንተ አምላከ ሰማይ ወምድር
እስመ አንተ ምሉአ ፀጋ መክብር
ትባላለህ በነግ በሰልስት በቀትር
ኢየሱስ ደግ ባለ ጸጋ ንጉሥ
ኢየሱስ በአፈ ሁሉ ውዱስ
ኢየሱስ ቅዳሴ ሥራ ወነፍስ
አንተ እንጂ ነህ የማትዋረድ አታንስ
ብርቱ ዳኛ ያላንተ የለ ደገኛ
ፈጣሪዬ በከንቱ አለቀች እድሜዬ
ሳልገዛ እያሸነፈኝ ሥጋዬ
ዳሩ ግና አዛኝ እሩህሩህ ነህና
አደራህን የነፍሴን ነገር አትጽና
መበስበስ ደግሞ አለ ገና መፍረስ
መነሣት ደግሞ አለ ገና ፍርድ መስማት
በአንቲቱ እስመ ለዓለም ምህረቱ
መላእክቱ አይሸፍቱበት ከቤቱ ሌላ ጌታ
ያ ላንተ የለም በውነት
ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ
ለዓለም እስከ ዘላለም ድረስ

ስለ ሥነ-ስቅለት (አቶ አለሙ አጋ በገና)

ቅኝት - ሠላምታ

እፀ-ብ ድንቅ እንጂ ነው የጌታ ስቅለቱ/2/
እንዲህ በአርምሞ በእንዲህ ያለ ምክንያት አልቀው ህፃናቱ
የሴፍ ሰሎሜ ጌታ ከነእናቱ
ሆረ ደብረ ቁስቋም ምድረ ግብፅ ሰደቱ
በዚያ በበረሃ በመንከራቱ
ውሃ እየለመነች እመቤት አናቱ
የሄሮድስም ጥፋት ተሰማና ሞቱ
ምድረ ናዝሬት ገባች ከህይወት እርስቱ ከቶ አይቀርም ሞቱ
ወዲያውም ደረሰ ለመምህርነቱ
አርባ ሌሊት መዓልት/2/ ፆመ ወፀሎቱ
በእደ ዮሃንስ በባህረ ዮርዳኖስ የጌታ ጥምቀቱ
ተፅእኖ ገባ በነህስ እድገቱ
ሆሳእና ዳዊት ለአለም መድሀኒቱ
ክሪያላይሶን ብለው ሰግደዋል ካህናቱ
ደቂቀ ሰራዊት አልቀሩም አበይቱ
ጌታችን ተይዞ በጊዜ ሠለስቱ
ወድቆ ተገረፈ ለምለም አካላቱ
ሰቀሉከ እየሱስ ግፍአሙ ዝንቱ
ወለፈ ወለፈ አዕባን ተማቱ
ፀሀይም ጠለቀ ሆነ እንደሌሊቱ
ጨረቃም ደም ሆነ ሸሸ ብርሀናቱ
ከዋክብት ረግፈው ታጡ ካሉበቱ
ሲገርፉት ሲያዳፉት ሲወድቅ በደረቱ ከቶ አይቀርም ሞቱ
በስተኋላ ቆመው ስበው ወደአንገቱ
በስተፊቱ ቆመው ስበው በደረቱ
ስቅሎ ስቅሎ አሉት ሲዛበቱ
ሲገርፉት ሲያዳፉት ሲወድቅ በደረቱ
በከየት ማርያም አዘነች እናቱ
ከቶ አይቀርም ሞቱ ምንም ቢታከቱ
ምድረ ቀራንዮ መስቀል መሰረቱ
ጌታችን ተነሳ በእለተ ሰንበቱ
መነስቆሉ ቀረ መጣ ጌትነቱ
ፅኑ ሽብር ሆነ አይሁድ ተፀፀቱ
ዲያቢሎስ ድል ሆነ ከነ ሰራዊቱ
ቁልቁለት ወረደ በመትህቶ ርስቱ
አዳምን አወጣው ምስለ ብእሲቱ
ወዲያው ገነት መራው ከቀደምት እርስቱ
እፀ-ብ ድንቅ እንጂ ነው የጌታ ስቅለቱ
ከቶ አይቀርም ሞቱ ምንም ቢታከቱ
ምን ቢሰነብቱ ከቶ አይቀርም ሞቱ

- -

ማን ይመራመር (አቶ አለሙ አጋ በገና)

ቅኝት - ሠላምታ

315515 45 131 13

155513 242 /2/

31113 242 31113 242 42 4222 22

ማን ይመራመር
ያንተን ሥራ ያንተን ክብር
ማን ይመራመር

አዳምና ሔዋን ጠፍቷቸው መንገዱ /2/
ለሰው ልጅ መከራን ትተውለት ሄዱ
እስከዚያው ድረስ ነው ሲሶ ማረሳችን
እንገባው የለም ወይ በየመሬታችን

አለህም እንዳልል እንዲህ ይደረጋል /2/
የለህም እንዳልል ይመሻል ይነጋል
እባክህ አምላኬ የምለምንህ /2/
ያጣ ሰው ሳያገኝ አይሙት አደራህን
የታመመ ሳይድን አይሙት አደራህን

አንተ ነህ ይላሉ የዓለም ሁሉ ጌታ
ሰማይና ምድርን ያቆምክ ያለዋልታ
ወዴት እንዴት ይሆን ያለህበት ቦታ
እነግርህ ነበረ እኔ በቆይታ
የሰራችልኝን የእናትህን ወሮታ
ሁልጊዜ አትለይም እሷ ከእኔ እርዳታ
ምግብና መጠጤን በውል አጋጅታ
እግሬን አሳጥባ ዙፋን አዘርግታ
እኔስ ይገርመኛል ከጠዋት እስከ ማታ
ካለሁበት ሀገር አለመለየቷ
ለሁሉ ነው እርሷ ይህ ሩህሩህነቷ
አንቺ አማልጂኝ እንጂ መድኃኒት ለዓለሙ
ወልደ አብ ሲለምን አባ ስረይ ሎሙ
እመቤት እመቤት የዓለም መድኃኒት
እንድታማልጂን በዕለተ ምፅአት
ምንም ክፉ ብንሆን አውቀን ብናጠፋ
አዛኝቷ አስምሪን እናት አትገፋ
ንኡ ና ሑሩ ሲል ሲያደራጅ ለጅሽ
እንደበላኤሰብእ ያድነን ጥላሽ
ያንተን ሥራ ያንተን ክብር
ማን ይመራመር
አለህም እንዳልል እንዲህ ይደረጋል/2/
የለህም እንዳልል ይመሻል ይነጋል

- -

ማን ይመራመር (አቶ ታፈሰ በገና)

ቅኝት-ሠላምታ

ማን ይመራመር /4/
ያንተን ሥራ ያንተን ግብር
እስቲ በስመ አብ ብዬ ሰላምታ ላድርስ
ለአብና ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ
ደግሞም ላመስግን ብዬ ሃሌሉያ
አቤቱ አድነኝ ከዓለም ገቢያ
አስረው ደበደቡት መድኃኔዓለምን
ሰማይና ምድርን ያስታረቀውን
ተይዞ ታሰረ እንደተራ ሽፍታ
እውር ስላበራ ሽባ ስለፈታ
ልብሱን ተገፈፈ ቆሞ በአደባባይ
ታስሮ ተገረፈ አጥንቱ እስኪታይ
የእሾህ አክሊል ደፍተው ተዘባበቱበት
እንደወንጀለኛ ጥፋት ሳይኖርበት
ደብድበው ሰቀሉት መድኃኒአለምን
ምንድነው ጥፋቱ ከቶምን ይኾን
የአለም መድኃኒት ክርስቶስ ስማን
ተጨንቀናል ምህረትን ላክልን
አንተ መድኃኔዓለም የሰው ልጆች ተስፋ
በምህረትህ ጐብኘን ከቶ እንዳንጠፋ
ቅዱሳት እጆችህ ተቸንክረው ዋሉ
ቅዱሳት እግሮቹ ተቸንክረው ዋሉ
በጣም አልቅሱለት ሰዎች ወዮ በሉ
እሥራኤልን መና የመገበ አውርዶ
በግፍ ተሰቀለ ለአዳም ሲል ተዋርዶ
መቃብር ቻለችው እንደ ተራ ሰው
አወይ መድኃኔዓለም ክርስቶስ ወየው
ቸሩ መድኃኔዓለም ታላቁ ባለአልጋ
ሰማይና ምድርን በቃሉ የዘረጋ
ጌታ አማኑኤል ኃያል ነው ንጉሥ
ለወደደው ኹሉ ጸጋን የሚያለብስ
የሕይወትን እስትንፋስ እፍ ያለው በአዳም ላይ
ምድረ ቀራንዮ ዋለ በመስቀል ላይ
የተመላለሱ በገነት እግሮቹ
በሞት ተወሰዱ ተጨፈኑ ዐይኖቹ
እንደ ወንጀለኛ ጥፋት ሳይኖርበት
የእሾህ አክሊል ደፍተው ተዘባበቱበት
ሰማይና ምድርን በእጁ የፈጠረ
ዓለምን ለማዳን ሞቶ ተቀበረ
በሦስተኛውም ቀን ብርሃንን ተላብሶ
በኃይሉ ተነሣ መቃብር አፍርሶ
ወደ ሰማይ ወጣ አረገ በኃሉ
ብርሃንን ላከልን ሰዎች እልል በሉ
ቸሩ መድኃኔዓለም ያለም ሁሉ ተስፋ
በቀኝህ አቁመን መለከት ሲነፋ
ነጋሪት ሲጐሰም ለፍርድ ስትመጣ
አቤቱ ክርስቶስ በጉድ እንዳንወጣ
በጐልጐታ ምድር መድኃኒት ተቀብሮ
ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊቶች አድሮ
በኃይል በሥልጣኑ ከሙታን ተነሣ
አቤቱ ተሻረ የሰው ልጅ አበሳ
ምድረ ቀራንዮ ምድረ ጐልጐታ
የጌታን ትንሣኤ መስክሩ በአልልታ
ለዓለም ግለጹ ሞቱን ትንሣኤውን
ኃላም በክብር ሆኖ ለፍርድ መመለሱን
በክብረ መንግሥቱ ሲገለጥ በሰማይ
የሰው ልጆች ኹሉ ይሉለታል ዋይ ዋይ
አማኑኤል መጥቶ ሊያድን ዓለምን
እርቃኑን ተገልጦ መድኃኒት ሆነን

- -

ከቶ አይቀርም ሞቱ (አቶ አለሙ አጋ በገና)

ቅኝት -

ሞት ፊደል ተምሮ ያነባል ስንል
እንኳን ሊያነብና ገና ያግዛል
እህል ታሟል አሉ በእግሬ ልገስግስ
ሀሞት የለውም ወይ በቅሎማ እስኪደርስ
እኔን መስሎኝ ነበር ደሃ ነው ደካሚ
ለካስ ሁሉም ኖሯል አፈር ተሸካሚ
በሉ እናንተም ሂዱ እኛም ወደዚያው ነው
ወትሮም መንገደኛ ፊትና ኋላ ነው
ለሠሪው ለመስጠት አፈሩን ይጉለሁ
ገል አፈር መሆኑን ተረድቼዋለሁ
እኔስ ፍረድ ቢሉኝ ሞት በደለኛ ነው
አንድ ሰው ለምስል ቀምሶ ቢቀር ምነው
ሞት ይቅር ይላሉ ሞት ቢቀር አልወድም
ድንጋዩም አፈሩም ከሰው ፊት አይከብድም
ሂያጅ ተሳፋሪ ሰዎች ከሆናችሁ
ኧረ ለመቼው ቀን ቤት ትሠራላችሁ
እረገጡኝ ብለህ ምድር አትቆጣ
ይህ ሁሉ ያንተ ነው ሸማውን ቢያነጣ
ዲያቆናት ቀሳውስት ደብተሮች በሙሉ
ለመቀደስ ሲሉ መካን ይወልዳሉ::

- -

በስመ ልዑል (ሶስና በገና)

(ሰላምታ ቅኝት - ይበላ ሀላ)
በስመ ልዑል በስመ አብ
በመንፈስ ቅዱስ ቅኔ ላቅርብ
ፈጣሪ በሰው ትዳኛለሀ
ደሀ ፊት ቆመህ ሲከስህ ደሀ
አባቴ ሞኙ አዳም ተላላ
በጠላት ምክር በለስ ትበላ
አባቴ ምነው አዳም አጅሬ
ህግን አስጥሶ ከሰሰህ አውሬ
እንደምትነግስ ነግሮህ ቀጣፊ
ሽሮ አለበሰህ ቅጠል ረጋፊ
ጠላት ሲመክርህ ተደግፎ ዛፍ
ለካ አለ ቅጣት ጸጋ መገፈፍ
የብርሃን ጸጋ የብርሃን ካባ
በለስ ስትበሉ ወዴት ገባ
ትዕዛዝ መጣስ ህግን መድፈር
ሞትን ያመጣል ያገባል ካፈር
ሄዋን እናቴ አታላይ ሰምታ
እርቃኗን ቆመች ጨለማ ገብታ
ማልቀስ ደግ ነው ያሰጣል ዋጋ
ንስህ መግባት ያስገኛል ፀጋ
ፈጣሪያችን ሆይ ህግን ሰርተህ
እኛ ብንሽረው ምን አመጣህ
ላትጨክን ትራራለህ
ማን ያከብርሃል ሆነህል ደሀ
አዳም ዘንግተህ ሄዋን ስተሽ
እባብን አምነሽ አውሬ ሰምተሽ
እንዴት ከጠላት ትመክሪያለሽ
አዳም ሳይሰማ ትቀጥፊያለሽ
እኔ አላማህም አዳም ንጉስ
ንስህ እኮ ነው የሔዋን ፈውስ
ንስህ ገብቶ በትህትና
ልጆችን ማዳን ሙያ ነውና
አዳም ልጆችህ ህጉን ሰርዘው
ሄዋን ልጆችሽ ፈጣሪን ረስተው
አውሬውን ወደው ጠፍተዋልና
ቆመዋል ይሽው በሞት ጐዳና
አዳምም ጮኸህ ሄዋን ለምነሽ
አንተ አማልደህ አንቺም አግዘሽ
ያንተ ልመና ይረዳልና
ሄዋን አልቅሰሽ ድነናልና
እንደለመነህ እዝራ ሱቱኤል
እንዳሳሰበህ ቅዱስ ሚካኤል
ራራልን ማረን ያንተ ነንና
ለምን ዲያብሎስ ኮርቶ ይዝናና
ፈቃደ ሥጋ እያታለለን
ዲያብሎስ መክሮ አንተን አስጠላን
ታውቃለህና ድካማችንን
ደምስሰህ ፋቀው በደላችንን
አምላክ አቅርበህ ልጆቼ በለን
በእመ ልዑል በድንግል ማርያም
በህያው ስምህ በመድኃኔዓለም
ሥጋ ነፍሳችን እንዳትደክም
መድኃኒታችን በአንተ እንታከም
ከላይ ዙፋንህ ጽርሀ አርያም
እዚህ የመጣህ እንዲድን አለም
ወዲህ ነውና ቢጠራን አዳም
ባርከን ቀድሰን በድንግል ማርያም
በቀራንዮ ሄሎሄ ያልከው
ሰይጣንን መተህ ሀይል ያሳጣኸው
ለኛ ነውና ወደህ የሞትከው
ዲያብሎስ ይሻር ሰውን አይፍጀው
ስለነበረው አሁን ስላለው
የምታውቅ አንተ ስለሚመጣው
አትርሳን አንተ በፍርድ ሰዓት
ሲኦል ይቅርልን ገሀነም እሳት
የነበርክ ያለህ የምትኖር
ምሥጋና ይግባህ እግዚአብሔር
አሜን ይገባል ለመድኃኔዓለም
ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለም

- - - - - - - - - - - - - - - - - - - -

ሰላም ለማርያም (ሶስና በገና)

ቅኝት - ሠላምታ

23 1555 1555 11 31132

23 15 31 113 242 45

423-1 113-1 113 242

ሰላም ለማርያም የአምላክ እናት
የአቤል የዋሂት የአዳም ህይወት
እመቤቴ በምልጃሽ መድኃኒቴ ነሽ
የአብ ቃል መቅረጫ ጽላቱ ለሙሴ
የመንፈስ ቅዱስ ቤት እመቃል ሞገሴ
የርኅራኄ መዝገብ እህተ መላእክት
የጻድቃን ተስፋቸው ጽላተ መለኮት
ትናንት ተጨንቀን በጨለማው ዓለም
ዛሬ ብርሃን አየን በድንግል ማርያም
የኢያቄም እንቁ የሃና ንብረቷ
ሥጋ ነፍሴን እርጂያት ይቅርላት ቅጣቷ
በወንጌል ሰማነው ድንግል የአንቺን ዜና
አማላጅነትሽ ሲገለጽ በቃና
ከዳዊትም ሰማን ድንግል ስለአንቺ ክብር
ወትቀውም ንግሥት እያለ ሲዘምር
በላዔ ሰብ ከሞት ከሲኦል የዳነው
በምልጃሽ ነው እንጂ ሞች በጥርኝ ውሃ ነው
ሊውጡኝ ቢነሱ አጋንንት በመሉ
ስምሽን ስጠራ ትቢያ ይሆናሉ
ጽዮን እመብርሃን ጽላተ ሥላሴ
የበረከት ካዝና ደመወዜና ዋሴ
ሲጨንቀኝ ሲጠበኝ ሲከፋኝ ኑሮዬ
ድንግል አንቺ እኮ ነሽ አጽናኝ አለኝታዬ
ስምሽን ስጠራ ሲታወክ ህይወቴ
አለሁልሽ በይኝ ድንግል እመቤቴ
ድንግል ሆይ አትርሺኝ የዘላለም ልብሴ
ምልጃሽ ያውጣኝ ከሞት ከክፉ ድምሳሴ
የቅዱሳን ካባ የቅዱሳን ኩታ
ጸጋ ሰማዕታት የድሆች አለኝታ
ሹመተ መሳፍንት ቅብዐ ነገሥታት
የሰሎሞን ጥበብ የዳዊት መዝሙራት
ዓለም የዳነብሽ ከሞት ከሲኦል
ለእኔስ እናቴ ነሽ ማርያም ድንግል
አድኚኝ እናቴ ከሥጋ ፈተና
እኔማ ያለአንቺ አልችልም ልጸና
ሸክም የከበደኝ እንግልት ሆኖለሁ
ከእኔ እንዳትለይ አደራ እልሻለሁ
አደራ እልሻለሁ ከጎኔ አትራቂ
ወዳጅ ዘመድ የለኝ ያለአንቺ ጠባቂ
ተሳክቶልኝ ባየው ሀሳቤ ምኞቴ
ድንግል ያላንቺማ ሞች ይፀናል ቤቴ
ልጅሽ እንዳይነሳኝ መንግሥተ ሰማያት
ከኃጢአት ጠብቆ እንዲያኖረኝ ገነት
አንቺ ንገሪልኝ ለዓለም መድኃኒት
ተስፋዬ ነሽና አትርሺኝ የኔ እናት

- -

አባ ግራኝ ሞተ (አቶ አለሙ አጋ በገና)

/ስለ አፄ ቴዎድሮስ/

ቅኝት - ሠላምታ

23 15-15 1515 11 31132

231531 113 242 45

423-1 113-1 113 242

አባ ግራኝ ሞተ የሆዴ ወዳጅ /2/
የሚያበላኝ ጮማ የሚያጠጣኝ ጠጅ
እኔ መዩ ቱርክን ባይ የምሸሽ ነኝ ወይ
ታጠቅ ብሎ ፈረስ ካሳ ብሎ ስም
ዐርብ ዐርብ ይሸበራል ኢየሩሳሌም
እኔ መዩ ቱርክን ባይ የምሸሽ ነኝ ወይ
ሺህ ገመር ሺህ ጎራች የሸዋ ፈረስ
አንድ ጥርኝ ሆነ ቢዘልቅ ቴዎድሮስ
እኔ መዩ ቱርክን ባይ የምሸሽ ነኝ ወይ
ፈረሱ አባ ታጠቅ ስሙ ቴዎድሮስ
ጠላት የሚበትን እንደ ዐውሎ ንፋስ
እኔ መዩ ቱርክን ባይ የምሸሽ ነኝ ወይ
መቅደላ አፋፉ ላይ ጩኸት በረከተ
የሴቱን አናውቅም ወንድ አንድ ሰው ሞተ
እኔ መዩ ቱርክን ባይ የምሸሽ ነኝ ወይ
መቅደላ መቅደላ አንቺ ክፉ ጎራ
ሴቱን ሁሉ ንቆ ሲኮራ ሲኮራ
ወንዱ አንቺን ወደደ ተኛ ካንቺ ጋራ
እኔ መዩ ቱርክን ባይ የምሸሽ ነኝ ወይ
አያችሁት ወይ ያንበሳውን ሞት
በሰው እጅ መሞትን ነውር አድርጎት
እርሳሱን እንደጠጅ ጎርሶ ሲጠጣት
እኔ መዩ ቱርክን ባይ የምሸሽ ነኝ ወይ
አውሮፖም ያውቁሃል አፍሪካም ያውቁሃል እስያም ያውቁሃል
እንኳን የሰው ንጉሥ ውሃ እንኳን ፈርቶሃል
እኔ መዩ ቱርክን ባይ የምሸሽ ነኝ ወይ
አባትና እናቱ ያለ አንድ አልወለዱ
አባ ታጠቅ ካሳ ያ ወንዱ ያ ወንዱ
እኔ መዩ ቱርክን ባይ የምሸሽ ነኝ ወይ
የትግሬንም ንጉሥ ሲንቁ ሲንቁ
የሸዋንም ንጉሥ ሲንቁ ሲንቁ
ወንድ ያለ ራስዎ ገድለውም አያውቁ
እኔ መዩ ቱርክን ባይ የምሸሽ ነኝ ወይ
ገደልን እንዳይሉ ሞተው አገኙዋቸው
ማረክን እንዳይሉ ሰው የለ በእጃቸው
ምን አሉ እንግሊዞች ሲገቡ ሀገራቸው
መቼም ለወሬ አይመቹም ተንኮለኞች ናቸው
እኔ መዩ ቱርክን ባይ የምሸሽ ነኝ ወይ
እንደ አፄ ቴዎድሮስ አላየሁም ኩሩ
ቢመጡ እንግሊዞች ምከር ሊማከሩ
በአርምሞ ሸኙዋቸው ሳያነጋግሩ

- -

ድንግል ስልሽ (ሶስና በገና)

ቅኝት - ሠላምታ

22-4 2315 454 22-4 231311 1

154513 1113 15 454

22-423132 542 54

22-4 2315 454 22-4 231311 154

22-4 2315 454 22-4 231311 1

154513 1113 15 454 5422-22 542 54

ድንግል ስልሽ ማርያም ስልሽ
እንደ በላኤ ሰብ ይጋርደኝ ጥላሽ ድንግል ስልሽ
በጭንቅ ውስጥ ሆኜ ከብዶኝ መከራ
የአምላክ እናት ስምሽን ስጠራ
ታማልጂኝ ዘንድ ልቦናሽ ይራራ /2/
ጭንቄ በረታ ሀዘን ከበበኝ
ኃጢአቴ በዛ ተስፋ ቢስ ሆንኩኝ
ድንግል እመቤቴ ምልጃሽ አይለየኝ /2/
ልጅሽ በሰጠሽ ቃል ኪዳንሽ
ተማተሽ ዘወትር እያማለድሽ
የሰውን ልጅ ሁሉ ታስምሪዋለሽ /2/
ስምሽ እንደ ማር እየጣፈጠኝ
ደግነትሽም እየመሰጠኝ
ሁሌ እዘምራለሁ ልቤን ደስ እያለኝ /2/
እምነቴ ሳስቶ ጽድቅም ባልሠራ
እመቤቴ ሆይ ነፍሴን አደራ
አስታርቀሽ አኑሪያት ከቅዱሳን ጋራ /2/
ድንግል በሀና በእናትሽ
በኢያቄምም በአባትሽ
ተማጽኜሻለሁ ልቁም በፊትሽ /2/
አንቺን ስጠራ ልቤ ይረካል
ሀዘኔ ርቆ ሰላም ይተካል
ለሀዘንተኞች ተስፋ ከቶ እንዳንቺ የታል /2/

- -

ርግብና ዋኔን (አቶ ታፈሰ በገና)

ቅኝት- ዋኔን (ትዝታ)

4444 553 115 42

4445 253 115 42

33 11 33 4231 42

33 11 33 422 42

ርግብና ዋኔን ዋኔን አብረው ዘመቱና ዋኔን
ርግብ ደህና ገባች ዋኔን ዋኔን ገደሉና ዋኔን
እስቲ በስመአብ ብዬ ዋኔን ልጀምር ውዳሴ ዋኔን
ማርያም በመሆኗ ዋኔን ክብሬና ሞገሴ ዋኔን
ሰላም እልሻለሁ ዋኔን ጽላተ ጽዮን ዋኔን
ደጅ እጠናሻለሁ ዋኔን አምኜ አንቺን ዋኔን
አዛኝቷ እመቤት ዋኔን ኪዳነ ምህረት ዋኔን
አለሁልህ/ሽ/ ብለሽ ዋኔን አውጪኝ ከመአት ዋኔን
እስቲ ሁላችሁም ዋኔን ኪዳነ ምህረት በሉ ዋኔን
መድኃኒት ናትና ዋኔን ለሰው ልጆች ኹሉ ዋኔን
ሁሌ እጠራሻለሁ ዋኔን በቃል ኪዳንሽ
የምህረት አማላጅ ዋኔን ድንግል አንቺ ነሽ
የዓለም ፈርጥ አንቺ ነሽ ዋኔን ማርያም እመቤቴ ዋኔን
እመካብሻለሁ ዋኔን እስከ ጊዜ ሞቴ ዋኔን
ያንን የእሳት ባህር ዋኔን አሻርጊኝ ድንግል ዋኔን
እንዳወድቅ አደራ ዋኔን ከሲኦል ገደል ዋኔን
የነቢያት ትንቢት ዋኔን ተሰማእታት አክሊል ዋኔን
ያላንቺ ማን አለኝ ዋኔን እመቤቴ ድንግል ዋኔን
ያዕቆብ በህልሙ ዋኔን ያያት መሰላል ዋኔን
የዓለም አስታራቂ ዋኔን አንቺ ነሽ ድንግል ዋኔን
ታማልደናለች ዋኔን እጆቿን ዘርግታ ዋኔን
ከቶ እረፍት የላትም ዋኔን ከጧት እስከ ማታ ዋኔን
ኪዳነ ምህረት ነሽ ዋኔን አንቺ የኛ ተስፋ ዋኔን
መርቆ የሰጠን ዋኔን አልፋና አሜጋ ዋኔን
የዓለም ሀሁሉ መቅረዝ ዋኔን መንበረ ሥላሴ ዋኔን
መድኃኒቴ እሷ ነች ዋኔን ለሥጋም ለነፍሴ ዋኔን
ሁሌ ላመስግናት ዋኔን ተፈታ ምላሴ ዋኔን
የምህረት ቃል ኪዳን ዋኔን የሰውልጅ መዳኛ ዋኔን
እንድታማልደን ዋኔን የተሰጠች ለኛ ዋኔን

ምላሴ ተናገር ዋኔን የማርያምን ዝና
ለኛ መሰጠቷን ዋኔን ሳትፈጠር ገና ዋኔን
ታስባ ስትኖር ዋኔን በእግዚአብሔር ሕሊና ዋኔን
ተወልዳ አደገች ዋኔን ጊዜው ደረሰና ዋኔን
ዘመን የማይሽረው ዋኔን ስላላት ቃል ኪዳን ዋኔን
ታማልደናለች ዋኔን መድኃኒት በመሆን ዋኔን
ምን ቃላት ይገኛለ ዋኔን እርሷን ማመስገኛ ዋኔን
እነ ሕርያቆስ ዋኔን ያልቻሉት እነኛ ዋኔን
ከዐይኗ እያዘነበች ዋኔን የእንባዋን ዘለላ ዋኔን
ወደ ግብፅ በረረች ዋኔን አንድ ልጇን አዝላ ዋኔን
ፅጌ ፀዐዳ ነች ዋኔን እመቤቴ ድንግል ዋኔን
ድረሺልን ሲሏት ዋኔን ከተፍ ነው የምትል ዋኔን
የፃድቃን እመቤት ዋኔን የኃጥኣን ተስፋ ዋኔን
ወዳንቺ እፎህለሁ ዋኔን ሳዝንና ስከፋ ዋኔን
በላኤ ሰብን ዋኔን ያዳንሽው ድንግል ዋኔን
ለእኔም አትንፈጊኝ ዋኔን ይህን እድል ዋኔን
ስንቅ የለኝ ለነፍሴ ዋኔን እንዴት ልሆን ነው ዋኔን
ድንግል እመቤቴ ዋኔን መግቢኝ አንቺው ዋኔን
ጥላሽን ጣይብኝ ዋኔን ኪዳነ ምህረት ዋኔን
ስጨነቅ ስጠበብ ዋኔን ስጋለጥ ያን ዕለት ዋኔን
ድንግል መድኃኒት ነሽ ዋኔን ለሰው ልጆች ሁሉ ዋኔን
ከገኔ ቁሚልኝ ዋኔን ሳዝንና ስከፋ ዋኔን
የዓለም መድኃኒት ነሽ ዋኔን ማርያም እመቤቴ ዋኔን
በረድኤት ግቢልኝ ዋኔን ነይልኝ ከቤቴ ዋኔን
አደራሽን ማርያም ዋኔን ኪዳነ ምህረት ዋኔን
ፀጋሽን አልብሽኝ ዋኔን ኋላ ስራቆት ዋኔን
ዕርቃኔን መሆኔን ዋኔን አውቀዋለኩና ዋኔን
አልብሽኝ ፀጋሽን ዋኔን በኢያቄም በሃና ዋኔን
እስቲ ሁላችሁም ዋኔን ኪዳነ ምህረት በሉ ዋኔን
መድኃኒት ናትና ዋኔን ለሰዉ ልጆች ሁሉ ዋኔን
አፍሮ አይመለስም ዋኔን የቆመ ከደጇ ዋኔን
እምቤቴ ማርያም ዋኔን የጭንቅ አማላጇ ዋኔን
የአዳም መድኃኒት ዋኔን አንቺ ነሽ ድንግል ዋኔን
በኢያቄም በሃና ዋኔን አውጭኝ ከሲኦል ዋኔን
አንቺ የኤዶም ገነት ዋኔን የሰው ልጆች ተስፋ ዋኔን
መድኃኒት ነሽና ዋኔን አዝኖ ለተከፋ ዋኔን
የዓለምን መድኃኒት ዋኔን በጀርባሽ አዝለሽ ዋኔን
አረ ልምን ይሆን ዋኔን ቁራሽ የለመንሽ ዋኔን
ፍግም ብዬ ልስገድ ዋኔን ለእመቤቴ ድንግል ዋኔን
እርሷ በመሆኗ ዋኔን የሰው ልጆች እድል ዋኔን

- -

ዋኔን (ሶስና በገና)

(በሰላምታ ቅኝት)
እስኪ ሰላም ብዬ ዋኔን ልጀምር ውዳሴ ዋኔን
አንተ አይደለህም ወይ ዋኔን መዓዛ ለነፍሴ ዋኔን
ምነው ከጠቢቦች ዋኔን ዝምድና ቢኖረኝ ዋኔን
ሥጋ ሞልቶ ሳለ ዋኔን መቁረጫው ቸገረኝ ዋኔን
እኔ እየመሰለኝ ዋኔን ሳላስበው ድንገት ዋኔን
ያንን ልብ ሥጋ ዋኔን ለውሻ ሰጠሁት ዋኔን
የጠቢቦች አባት ዋኔን አንተ መሰልከኝ ዋኔን
መልካም አይነት ጥበብ ዋኔን እንድትሰራልኝ ዋኔን
ጃኖማ ሁልጊዜ ዋኔን እለብስ የለም ወይ ዋኔን
ብርቅ ይሆንብኛል ዋኔን ጥበብ ለብሰው ሳይ ዋኔን
ወዳንተ ስመጣ ዋኔን መንገዱ ጠፍቶኝ ዋኔን
መልሶ መላልሶ ዋኔን እንቅፋት መታኝ ዋኔን
አዝግሜ መጥቼ ዋኔን ካንተ እንዳልገናኝ ዋኔን
ውስጥ እግሬን ሆነና ዋኔን አላስኬድ አለኝ ዋኔን
ሥጋዬ ላመሉ ዋኔን ሜዳ ሲል ተራራ ዋኔን
ውሃ ጠምቶት ቆሟል ዋኔን ቢመጣ መከራ ዋኔን
አምላኬ በሰማይ ዋኔን በምድርም ያለኸው ዋኔን
ሊጠፋ ነውና ዋኔን ዓለምን ታደገው ዋኔን
ብርብር ብላ ዋኔን ሄዳ ካጠገቤ ዋኔን
ሳትመለስ ቀረች ዋኔን ተቅበዝባዧ ልቤ ዋኔን
ምርቃቱንማ ዋኔን ችዬበት ነበረ ዋኔን
አለማመኔ ግን ዋኔን ሲያዋርደኝ ኖረ ዋኔን
በልቼ እንዳላድር ዋኔን ቆርጥሜ ከጥሬው ዋኔን
መምህሩ አይደሉም ዋኔን የጐዳኝ ረዱ ነው ዋኔን
እሜቴ መቃብር ዋኔን መጥታ እንደንግዳ ዋኔን
ጥሬ አልበላም አለች ዋኔን ሥጋ ብቻ ለምዳ ዋኔን
ጫጩት ከበዛበት ዋኔን አደርኩኝ ጉብቼ
አዬ ልብ ማጣት ዋኔን ቅንቅኑን ረስቼ ዋኔን
ሜዳውን ቢኖጡ ዋኔን አይድከሙ አይለፉ ዋኔን
የሰው ሁሉ ዕዳ ዋኔን አፋፈ ነው ክፉ ዋኔን
ወደ ኢየሩስአሌም ዋኔን ልሄድ ኹሌ ስመኝ ዋኔን
እንጀልኝ አሁንስ ዋኔን ዝቋላም እራቀኝ ዋኔን
ዛሬስ ታርቀኝ ኑሪ ዋኔን ሥጋ ከነፍስኝ ዋኔን
ጾምና ጸሎትን ዋኔን አማላጅ ይዘሽ ዋኔን
እመቤቴ ማርያም ዋኔን ሳንኳኳ ደጅሽ ዋኔን
ማርማር ብለሽ ለኔ ዋኔን ጠይቂው ልጅሽን ዋኔን

- -

ስቀለው ስቀለው (ሶስና በገና)

ቅኝት - ዋኔን
542 2 423 3 1513 545131 (5451131) 4222 542
542 2 423 3 351213 5451131 422222
554222 45 545115 5451131 422222

ስቀለው ስቀለው እያሉ
አይሁድ ባንተ ላይ ተማማሉ
እውነተኛ ዳኛና አንተ ሆነህ ሳለ
የጲላጦስን ፍርድ ፍቅርህ ተቀበለ
ጌታ ይቅር በለን /2/
ምንም ብንበድልህ የእጆችህ ሥራ ነን/2/
ተጠማሁ ተጠማሁ እያለ
በቀራንዮ ላይ መስቀል ላይ ሆነልን
የአፍላጋት ጌታ አንተ ሆነህ ሳለህ
ሆምጣጤ አጠጡህ ሳለህ ተቸግረህ
ማን መታህ ንገረን እያሉ
ፊቱን እየጸፉት ሲሳደቡ ዋሉ
ምንም አልመለሰ ምነውም አላለ
ህማሙን በትዕግስት አውቆ ተቀበለ
ምራቅ እየተፉ ፊትህ ላይ
ሲመቱህ ሲሰድቡህ ስትሰቃይ
ምንም ሳትመልስ በፍቅር አየሀቸው
በመስቀል ሰቀሉህ ወደህ ሞትከላቸው
ይቅር ባይ ነህና መሀሪ
ትህትና ፍቅርን አስተማሪ
ጠልተው ለሰቀሉት ለተፉት በፊቱ
ምህረትን ጠየቀ ከአብ ከአባቱ
መከራህን ሳስብ ስቃይህን
መስቀል ላይ እንደዋልክ እርቃንህን
ነፍሴ ተጨነቀች እጅጉን አዘነች
ፍዳና በደሏን እያሰላሰለች

- -

ኢትዮጵያ ሆይ ተነሽ (ይልማ ኃይሉ በገና)

ቅኝት - ዋኔን

213 24552 42 421-11553 23

213 24552 42342 22-2 42

15-11342 42421-11553 23

15-11342 42452-22-2 42

ኢትዮጵያ ሆይ ተነሽ ክብርንም ልበሽ
በአዲስ ምሥጋና ይመላ ልብሽ
የተወደደ ነው በእግዚአብሔር ህዝብሽ/2/
ንብረቱ ጠፊ ነው ከንቱ የማይረባ
በግፍና ቅሚያ በአመፅ ሲገነባ
ሲሳይሽ ብዙ ነው ከአምላክ የተሰጠሽ
በረከት ለማግኘት መሥራት ነው ጠንክረሽ
የአህዛብ ብልጽግና አያስቀናሽ ፍፁም
ኃላፊ ጠፊ ነው ምኞቱም ዓለሙም
ደመና ነውና ይበናል በቅጽበት
በግፍ የተገኘ የተከማቸ ሀብት
ይልቅ በቅንነት በሰላም ለሰራ
ሲሳዩ ብዙ ነው ክብሩም አያባራ
ጉቦና ፍትህን ማጣመም እንዳንለምድ
ከወንጌሉ ጋራ አለብን መዛመድ
እግዚአብሔር ያለው ሰው በእርሱ የታመነ
ከግፍ ሥራ ሕመም አካላቱ ዳነ
ክርስቲያነኝ ብሎ ጉቦ የሚበላ
የሚያቃጥል እሳት ያገኘዋል ኋላ
በመታመን ፀጋ ይጠራ ስማችን
እውነተኛ እንሁን ለውድ ሀገራችን
የራሱን ሳይሻ ለሀገር የሚያስብ ሰው
በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ ነው

- -

የብርሃን እናት ነሽና (ይልማ ኃይሉ በገና)

ቅኝት - ዋኔን

2423111 1354 2423111

3513122 42311 1 3513122 4222 2

5511523 4222 2 5531215 4222 2

2312115 2111 1 3513123 4222 2

የብርሃን እናት ነሽና የብርሃን እናት
ለምኚልን ድንግል ለምኚልን /2/
ጸጋንና ክብርን የተመላሽ
ከሴቶች መካከል የተመረጥሽ
ለቃሉ ማደሪያ ዙፋን ሆነሽ
በደመና መንበር የተመሰልሽ
የሸቶ መኖሪያ የተቀደስሽ
መዓዛሽ ያማረ ሽቶ ያለሽ
ውዳሴሽ ብዙ ነው እናታችን
ስምሽን እያሰብን ነው መጽናኛችን
በሀሳብ በግብር ፍጹም ሆነሽ
ምንኛ ብሩህ ነው ድንግል ልብሽ
አንቺን የሚመስል የለምና
ይሰማል ምልጃሽ ያንቺ ልመና
የብርሃን መውጫ ምሥራቁ ነሽ
ሰውን ለለወጠ ድልድይ ነሽ
ምሥጋናሽ አያልቅም ለዘላለም
ማህሌት ነሽና በአርያም
መላዕክት ፍጥረትሽን ያደንቃሉ
ጌታን በመውለድሽ ይመካሉ
ሰማይና ምድር ሳይወስኑት
ባንቺ ተወሰነ እፁብ በእውነት

- -

አቤቱ ደግ ሰው አልቋልና (ይልማ ኃይሉ በገና)

ቅኝት - ዋኔን

521-115 1113 4222 42

521-115 1113 4223 23

3524453 1113 4222 42

3524453 1113 4222 42

አቤቱ ደግ ሰው አልቋልና /2/
ከምድርም ፍቅር ጠፍቷልና /2/
እንደ ቸርነትህ አድነን /2/
በደላችንንም አትቁጠር /2/
የረድኤት አምላክ ፍቅር ስጠን /2/
እንደ አህዛብ አታድርገን /2/
ክርስቲያን ነንና እንዋደድ /2/
እባክህ አንውጣ ካንተ መንገድ /2/
አቤቱ ንፁህ ልብ ፍጠርልን /2/
ሰውን የሚያስወድድ ያለ እንከን /2/
አንደበታችን እንዲናገር /2/
ስለ ሰላም ቋንቋ ስለ ፍቅር /2/
በእግዚአብሔር ፈቃድ የሚመራ /2/
ትሩፋት ደግነት የሚሠራ /2/
አንደበቱ ሁሉ የታረመ /2/
ለቃለ ወንጌሉ የደከመ /2/
ምግባርና እውነት የተሰጠው /2/
እባክህ አድለን ሁነኛ ሰው /2/
አንተን የሚመስል በሕይወቱ /2/
ፍቅርና ትህትና የግል ሀብቱ /2/
የማስመሰል ፍቅር እየበዛ /2/
ሰው ረክሷልና እንደዋዛ /2/
ፍፁም መዋደድን ስጠንና /2/
አዲስ ሰው እንሁን እንደገና /2/
ደገኛ ሰው ማግኘት አስቸግሯል /2/
እስከ መጨረሻ ማን ይፀናል /2/
ምግባሩ ትክክል እውነተኛ /2/
ልቡ የሚፀየፍ ከዳተኛ /2/

- -

አልፈርድም እኔ (ይልማ ኃይሉ በገና)

ቅኝት - ዋኔን

31542 2 54513 3 42315 5

31542 2 54513 3 42315 5 42222

አልፈርድም እኔ በንም በደል በማንም ኃጢአት
በፈርድኩበት እንዳልመዘን ጌታ ሲመጣ በኃይል በስልጣን
አዝ
በቸርነቱ አምላክ ባይተወው በደሌን ሁሉ
ውስጤ ቢፈተሽ በተሰጠኝ ሕግ በቅዱስ ቃሉ
በምን ምግባሬ በሰው እፈርዳለሁ አይኔን አቅንቼ
በደሌ በዝቶ ለራሴ ሳላውቅ በኃጢአት ሞቼ
አዝ
ይልቅ የአንዱን ሸክም ሌላው ሰው አዝሎ መጓዝ ይሻላል
መፍረድ ከመጣ አንድም ሰው አይድን ሁሉም በድሏል
ወንድም ወንድሙን እየከሰሰ ለፍርድ አቁሞ
አህዛብ ያያል በንትርኩ እጅግ ተገርሞ

አዝ
ክርስቲያን ሆኖ ከወንድሙ ጋር እየተጣላ
ዓለም ዳኝቸን በፀብ ፍርድ ቤት ታረቁ ብላ
ክርስቲያን ሆነን በአሕዛብ መሀል እየተካሰስን
አምላክ አዘነ የመስቀሉን ዓላማ ስተን
አዝ
መቼ ከሰሰ የከሰሱትን የገረፉትን
አይተናል ሲምር ለጠላቶቹ ምህረት ሲለምን
ለጽድቅ ሥራ ለእውነት ብለን መጥተናል እንጂ
ማነው የሾመን በወንድሞች ላይ አድርጎ ፊራጅ

ኑ እንቅረብ (ሊቀ መዘምራን ኪነጥበብ)

ቅኝት - ዋኔን
11234 342 355 5
11234 342 222 2
211-513 22 211-513 33
211-513 342 222 2
111321 1 444 515 5
333 242-4 2342-222
ኑ እንቅረብ መጠራት ሳይመጣ /2/
ሥጋውን እንብላ ደሙንም እንጠጣ
የቀራንዮ በግ የአምላክ ሥጋው
ተሰውቶልናል እንመገበው
እድፋን ኃጢአታችንን በንስሓ አንፅተን
እንቀበል አምነን በልጅነታችን
መቅረብ ወደ ጌታ በእምነት የሚገባው
በስተርጅና አይደለም በወጣትነት ነው
ጨረቃና ፀሐይ ደም የለበሱለት
ከዋክብት ከሰማይ የተነጠፉለት
ይኸው ተፈተተ እሳተ መለኮት
ቅድስት እናታችን ቤተክርስቲያን
ትጋብዘናለች ሥጋና ደሙን
የአማኑኤል ሥጋ ይኸው ተዘጋጀ
ከግብጣው ተጠራን አዋጁም ታወጀ
መጥቁ ተደወለ እንቅረብ በእልልታ
በኋላ አይረባንም ዋይታና ጫጫታ
ይህችን እድል ፈጥነን እንጠቀምባት
ዓለምን አልያዝንም ብዙ ልንቆይባት
ካሁኑ ቅረቡ ታውጇል አዋጁ
የይለፍ ደብዳቤ ስንቅን አዘጋጁ
ይህ ዓለም ጠፊ ነው በሀብት አትመኩ
ብሏል አምላችን ተስፋችሁን እንኩ

ማኔቴቄልፋሬስ (ይልማ ኃይሉ በገና)

ቅኝት - ***ሠላምታ***
222 421 <u>1 231</u> 5455 311 <u>1 231</u>
222 445 <u>5 315</u> 5455 311 <u>1 231</u>
<u>ዋኔን</u>
555 152 <u>2 542</u> 3133 422 <u>2 542</u>
545 113 <u>3 423</u> 3133 422 <u>2 542</u>
ማኔቴቄልፋሬስ /4/
የሰዎች መሰረት እዩት ሲገረሰስ
ማኔቴቄልፋሬስ /2/
በእውነት መስፈሪያ ተመዝነህ ነበር
የልብህ ትዕቢት ግን አዘቀጠህ እንዳፈር
ቆረጠው ዘመንክን ቅጥፈቱ አጀበህ
በለጋነት ዕድሜህ ወደሞት ተጠራህ
ዳንኤል የታለ አሁን የሚገስጽ
በመንፈሱ መብራት ወገንን የሚያንጽ
አብነት የታለ በጸሎት የተጋ
የህሊናን ወጀብ በፍቅር የሚያረጋ
አምላክ ያላነፀው የእንቧይ ካብ ተንዶ
የትናንቱ ትልቅ ማምሻውን ተዋርዶ
እንደ አበባ ፈክቶ ሲረግፍ እያየነው
ዛሬም ልቦናችን ለትእቢት ጽኑ ነው
ቀይ ባህር ሲሰጥም ያለፈው ፈርኦን
ዛሬም የአምላክን ህዝብ አንለቅም ብለን
እንደጠጣር አለት ጠንክሮ ልባችን
ደግሞ ተፈጥረናል ፈርኦን ነን ብለን
- - - - - - - - - - - - - - - - - - - -

ድንግል ወላዲተ ቃል (ሊቀ መዘምራን ኪነጥበብ)

ቅኝት - ዋኔን (ትዝታ)
2111 2344 5223511
21112344 342 222 2
3542 222 254 234 2 255 5
ድንግል /2/ ወላዲተ ቃል /2/
አሟሟትሽ በጠር ነሐሴ መቃብር ድንግል
ያንቺስ ለብቸ ነው ትንሳኤሽ ሲነገር "
ሥጋሽ በምድር ላይ የትአለ እንደፍጡር "
ዐርጓል ወደ ሰማይ ከክርስቶስ መንበር "
ሥጋሽን ሲያሳርጉ መላእክተ ሰማይ ድንግል
ቶማስ በደመና ሲመጣ መንገድ ላይ "
መግነዝ ተረከበ ለሐዋርያት ሊያሳይ "
ትንሣኤሽን ሽተው ግራ ሲገባቸው ድንግል
ሐዋርያት ፆመው ተገለጽሽላቸው "
ተቀብራ አልቀረችም በምድር ከደጇ "
ወደ ላይ ዐረገች እሷም እንደልጇ "
ለማየት ሲጓጉ የድንግልን ትንሳኤ ድንግል
እርገቷን አወቁ በንፁህ ሱባኤ "
እኛም እንፀልይ ደጃችን እንዝጋ "
ከወላዲተ አምላክ እንድናገኝ ዋጋ "
- - - - - - - - - - - - - - - - - - - -

ሞቼ ስለማልቀር

<u>ቅኝት- ዋኔን (ትዝታ)</u>
4222 15 5 554421 11
1151323 33 3313 242 2

ሞቼ ስለማልቀር ትንሣኤ ስላለኝ
በሰማይ ቤታችን ስለምንገናኝ
ወዳጅ ዘመዶቼ አታልቅሱ በቃኝ /2/
አገኛለሁና ገና አዲሱን ኑሮ
አምላክን አስቡት ይብቃችሁ እሮሮ /2/
ዓለም ኪራይ ቤት ናት ዘላቂ አይደለችም
ለሥጋ ነው እንጂ ለነፍስ አትመችም /2/
ግን በርሷ ስንኖር ትዕዛዙን ከፈፀምን
ለተዘጋጀው ቤት ወራሾች እኛው ነን/2/
ይልቅ ጸልዩላት ለነፍሴ እረፍት
በቀኝ እንዲያቆማት የጻድቃን አባት /2/

- - - - - - - - - - - - - - - - - - - -

ምድረ ቀራንዮ

ቅኝት- ዋኔን (ትዝታ)

4231532 423511 4

4231532 422222

ምድረ ቀራንዮ ምድረ ኅልኅታ
መድኃኒት ክርስቶስ በአንቺ ተንገላታ
መስከሪ አንቺ ምድር ግእዚቷ ሥፍራ
መድኃኒት ክርስቶስ ያየብሽ መከራ
ደሙ እንደውሃ ሲፈስ ከመስቀል ላይ
በቀራንዮ መዳን መከራውን ሲያይ
ፀሐይ ከለከለች ለመስጠት ብርሃን
ለመሸፈን ብላ የአምላክን እርቃን
ሁሉንም ለማድረግ ሥልጣን ቢኖረው
በእንጨት ተሰቅሎ ፍቅሩን ገለፀው
በመስቀል ላይ ሆኖ ተጠማሁ እያለ
የእሾህ አክሊል ደፍቶ ቀራንዮ ዋለ
እጆቹና እግሮቹ በችንካር ተመተው
ይቅርታ አደረገ ለዚህ ኃጢአታቸው
ቸሩ መድኃኔዓለም እባክህ ማረን
ደካሞች ነንና እንዳንቀር ጠፍን
በቆረስነው ሥጋህ ባፈሰስከው ደም
አቤቱ ተራዳን ለዘለዓለም

- -

የአብርሃም አምላክ

ቅኝት- ዋኔን (ትዝታ)

5-2-2-234-2 515-3545 5 /2x/

25231513-1 24-2-5232 2 /2x/

የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም ቤዛ
ወገኖቹን ሁሉ በራሱ ደም ገዛ
የሐሰት ምስክር አቁመው ከሰሱት
በሞት እንዲቀጣ ሁሉም ፈረዱበት
ጲላጦስ ገረፈው በሰንሰለት አስሮ
ከሮማዊው መንግሥት እንዲኖር ተባብሮ
ድንግል አልቻለችም እንባዋን ልትገታ
እያየች በመስቀል ልጇ ሲንገላታ
በብርሃን ዙፋን ላይ የቆሙት እግሮቹ
በችንካር ላይ ቆሙ ምንም ሳይሰለቹ
የብርሃን አክሊልን ለሰማዕት ያደለ
የእሾህ አክሊል ደፍቶ ቀራንዮ ዋለ

- -

እንደቸርነትህ

ቅኝት - ዋኔን

እንደ ቸርነትህ አቤቱ ማረን /2/
እንደ ምህረትህም ይቅርታን ስጠን /2/
ከኃጢአቴም አንፃኝ ከክፉ በደሌ /2/
ለዚያች ክፉ ኃጢአት እንዳልሆናት ሎሌ /2/
አንተን ብቻ በደልኩ ክፉም አደረግሁ /2/
አሁን ይቅር በለኝ ከፊትህ ወደቅሁ /2/
ከፊትህ ወድቄ ስለምን አንተን /2/
መውደቄን ተመልከት አምላክ ብርሃን /2/
አሁን ትባርክ ዘንድ ማኅበራችንን ጸሎታችንን
ጌታ ሆይ ላክልን ቅዱስ ሚካኤልን ቅዱስ ገብርኤልን
አሁን ትጠብቅ ዘንድ ሀገራችንን ኢትዮጵያን
ጌታ ሆይ ላክልን ጸራቅሊጦስን መንፈስ ቅዱስን

- -

በደምህ ተገዛ

ቅኝት- ዋኔን

422 424515 422 3135 /2x/

545 5 3132 2 454245

545 5 3132 2 454222

በደምህ ተገዛ የጠፋው ዓለም
ሃሌ ሃሌ ሉያ አምላክ ሠላም /2/
በደምህ እጠበው ኃጢአታችንን /2/
ሃሌ ሃሌ ሉያ የዓለም መድኅን /2/
ሞትን ያሸነፍከው የሠራዊት ጌታ /2/
ሃሌ ሃሌ ሉያ ለነፍሳችን ዋልታ /2/
ወንዞች ተነሱ አንተን ለማመስገን /2/
ሃሌ ሃሌ ሉያ አምላክ ብርሃን /2/
ወንዶችና ሴቶች ሕፃናትም ሁሉ /2/
ጌታን አመስግኑ እልል እልል በሉ /2/

- -

ስለ ቸርነትህ (ይልማ ኃይሉ በገና)

ቅኝት - ስለቸርነትህ

231542-3 45-13-42 /2x/

231542-3 231515 /2x/

ስለ ቸርነትህ ጌታ ተመስገን
ስለ ፍፁም ፍቅርህ አምላክ ተመስገን
ማነው የገሙተ ከዛሬ መድረስን
ልብሱ ሳይነካ በእሳቱ ወላፈን
ባህሩን አሻግሮ ማዕበል አቁሞ
እርሱ ያውቅልናል ለመጪው ቀን ደግሞ
ሃሌ ሃሌ ሉያ መስዋዕት እናቅርብ
ጌታ ይፈልጋል የተሰበረ ልብ
ክርስቶስ ከሌለው ፍቅር ላይኖረው
ሰላም ሰላም ይላል ፍጥረታዊው ሰው
ሰላም ሰላም ይላል የዘመኑ ሰው
የኢየሱስ ነገር ለሚጠፉት ሁሉ
የመስቀሉ ነገር ለሚጠፉት ሁሉ
ሞኝነት መስሏቸው ከህደት ተሞሉ
የስንፍና አመል እያናወዛቸው
መጸም መጸለዩ ይጎዳናል ብለው
አምላክን ቢክዱ ፍቅርን ነፈጋቸው

- -

መጾሙን ይጾማል

ቅኝት- ስለቸርነትህ

15-1515 151515 151551 42 (52-4511 42)

231551 112342 2 2323254 13 544442 45131542

መጾሙን ይጾማል ሁሉም የአዳም ልጅ /2/
የጊዜውን መድረስ የሚያውቅ የለም እንጂ /3/
ይደርሳል ሰዓቱ ሳስብ ሌላ ሌላ /2/
የተሰቀለውን ሥጋውን ሳልበላ /3/
ድኅ ጾመ ድኅ ተሰቅሎ ከቤቴ /2/
አወይ አለማወቅ ሳልማር መቅረቴ /3/
ደግሜ ደግሜ ቀረኝ አሌፋቱ /2/
አድኅነኒ ሣልል አትጥራኝ በከንቱ /3/
እኔስ እሄዳለሁ አጣቢ ፍለጋ /2/
በጣም አድፎብኛል የለበስኩት ሥጋ /3/

ዳዊት እንዴት ይሙት ሳልተዋወቀው /2/
የሚመጣውን ሁሉ በገና የሚያውቀው /3/
ዐርብ ረቡን ገደፈኩ በሥጋ በአዋዜ /2/
እንዲህ ለሚደርሰው ለማይቆየው ጊዜ /3/
ከሥጋው ሳልበላ ተጠይፌ ደሙን /2/
ማን ይችለው ይሆን የላይ ቤት ረሃቡን /3/
ከንብረቴ ሁሉ አልጋዬ ነው ሀብቴ /2/
አድርሶኝ ይመጣል ከዘላለም ቤቴ /3/
ብልህ ነው ስትሉኝ እዩት ሞኝነቴን /2/
በራሴ ላይ ሆኖ አላውቀውም ሞቴን /3/
መማሩንስ ዳዊት ተምሬ ነበረ /2/
ከአምላኪየ ሳልደርስ ልቤ ሰንፎ ቀረ /3/
እንኳን ነአኩተከ በስመ አብም ቸገረኝ /2/
ዳዊት እንዴት ተማርክ እባክህ ንገረኝ /3/

- -

አምላኬ አምላኬ (ይልማ ኃይሉ በገና)

ቅኝት - ስለቸርነትህ
አምላኬ /3/ ፈጣሪ አምላኬ አምላኬ
ስለው ደስ ይለኛል
በቸገረኝ ጊዜ ከተፍ ይልልኛል /2/
አይቀርም ሞቱ
እንባ እየወረደ /2/ ሆዴን ምነው ከፋው
አምላክ እያለልኝ የችግሬ መፍቻው /2/
አይቀርም ሞቱ
ሰማዩም መሬቱም ደጋውም ቆላውም ባህሩም ጠፈሩም
ሁሉም ያንተ ሀገር ነው
ልቤ ከወደደው ብሰነብት ምነው /2/
ከአዳም ልጆች መሀል ልቡናው የጠፋ ማሰብ የተሳነው
በሰው ግፍ ይሰራል ተዘጋጅቶ ጽዋው/2/
አይቀርም ሞቱ
ይሄ ቂላቂሉ የዋህ ሞኛሞኙ ጥበብ የጐደለው
እህል ያከማቻል ስንቅ እየመሰለው/2/
አይቀርም ሞቱ
ታላቅ ባለሞያ ጉዳዩ የገባው የተመራመረው
የነፍስ ስንቅ አማዞ በሰማይ አኖረው /2/
ከቤተስኪያን ጓሮ /2/ ሰው እየዘራችሁ
ሲበሰብስ እንጂ ሲበቅልን አያችሁ /2/
ካጣቢውም ቢሆን ከሳሙናው ቢሆን ከእንዶዱም ማነስ
አፈር መስሎ ታየኝ የሰው ሁሉ ልብስ /2/
ሥጋ ሥጋ ሽተትክ /2/ ለምን ትለኛለህ
ይህን እርጥብ ስጋ ለብሼው እያየህ /2/
እኔስ እሄዳለሁ ሳሙና ፍለጋ አጣቢ ፍለጋ
እጅግ አድፎብኛል የለበስኩት ሥጋ /2/
ሰይጣን አታለለኝ/2/ ወርቅ እያፈለቀ
ከቶ ምን ሊበጀኝ ዘመኔ ካለቀ /2/
ሰው ሁሉ እያወቀው /2/ አልሞትም ማለቱ
ይረዳዋል በግድ ሲፈራርስ ቤቱ/2/
ታላቁን ገበያ ጸሎትን ገፍቼው
የጽድቁን መሰላል ምጽዋትን ትቼው
ሕሙማን መጠየቅ ከንቱ እየመሰለኝ
ሞት ይጠራኝ ጀመር ከቶ ምን ይዋጠኝ/2/
ስንቄን ሳላደራጅ ተጠራሁ መሠለኝ
አንተ መጠየቅ ወዳድ ምን ይመልስ ይሆን /2/
ነጣቂ ሳይወስደኝ ሌባ ሳይመጣብኝ
በሬን ልዘጋጋ የሰማይ መንገዴን /2/
አንቺ የፍቅር ድግስ ፍኖተ ሰላም
ወንጌል እናታችን እስከ ዘለዓለም /2/
የወዝ ገንዘቡ በሥጋ የገባው
መከራ መስቀሉ መሞት መነሳት ነው/2/
ሥጋው ከመለኮት ሳይለይ የሠራው
ከመቃብር ያሉን ማስነሳቱ እኮ ነው/2/

- -

በህይወቴ (ይልማ ኃይሉ በገና)

ቅኝት - ስለቸርነትህ
23-42 2 14-15 5
151123-1 1 2223 42
222342 2 141542 2
222342 2 231511 1

በህይወቴ በዘመኔ ደስ የሚለኝ ለኔ በወንጌል ማመኔ
ሕይወቴ ሲመራ ጌታ በቃልህ
ጣፋጭ ይሆን ነበር ሲያድሰኝ ፍቅርህ
ያንተ ጸጋ ጌታ ስለበዛልኝ
ጨለማው ተገፎ ብርሃንህ መራኝ
ወዴት እሄዳለሁ የእጅህ ጥበብ ሆኜ
ፍቅርህ እያደሰኝ ሞተህልኝ ድኜ
ምን አይነት መውደድ ነው ለኔ አንተ ያለህ
ምን ይከፈለዋል ለፍፁሙ ፍቅርህ
ምን አይነት መውደድ ነው አንተ ለኔ ያለህ
ምን ይከፈለዋል ለፍፁሙ ፍቅርህ
ደጅህ ላይ ተጥዬ ደጅህ ላይ ልሙት
ቃልህን ልጠብቅ በፍፁም ፍርሃት

- -

ለእኔስ ልዩ ነች (ይልማ ኃይሉ በገና)

ቅኝት - ስለቸርነትህ
233-42 2-42423-15-13 31-31 (2x)
342 2-42423-15-13 31-31
233-42 242423-15-13 31-31
23342 23342 2-42 (2x)
233-42 2-42423-15-13 31-31 (3x)
23342 23342 2-42
ለእኔስ ልዩ ነች ድንግል ማርያም
ለእኔስ ልዩ ነች እመብርሃን
ፈልጌ /2/ ላንቺ ምሥጋና አላገኘሁም /2/
ልቤ ሲያበቅል የኃጢአት አረም
ውስጤ ሲሸፍት አልተወቸኝም
ከቤተ መቅደስ እጇን ዘርግታ
ትጠራኛለች የእኔ መከታ
የሆዴን ሀዘን የልቤን ምሥጢር
እነግርሻለሁ አንድም ሳይቀር
የምትሸሸጊ የሕዝብን ኃጢአት
ለእኔስ ልዩ ነሽ ድንግል አዛኝት
ጣዕሙ ልዩ ነው ከእርሷ ጋር መኖር
ድንግልን ይገፍ መቼም አላፍር
ወደ ጽድቅ ህይወት ትወስደኛለች
ድንግል ማርያም ለእኔ እናቴኮ ነች
በሀዘን ስሰበር ማንን እጠራለሁ
ውስጤ ሲደማ ለማን እነግራለሁ
ከኃጢአት እድፍ ንፁህ መሆኛዬ
አንቺ ነሽ ድንግል የኔስ መጽናኛዬ
የኃጢአት ቁስል ያለአንቺ አይጠርግም
ልጅሽ ሳይፈቅድ በህይወት አልኖርም
ከልጅሽ ሌላ መድህን የለኝም
ከጸሎት በቀር ፍፁም አልድንም

- -

የእኛ ጌታ (ይልማ ኃይሉ በገና)

ቅኝት - ስለቸርነትህ

23 5 42 242 23542 242

23154 44513 313

15121 4322 242

52222 23423 313 44551 5222 242

15131 4323 313 15131 4342 242

የእኛ ጌታ የኛ መድኅን
በቸርነትህ ታደገን
እኛ እንደሆነ ኃይል የለን
ጠዋት ለምልማ ማታ ጠፋች
የሰው ህሊና እያባባች
ዓለም ምኗ ነው የጣፈጠን
እያሳሳቀ የወሰደን
ዛሬ አለች ሲሏት ትጠፋለች
ከነተንኮሏ ዓለም ሟች ነች
እሾህ በቅሎባት እሾህ ሆና
በመተላለፍ ሰው ሊያልቅ ነው
ከእኛ ጋር ያለው ኃያል ነው
በሥጋዊ ዓይን ባናየው
የፆሩ ብዛት መች አድኗት
ዓለምን ትምክህት ተዋህዷት
እንደ ሰው ጥበብ ጥበበኛ
እንደሰው ጉበረት ወደረኛ
እንደ ዓለም ጉልበት ጉልበተኛ
በአምላክ ፊት ሲታይ ህመምተኛ

- -

ኑ ተመልከቱልኝ (ይልማ ኃይሉ በገና)

ቅኝት - ስለቸርነትህ

ኑ ተመልከቱልኝ የአምላክን ቸርነት
አንደበት የለኝም ስራውን ለማውራት
ሰላምና ፍቅር በልቤ ተሞልቷል
በምን ቋንቋ ላውራው ቃላቶች ያጥሩኛል /2/
ሰማይ ጉም ቢመስል ቀለያት ቢናጉ
የጥፋት አጋንንት እጅጉን ቢተጉ
እኔን የሚጠብቅ ኃይሉን አይሰውርም
እረኛዬ ከእኔ ዘወትር አይርቅም /2/
ፍርሃት ከኔ ራቅ ጨለማም ተወገድ
በጌታዬ ትምክህት እንደልቤ ልሂድ
የሞት አበጋዞች ተስፋችሁ ጨልሟል
እግዚአብሔር ሊያድነኝ ከአጠገቤ ቆሟል
ቅዱሳን በሙሉ ለእኔ ዙብ ቆመዋል
ወደእነርሱ ጉበረት ሊስቡኝ ጓጉተዋል
ዘወትር በመአልት ድንግል ትመጣለች
በብርሃን እጆቿ ትባርከኛለች

- -

ዳግም ስትመጣ (ዘርፉ ደምሴ በገና)

ቅኝት - ስለቸርነትህ

ዳግም ስትመጣ በዓለም ፍፃሜ
እንዴት አይህ ይሆን በየት በኩል ቆሜ /2/
ለነፍሴ ሳልሰንቅ አንዳች በጐ ነገር
እንዴት እወርሳለሁ የመንግሥቱን ሀገር/2/
እግሮቼ ካልቆሙ ከቅስት ተራራ
በረከት ካልያዙ የጽዮንን ሥፍራ
በቁጣው እሳት ፊት እንዴት ይድናሉ
በመቅረዙ በርተው በከብር ካልዋሉ/2/
ዓይኖችህ በፍቅር እንዲያዩኝ በምህረት
ልተከል በደጅህ ከድህነት ሰገነት /2/
ሳልል በላዬ ላይ ተራራን ተከዳን
በንስህ ልቁም በምጽአትህ ቀን/2/
አለቆች ሲሻሩ ከዙፋን ሲወድቁ
ጠቢባን ሲሰንፉ በኃይልህ ሲወድቁ
አቤቱ ባርያህን አትተው ብያለሁ
ትንሣኤህን ለከብር ለመንግሥትህ በለው/2/
ላንተ የማቀርበው አጣሁ በጐ ነገር
ከፍቶ የሚያስገባ የመንግሥትህን በር/2/
አለው ባዶ እጇን መብራት ሳላበራ
ኃጢኣቴ በዝቶ መቅረዜ ተሰብራ/2/
ኃያላን ሲፈቱ ሲሰበር ቀስታቸው
ትምክህታቸው ሲቀር ሲጠፋ ስማቸው
ታናሹን ባርያህን ጻፈኝ በመጽሐፍህ
ቅዱሳን ካሉበት የድህነት መዝገብህ/2/
ጣዖታት ሲናዱ ወድቀው ሲሰበሩ
ገፃቸው ሲጠቁር ወድቀው የነበሩ
ሀፍረት ሲከናነብ አንተን የበደለ
ዐየን በምህረት ጻድቅ እንደ በቀለ/2/

- -

ሙሽራው ሙሽራ (የሠርግ)

ቅኝት- ስለቸርነትህ (አንቺ ሆዬ ለኔ)

ሙሽራው ሙሽራ /2/
እጹብ ነው ደስታው
ሙሽራው ሙሽራ
እንደ አደይ አበባ ሙሽሮች ፈክታችሁ
በለምለም መስክ ያለ ፍሬ መሰላችሁ
ልክ እንደ ጨረቃ እንደ ሰማይ ፀሀይ
መልካሙ ሥራችሁ በራ በአደባባይ
አዝ.....
ካባዋን ደርባ በጥበቧ ላይ
የተዋህዶ ልጅ ደምቃ ስትታይ
በቤተክርስቲያን ሥርዓት በማደጓ
ይሽው መሠከረ የሙሽሪት ወጓ
አዝ.....
መልካም ሥነ ምግባር ፍቅር የከበበህ
የእሙበርሃን ልጅ አቤት ማማርህ
ከመቼውም ይበልጥ ዛሬ ተውበሃል
የአማኑኤል ግርማ ዙሪያህን ከቦሀል
የእመቤቴ ፀዳል በእውነት አምሮብሀል
አዝ.....
መልካም ሥነ ምግባር ፍቅር የከበበሽ
የእሙበርሃን ልጅ አቤት ማማርሽ
ከመቼውም በላይ ዛሬ ተውበሻል
የአማኑኤል ግርማ ዙሪያሽን ከቦሻል
የእመቤቴ ፀዳል በእውነት አምሮብሻል

- -

የሀብ ከዮም (የሠርግ) (ይልማ ኃይሉ በገና)

ቅኝት -

የሀብ ከዮም የሀብከ መድኃኔዓለም /2/
እድሜ ማቱሳላ ወአብርሃም /2/
ይስጣችሁ ዛሬ ይስጣችሁ መድኃኔዓለም/2/
እንደ ማቱሳላ እንደ አብርሃም /2/
አዝ.....
በቅዱስ ጋብቻ ሙሽሮች የተወሰናችሁ /2/
ክርስቶስ ተገኝቷል በመሀከላችሁ /2/
የድንጋዮቹን ጋን ወይኑን ወይኑን ሊመላበት/2/
ከድንግል ማርያም ጋር ተገኝቷል ሠርግ ቤት/2/

የእኛ ጌታ (ይልማ ኃ
ቅኝት - ስለቸርነትህ
23 5 42 242 23542 242
23154 44513 313
15121 4322 242
52222 23423 313 4455
15131 4323 313 15131
የእኛ ጌታ የኛ መድኅን

አዝ.....
ደስታውን አይቶ አምላክ ፍፁም ተደስቷል/2/
ሊባርካችሁም እጆቹን ዘርግቷል /2/
በህይወታችሁም ፍቅር ፍቅር ቅመም ሆኖ/2/
ትህትናን ይስጣችሁ እግዚአብሔር በቶሎ/2/
አዝ.....
ሠርጋችሁ እንዲሆን ደስታ ፍቅር የሞላበት
በህይወታችሁ ውስጥ ክርስቶስ ይግባበት
በህይወታችሁ ውስጥ አምላክ ይኑርበት
አዝ.....
የበረከት ፍሬ በጸጋው እንዲበዛላችሁ /2/
ዛሬ ተደሰቱ ድንግልን ይዛችሁ /2/
እራስን በመግዛት እውቀት እውቀት ለሞላችሁ
ዛሬ ተደሰቱ አምላክን ይዛችሁ /2/
አዝ.....
በሥጋ ወደሙ እግዚአብሔር ስለመረጣችሁ
የመንፈስ ቅዱስም ህፃናቶች ናችሁ /2/

- -

አሥር አውታር ባለው በበገና (ሶስና በገና)

ቅኝት -

አስር አውታር ባለው በበገና
ስለ ቅዱስ ስምህ ልቀኝና
ስምህን ላወድስ በዝማሬ
እኔም ከአባቶቼ ተምሬ
ዳዊት ስለ ከብርህ እጅግ ቀንቶ
በሰው ፊት መክበርን ሁሉን ትቶ
ሲዘምር የዋለው ስምክን ጠርቶ
መች ሆነና እርሱ ሹመት ሸቶ
በእስር ቤት ሳሉ እነ ጳውሎስ
የእጃቸው ሠንሰለት እስኪበጠስ
የወህኒውን ደጆች ያስከፈቱት
ባንተ ምስጋና ነው የበረቱት
ባንደበቴ ልጩህ ላመስግንህ
በቀንና በሌት ልቀኝልህ
ልዋረድ ከፊትህ ሰው ይናቀኝ
ምስጋናዬን አንተ ተቀበለኝ
በምስጋና ልምሰል አባቶቼን
ለዘወትር ስምህን በማመስገን
ኃጢአቴን አታስብ መበደሌን
ምስጋናዬን ስማ ዝማሬዬን
ፍቅርህ የጎደለኝ ብሆንብህ
ለምስጋና አቆመኝ ቸርነትህ
አወድስሀለሁ በበገና
ምስጋናህ ይብዛልኝ እንደገና

- -

አድነኝ ከሞት (ሶስና በገና)

ቅኝት -

አንተ ሠርተኽ ነበር ትልቅ አዳራሽ አድነኝ ከሞት
አውሬ አስገብቼበት አረጉት ብላሽ " "
አንተማ ሰጠኽኝ የተከበረ ዕንቁ " "
እኔ ግን ተሳነኝ ዋጋውን ማወቁ " "
አንተ ለኔ ታማኝ እኔ አደራ በላ " "
በቤትኽ አስገባኹ ጅብ ቀበሮ ተኩላ " "
አንተህ ሰርተህ ነበር መልካም አገልግል " "
እኔ ግን ላጥሞኝ ልክስክስ እድል " "
ማፈሻ አደረኩት ያመድ የከሰል " "
በፈቃደ ሥጋ ሰይጣን ሲያገብረኝ " "
አንተ አስረህ ያዘኝ ለጠላት አትስጠኝ " "
አሁን ግን ፈለግኹ ጭልጥ ሳትል ነፍሴ " "
ከጅብ አፍ አስጥለኝ የአብርሀሙ ሥላሴ " "
ለሰው የሚሻውን መሻቱን አውቀኽ " "
ኀጢቃድኽ ኹሉን ትሰጠዋለኽ " "
ጽድቅ የሚያበቃ ምግባር ባይኖረኝም " "
ምህረትህ አንተ ከሞት አድነኝ " "
ካሞኽ በረቱ ብርቱዎች ደክመው " "
ንተን አምነው ዳኑ አንተን ተማጽነው " "
መሰግኑሀል መናንኖን ኹሉ " "
ድንጋይ ተንተርሰው ቅጠል እየበሉ " "
በፍጹም ልብ ሆነው ጌታ ላመኑህ " "
አምባና መጠጊያ ጋሻም አንተ ነህ " "
በምህረት አስበህ ችግረኛውን " "
ታብስለታለህ መሪር እንባውን " "
ሁሉን ስታሳልፍ በጌትነትህ " "
አንተ አታልፍም ሁሌም ሕያው ነህ " "
ባህር ውቅያኖስ ሳይሆኑህ ወሰን " "
ትገሰግሳለህ አንተ ዓለምን ሁሉ " "
ዓለምን ለመምሰል እኔ አልጥርም " "
በአንተ አምኛለሁ ከቶ አላፍርም " "
ለሰው ልጅ ሁሉ ሰጥተህ ሕይወትህን " "
በልተው እንዲድኑ ሥጋና ደምህን " "
ንስህ የገባ በደለኛውን ሰው " "
ከበደሉ አንስተህ ለጽድቅ አበቃኸው " "
እንደ ቸርነትህ ካልሆነ ጌታዬ " "
እኔ አልድንምና በዚህ በሥራዬ " "
እየኝ ተመልከተኝ በምህረት ዐይንህ " "
ምስጋና እንዳቀርብ ለቅዱሱ ስምህ " "
ስለ ቸርነትህ ጌታ መድኃኔዓለም " "
ምስጋና ይድረስህ ዛሬም ዘለዓለም " "
አድነኝ ከሞት

- -

ቸሩ መድኃኔዓለም (ሶስና በገና)

ቅኝት -

ቸሩ መድኃኔዓለም ቸሩ እግዚአብሔር
በምን ቃል አንደበት ሥራህ ይነገር
ከአርያም ከብርህ ከዙፋንህ ወርደኽ
ከእጅህ ሥጋ ጋር ከኛ ተዋህደህ
እጅግ ያሰደንቃል ያንተ ትህትና
ለአዳም ስትኽን ህያው ምግብ ጤና
ፈጣሪ ሰው ሲሆን ሰው ሲሆን ፈጣሪ
የአዳም ኃጢያት ዕዳ ሲሻር ሲሆን ቀሪ
ያንተ ስራ . . .
ሰይጣን በተንኮሉ አዳምን ቢጥለው
ከሰማያት ወርዶክርስቶስ አነሳው
ድሮም ከአርያም እዚኽ የመጣኽው
ለማዳን ነውና ከሰጣን ሰውረን
ድንግል ማርያም ጌጤ የአዳም ልጅ ሲሳይ
ማደሪያ ሆነች ለአምላክ አዶናይ
ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷም የነሳ
ወልድ ዋህድ ጌታ ሞቶ የተነሳ
ያንተ ስራ . . .

አንተ ይቅር በለን ስለ በደላችን
ሁሉ አልቆበናል አይሞላም ስራችን
ሁሉ ጎዶሎ ነወ አይሞላም ስራችን
ጥንት የሌለህ አንተ ህፃን ኾነህ አንተ
አለም ናቀህ ቆሞ ዳግም እየሳተ
ያስደንቃል እንጂ ክርስቶስ ሲወለድ
ሁሉን ቻይ ፈጣሪ ለሰው ልጅ ሲዋረድ

ያንተ ስራ . . .
አልቀበል ካሉት አይሁድ በጥላቻ
መጣባቸው ስደት ሆኖ መተረቻ
በቃና ገሊላ ውሃ ወይን ሲኾን
አይሁድ ሳይረዱ የነላ ምስጢሩን
ታውረው ደርቁረው ተመቅኝተው ትላንት
ዛሬም በጨለማ አሉ በሞት ሥርዓት

ያንተ ስራ . . .
ዲያብሎስ ተራቆ በተንኮል ብዛት
ኣዳምና ሔዋን ቢፈርሙለት
አምስት ሺ ዘመን አምስት መቶ ዓመት
በሲኦል ከረሙ ውሉ ጠፍቶ ከቤት
ወልደ አብ ፈጣሪ ከላይ ተመልከቶት
በዮርዳኖስ ሻረው ዶሴውን አግኝቶት
ከሲኦሉ ዶሴ እጅግ ርቆ በፊት
አርብ ለት ተገኘ በመስቀሉ መብራት

ያንተ ስራ . . .
ሰይጣን አፍሮ ጮኸ ምስጢር ቢወጣበት
በዮርዳኖስ ሲኦል ያኖረው ታይቶበት
በቀራንዮ ላይ በመስቀል ኮረብታ
አምላክ ተሰቅሎ ዲያብሎስ ሲመታ
እኔ ዳንኩኝ ይኸው የታለል የሞት ካርታ
ተወግሯል በመስቀል ክብሩን ያጣ ሽፍታ
እንዲህ ከመታኸው በመስቀል በትር
እንጦሮጦስ ጣለው ከላይ አታስቀረው
እሱ ከታሰረ በእሳት ሰንሰለት
የአዳም ልጅ ይድናል ከዳግመኛ ሞት

ያንተ ስራ . . .
በዲያብሎስ ተንኮል ዓለም እየሳተ
መሬት ሲኦል ኾነች ሰው እያሟረተ
በኖህ ዘመን ጊዜ እንደሆነው ሁላ
ዓለም ተበሳሽ እየበዛ ጥሉ
አውሬ ሰለጠነ ሰው እየመሰለ
ሁሉ አልቆበናል የሰው ሰው የታለ
እግዚአብሔር ፈጣሪ ቸር አባት ነህና
ሰውን ልብ ስጠው ልባም ጠፍቷልና
ስለ እመአምላክ ብለህ ስለ ድንግል ማርያም
ይቅር በለን አንተ እሳት ሞት አይበጅም
ያንተ ስራ . . . . . /፪/

- -

ሰማይና ምድርን (የትምወርቅ በገና)

ቅኝት -

ሰማይና ምድርን ያቀናህ
የሰውን ልጅ ፈጥረህ አምሳያህን
የህጥያት ቀንበር ለመስበር
ጉበተህ ከፍጡራኑ መንደር 2x
ከድንግል ማርያም ተወልደህ
ከሰማያት ሰማያት ወርደህ
አምላካችን ወደህ ሰው ሆነህ
ህዝብህን በደምህ የዋጀህ 2x
ሀሙስ በሌሊቱ ጸለይክና
አርአያ ምሳሌ ሆንክንና
ጭፍሮች ተሰብስበው ጅራፍ ይዘው
ሊይዙህ ቀረቡ ሰይፍን መዘው 2x
ጅራፍና በትር አዘጋጁ
የሞትህን አዋጅ ሊያሳውጁ
ስቀለው እያሉ ተነሳሱ
በአንተ ሞት እነሱ ተፈወሱ 2x
በቀራንዮ ራስ አደባባይ
ተሰቅለህ ጌታዬ በመስቀል ላይ
ውሃ ስትጠማ ሀሞት ጠጣህ
ሰውን ከመከራ እያወጣህ 2x
መቃብሩን አልፈህ ከፈኑን
ሳትከብ ሳትነክር_____
የድንግል ማርያም ልጅ ተነሳህ
በሞትህ ሰይጣንን ድል ነሳህ 2x

- -

በገናዬን ላንሳ (የትምወርቅ በገና)

ቅኝት -

በገናዬን ላንሳ ሁሌም ልቀኝልህ
ንጉሴና አምላኬ ባሪያህ ላገልግልህ
ከእረኝነት ግብር ጠርተህ አነገስከኝ
ከበጐች ጥበቃ በህዝብህ ላይ ሾምከኝ
የኤልያብ ክብር በፊትህ ምንድነው
ከፊት አስቀደምከኝ ታላቆቼ ቀርተው
ሸሽገኝ አባቴ ሆኜ ብላቴና
አንተ ግን መረጥከኝ ሳትንቅ ለንግስና
ጠጠሬን ሳነሳ ቀኝህ እረዳችኝ
ጋሻ ጦሩ ከድቶት ጠላት ወደቀልኝ
ጐልያድም የለም ከነኃይሉ ተዋርዷል
ፍልስጤም በእስራኤል ተሸንፎ ሸሽቷል
ከኋላዬ ቀረ ሳኦል ከነ ጦሩ
ገዳዬን ጣልክልኝ ከነ ክፉ ምክሩ
ቀብተህ አቆመከኝ በርሱው አደባባይ
ከእጁ ቀስት ድኜ ወጣሁ ሰገነት ላይ
አቤሴሎም ልጄ ጨክኗል በአባቱ
ከላይ ባልተሰጠው መንግስቴን መሻቱ
በዮርዳኖስ አሸዋ በልቤ ተኝቼ
ታሪክ እስኪለወጥ አነባሁ አብዝቼ
እንደቸርነትህ መጠን ምረኸኝ
ስንቱን በደል ሸረህ በፍቅር አደስከኝ
በማለዳ በሰርክ ይብዛ ዝማሬዬ
ሌሊት መኝታዬን ልጠብ በእንባዬ

- -

ዐርብ የታረደውን (ዘርፉ ደምሴ በገና)

ቅኝት -

ዐርብ የታረደውን ምነው ባገኘኹት
ሥጋውን በልቼ ደሙን በጠጣኹት
አይቀርም ሞቱ
ሥጋውን በልቼ ደሙን በጠጣኹት
ሥጋዬና ነፍሴ ትግል ገጥመውብኝ
አዬ ጉድ ወየው ጉድ ወየው መከራዬ
ሞት አንተ ነህ አሉኝ መቼም ገላጋዬ
አይቀርም ሞቱ
ሞት አንተ ነህ አሉኝ መቼም ገላጋዬ
ሚ መጠን ሳይባል የመጣው ቀድሜ
ሥጋህና ደምህ አመለጠኝ ቆሜ
አይቀርም ሞቱ

ሥጋህና ደምህ አመለጠኝ ቆሜ
ሥጋዬን የበላ ደሜንም የጠጣ ከእኔ ጋር ይኖራል ብለህ ተናግረህ
ተኮነን ብትለኝ ተኮነን ብትለኝ
እንወርዳለን አብረን እኔ ምን ቸገረኝ
የከብር መብራቱ እሳቱ ሲቃጠል
አዬ ጉድ ወይ ሰይጣን አጠፉት በቅጠል
ከዛ ከሞኝ ሰው ከዛ ከቂሉ ሰው ከዛ ከየዋህ ሰው ተወልጄ ካዳም
አንዱ ትቶት ሲኼድ ስንቅ አያሳነዳም
አይቀርም ሞቱ
አንዱ ትቶት ሲኼድ ስንቅ አያሳነዳም
እስቲ ልናገረው የርሷን ልዕልና
የኪሩቤል መቅደስ የሱራፌል ፅና /2/
ዘካርያስ ያያት የተቋም ላይ ፋና
የሰሎሞን ሸቶ የዳዊት በገና /2/
የርሁባን ምግብ የድውያን ጤና
የሙሴ ሐመልማል ያያት ደብረሲና /2/
የዳንኤል ጉድጓድ የእንባቆብ ምድበና
የኢሳይያስ ጽንስ የገብርኤል ዜና
አንተ ነህ ይሉኛል የዓለም ሁሉ ጌታ
ሰማይና ምድርን ያቆምክ ያለዋልታ
አልታገልህም ግራ ካገባኸኝ
ደግሞም ማፈር አለ ከሰው ፊት ጥለኸኝ
አይቀርም ሞቱ
ደግሞም ማፈር አለ ከሰው ፊት ጥለኸኝ
ዲያቢሎስ ከሚስቱ ሳጥናኤል ከሚስቱ ተጣልቶ ሲፋታ
ለሷ የደረሳት ቀሚስና ኩታ
ለሷ የደረሳት ቀሚስና ኩታ
ምን ያሳዝንህል ብዙ ልብ አልባ ላንተም ይደርስህል
ምድርን ጠላ መጥመቅ ማን አስተማረው
እየጠራ አጠጣው ይኸን ኹሉ ሰው
አይቀርም ሞቱ
እየጠራ አጠጣው ይኸን ኹሉ ሰው
ሥራ ፈቶ ዋለ ትላንት ሸማኔው
ያ ቀለምሽ ነው ወይ የተበላሸው

- -

ድጓውን ከተቱት (ዘርፉ ደምሴ በገና)

ቅኝት -
አዲስ ቤት ስትሠሩ ባለ ጉልላት
ማዘን ጨምሩበት እንዲሰነብት /2/
ተካፈሉት አሉኝ እቴ የኛን እጣ /2/
የትም ሀገር ብንኼድ በይ መሬት አናጣም/2/
ቤቴን መንገድ ዳር ሠርቼው ቅር አለኝ /2/
አላፊው አግዳሚው ያፈር ሰው መሰለኝ /2/
መካሪዬ በዛ ቤት ሥራ ሚለው /2/
ምን ያታከተኛል አሁን ላፈርሰው /2/
ጣፍጦኝ እንዳልበላ ይምረረው ብለህ /2/
ምነው በሥጋ ሞት ጨምረህ ሰጠኸኝ /2/
ገበያ ወጥቼ ብመለከተው /2/
በጣም በዝቶ አየሁት ሥጋ ፈላጊው /2/
ዳዊቴን ወሰደው የማላውቀው ልጅ /2/
የማይቀር ገንዘቤን ደግሞት ይስጠኝ እንጂ/2/
ለምን ይዘሸዋል ዳዊቱን ለምስል /2/
ከስብሃት ለአብ ወዲ ይደገም ይመስል /2/
ድጓውን ከተቱት አስተጋቡት በጣም /2/
በቃ ተከተተ ከእንግዲህ አይወጣም /2/
ይገኝ መስሎኝ ነበር የመጣን ከተማ /2/
እንግባ አገራችን እውነት ከጠፋማ /2/
ድጓ ጾመ ድጓ ተሰቅሎ ከቤቴ
እኔስ የሚገርመኝ ሳልማር መቅረቴ
ድጓ ጾመ ድጓ ያልተማረ የለ
ዋ ነው የመጨረሻው የዚህ ሁሉ ቀለም
የራበው ካልበላ እንደምን ይሆናል
ከዚያ ወዲያ ጦም ነው ማማት ይዝምራል/2/
ዐርብ ረቡን በላሁ ሁዳዴንም በላሁ እንጀራ ባዋዜ /2/
እንዲህ ቶሎ ብሎ ለሚደርሰው ጊዜ /2/

- -

እንመን በስሙ (ዘርፉ ደምሴ በገና)

ቅኝት -
እንመን በስሙ በፈጠረን ጌታ
እርሱ ነው በሞቱ አዳምን የፈታ /2/
ከመቃብር በላይ ስማችንን ጽፎ
ጠራን በትንሣኤ ሞትን አሸንፎ /2/
ሰዎች ተሰብሰቡ ከፍሪዳው መንደር
የመከሩ ዘመን ደርሶ ሳንሰበር /2/
አጫጆች ቆመዋል ከደጃችን በራፍ
ይነጠፍ ፊታችን የጽድቃችን ምንጣፍ/2/
ሃይማኖት አቅንተን ምግባር እየሠራን
ቤተል እንታደም አምልጠን ከካራን /2/
የደም ጣቶች ካሉን ይንጹ በንስሀ
እርሱ ይሰጠናል የሂሶጵን ውሃ /2/
የእግዚአብሔር ልጆች ነን የተሠራን በደም
ወድቋል ከላያችን የታቀፍነው መርገም/2/
ተሠርተናልና በእጅ ዳግም እንደገና
ለሕይወት ተከለን ሞትን ነቀለና /2/
የሞትን አቀበት አፍርሶ በደሙ
ሁላችን ከበርን በገናናው ስሙ /2/
የመቃብር ስሞች ፈርሰው ተዘነጉ
በመስቀል ተሰቅሎ ታርዷልና በጉ /2/
መድኃኒት ነውና ኢየሱስ ክርስቶስ
ሸሽ ከላያችን ያስጨነቀን መንፈስ /2/
ሞት የተጻፈበት መዝገቡ ተከደነ
የሌጊዮን ጭፍራ ፊታችን ተነነ /2/
በብርሃን መስቀል ጨለማን ገፈፈው
መቃችን ወለቀ ፊት ለፊት አየነው /2/
የፍቅር አይኖቹን ተከሏል በላያችን
ፍጹም የወደደን ያዳነን ጌታችን /2/
የሸጥነውን ሀገር በደሙ ገዛልን
እዳችንን ከፍሎ ሕይወት ታወጀልን
ኃይልን አስታጠቀን ከበበን ሞገሱ
ሸፈንን በደሙ ባማረ ቀሚሱ /2/

- -

ተወለደልን (ዘርፉ ደምሴ በገና)

ቅኝት -
እራቆቱን በዚያ በከረምት በብርድ
ወድቆ አደረ እኛን ለማዳን ቢወድ
በዚያ በከረምት በብርድ እኛን ለማዳን ቢወድ
እረኞቹም አቀረቡለት ማፈድ
አይተው ነበር መላክ ከሰማይ ሲወርድ
አቀረቡለት ማዕድ መላክ ከሰማይ ሲወርድ
ሰባ ሰገልም መጥተው በምሥራቅ
በአውድ ሰገዱለት እንደ አገራቸው ልማድ
መጥተው በምስራቅ በአውድ እንደ አገራቸው ልማድ
ሄሮድስም ሰማ ተንቀጠቀጠ
አይጉድ ወሬው በዛ በኢየሩሳሌም ተስፋፋ
ወሬው በዛ ተስፋፋ ተንቀጠቀጡ አይጉድ

ፈለገውና ሕፃኑን ሊገል
ሄሮድስ ሕፃናት መግደል ዝምረ ማረድ
ቅድስት ማርያም ልጇን ጠቅልላ
በዳባ የሴፍ ጋር ሸሸች ሆና ስንቅ አልባ /2/
በዚያ በረሃ በንዳድና በወባ
ስትሸሽ ተያዘች በወንበዴና በሌባ /2/
እያለቀሰች ልቧ ቢዋልል ቢባባ
ወንበዴው ምሯት ወደዱሩ ገባ
ልቧ ቢዋልል ቢባባ ወንበዴው ምሯት ዱር ገባ
ውሃ ቢጠማት ጠጥታ አደረች እንባዋን
የሴፍ አይቶ ጥሟን ወድረቁን ተርባ
ፍሬ ለቃቅሞ አምጥቶ ሰጣት ዘንባባ /2/
በመከራ ጭንቅ ልትሞት ተርባ
ዝላ ደረሰች ከቁስቋም አንባ
በመከራ ጭንቅ ተርባ ዝላ ደረሰች ቁስቋም
ዘንግተዋል የሰሎሞን ዘንግ እሴይ
ከንፈሮቿም መከኖ ያፈራው እንኩይ
ፀጉሯም ደግሞ የሊባኖስ ዱር መሳይ
ጠቆረች በዚያ በሀሩርና በፀሓይ
ጠቆረች በዚያ ፀሓይ ጠቆረች በዚያ ፀሓይ

- -

ማዘን ጨምሩበት (ዘርፉ ደምሴ በገና)

ቅኝት -

አዲስ ቤት ስትሠሩ ባለ ጉልላት
ማዘን ጨምሩበት እንዲሰነብት
ተካፈሉት አሉኝ እቴ የኛን እጣ
የትም ሀገር ብንኼድ በይ መሬት አናጣ
ቤቴን እመንገድ ዳር ሠርቼው ቅር አለኝ
አላፊው አግዳሚው ያፈር ሰው መሰለኝ /2/
መካሪዬ በዛ ቤት ሥራ የሚለው /2/
ምን ያታክተኛል አሁን ላፈርሰው /2/
ጣፍጦኝ እንዳልበላ ይምረረው ብለህ /2/
ምነው በሥጋ ሞት ጨምረህ ሰጠኸኝ /2/
ገበያ ወጥቼ ብመለከተው /2/
በጣም በዝቶ አየሁት ሥጋ ፈላጊው /2/
ዳዊቴን ወሰደው የማላውቀው ልጅ /2/
የማይቀር ገንዘቤን ደግሞት ይስጠኝ እንጂ/2/
ለምን ይዘሸዋል ዳዊቱን ለምስል
ከስብሃት ለአብ ወዲ ይደገም ይመስል
ድጓውን ክተቱት አስተጋቡት በጣም
በቃ ተከተተ ከእንግዲህ አይወጣም
ይገኝ መስሎኝ ነበር የመጣን ከተማ
እንግባ አገራችን እውነት ከጠፋማ
ድጓ ጾመ ድጓ ተሰቅሎ ከቤቴ
እኔስ የሚገርመኝ ሳልማር መቅረቴ
ሸክላ በሩቅ ሲያዩት ብረት ይስላል
ለመረመረው ሰው ገል አፈር ኖሯል
ሰው አይቸገርም ሌሊት ዝናብ ቢሆን
ጉዳት የሚበዛው ቀን የጣለ እንደሆነ
በልቼ ጠጥቼ ገባሁኝ

- -

የኢየሩሳሌም ቆነጃጅት (ዘርፉ ደምሴ በገና)

ቅኝት -

የኢየሩሳሌም ቆነጃጅት አሉለት ዋይ ዋይ
የኃያላን ጌታ በግፍ ሲሰቃይ
እንደ ውሃ ሲፈስ በፊቱ ላይ ደሙ
አፋቸውን ያዙ እየተደመሙ
በአመፀኞች እጅ መውደቅ መገፋቱ
ሊያነሳን ሽቶ ነው መታመም መሞቱ
የግፈኛን ምራቅ ገጹ ተቀበለ
አላበቃም በነዚያ በእንጨት ተሰቀለ
የብርሃን ፊቱ በደም ተሸፈኖ
ሊያየው አልደፈረም ፍጥረት ዐይኑን ከድኖ
ድንቅ ነው ውለታው የበዛ ምህረቱ
ለገደሉት ሕይወት አንገቱን መስጠቱ
የአይኑድ ንጉሥ ብለው ቢዘብቱበት
ሊሸከም ወደደ የመውጊያውን ሸክም
አቁሳዮችን ቢያድን እርሱ እየቆሰለ
ያቀልጣል መውደዱ ፍቅሩን ላስተዋለ
አፏን ከፈተችው የኢየሩሳሌም ምድር
የፈጠራት ጌታ ከመቃብር ሲያድር
ሐውልቶች ተናዱ ሙታንም ተነሡ
ምስክር ሊሆኑ ለዚያ ለንጉሡ
የመከራው መንገድ በደም ተጠረገ
እርሱ ዝቅ እያለ ከፍ አደረገ
በችንካሩ ጥልቀት አይለካም ፍቅሩ
አርምሞ ይኖላል አለመናገሩ
ከሰማያት ወርዶ ዝቅ ዝቅ እያለ
ከከብቶች ማደሪያ ግርግሙ ላይ ዋለ
ከሐዋርያት ሀገር ቁጭ አለ ንጉሡ
እግራቸውን አጥቦ ጠረገ በልብሱ

- -

ኣሓዱ ብሎ ቅዱስ (ዘርፉ ደምሴ በገና)

ቅኝት -

እዛ ላይ ያለች ሸክላ ሰሪ
ድሃ ነች አሉ ጦም አዳሪ
ማን አስተማራት ጥበቡን
ገላ አፈር መሆኑን
ከወጥ ቤት ገባሁ ድንገት
ቋንጣ ጠብሼ ለሙበላት
ወድቄ ነበር ከሳት ላይ
ሥጋ ሥጋዬን ሳይ
ከዚያ ታች ያለች ከቶ ምን
ከቶ ምን ቀመሽ አልሻት ወይ
ኋላ ፀፀቱ ባንቺ ይሆናል
ተይ ሥጋ ብላሽ ይሆናል
የልጅ አገረድ አውታታ
አውራ መንገድ ላይ ተኝታ
ተነሽ ቢሏት ምነው
ይህ ሁሉ ዓለም አለም ዓፈር ነው
ትንኝ ቤት ሠራሁ እንዳቅመኛ
ኹለት ሦስት የሚያስተኛ
አላስገባ አለች እሷው ጠባ
ሰው በሰው ላይ እየገባ
የኢየሩሳሌም መንገድ
ቅርብ ነው አሉኝ የረፋድ
ለቀደመኝ ነው የማዝነው
ወይኔ የማልቀረው
የኢየሩሳሌም ሴት
ጐልጐታ ላይ ሠርታ ቤት
እግዚአብሔር ያጥናሽ አልናት ወይ
ወልዳ አልሞታትም ወይ
ከሰማየ ሰማይ ወርደህ
ከድንግል ማርያም ተወልደህ
ትጨክናለህ ምነው
አምላክ በናትህ ሰው

ኣሓዱ ብሎ ቅዱስ
እንዴት ይጠፋል ለቄስ
በስመ አብን ሳያውቅ እንዴት ኖረ
እንደኔ ያልተማረ
እኔ ተሠራው ጠጉሬን
አላርፍ ብዬ ነውሬን
ሌሎች ሲላጩ እያየ ዐይኔ
ለምን ተሠራው እኔ
ከብት ጠፍቶብኝ በሌሊት
ስፈልግ አደርኩ ስዋትት
እነግርሃለሁ ተጣርቼ
ይህን ቀን ወጥቼ አይቼ

- -

<u>በአዳም በደል (ዘርፉ ደምሴ በገና)</u>

<u>ቅኝት -</u>
እንዲህ ሲለው ተስፋውን ብቻ ሰማ እንጂ
አላገኘም ፈጥኖ የሚያድነው ወዳጅ
በአዳም ፍዳ የአዳም ልጅ ሁሉ ተጋዘ
እያንዳንዱ በቁራኝነት ተያዘ
ለሞትም በነፋስ በሥጋ ታዘዘ
ወደ ሲዖል ወደ ቃብር ተጓዘ
በአዳም በደል ባላጋራችን ሰይጣን
በሰው ላይ ተሰጠው እና ስልጣን
ኃጢአትን አንድ እንኳን ሳይቀር በሙሉ
በየዕለቱ ያስተምር ዝመረ ለሁሉ
ለቃየል ነፍስ መግደል ቢያሳየው
የናቱን ልጅ አቤል ወንድሙን ተጣላው
በድንጋዩ ራሱን ብሎ ገደለው
እንዲስፋፋ የመገዳደል ትምህርት
ለዛዛኤል ለተወለደው ለሴት
አስተማረው የጦር መሳሪያ መሥራት
በዓለም ላይ በዝቶ እንደሠራ
ዝሙት በወነዶች ላይ እንዲቀሰቀስ ፍትወት
ዐይንን መኳል መነቀስንም አንገት
በእንሾሽላ የእጅ የግር ጣት ማቅላት
አስተማረ እንዲያለ ተንኮል ለሴት
10ኛው ኖኅ የሚባለው ፍጡር
እሱ ብቻ ከነልጆቹ ሲቀር
በየሥራው ሰው ሁሉ እሱን መሰለ
ተካከለ ዓለምም በአንድነት በደለ
እግዚአብሔርም ፍጥረት ሁሉ ፈተነ
አላገኘም በሕጉ በሥርዓቱ የሆነ
ተጠጠተ ሰው በመፍጠሩ አዘነ
ሰበሰበው ቁርጠኛ መዓት ፈረደ
እስከ 40 ቀን የጥፋት ውሃ ወረደ
አስቀርቶ 8 ራሱን የኖህ
ደመሰሰ በጥፋት ውሃ ሰውን
ኖኅም አይቶ የወረደውን መከራ
ውሃው ሲደርቅ ከመርከቧ መውጣት ቢፈራ
መሥዋት ሰዋ ጌታም ወደ ርሱ መጣና
በቀስት አምሳል 4 ሳብር ባላት ደመና
በፍል ውሃ አላጠፋም ሰውን
ብሎ ሰጠው እግዚአብሔር ለኖኅ ቃል ኪዳን
የሰው ልጅም እንዲህ ከሆነ በኋላ
እጅግ በዛ ብዛቱም ምድርን ሲመላ
ኹለተኛ ከግብር አባቱ ተማረ
እንደ ቀድሞ ኃጢአት ይሠራ ዝመረ
በባቢሎን የኃጢአት ግንብ . . .
ይልቁንም ኃጢአት ሁሉ ከባድ
ጣዖት መሥራት ከወርቅ ከብር ከግንድ
የዝመረ ሴሩህ የሚባል ትውልድ
ሰው ሁሉ ጣዖት ማምለክ ወደደ
በጣዖት ፍቅር ልቡ እንደ እሳት ነደደ
ጣዖት ማምለክ በዓለሙ ላይ ተስፋፋ
የእግዚአብሔር ስም ጨርሶ ከምድር ሲጠፋ
ያልተሞኘ በጣዖት ባሕር ያልዋኘ
በዚያ ወራት አብርሃም ብቻ ተገኘ
የሚጠራ የእግዚአብሔርን ስም በምድር
በዚያ ወራት አብርሃም ብቻ ነበር

- -

አየሁኝ በህልሜ (አቶ ታፈሰ በገና)

ቅኝት- ሰላምታ
3322-35 3322-31
544455 1111-33 4222-22
አየሁኝ በህልሜ /2/
ሞት የተባለውን <u>እዳ ተሸክሜ</u> /2/
ሰማሁኝ በዝና /2/
ቀጠሮ አከባሪ ነው ሞት አይረሳም እና ሞት አይቀርም እና
ሞት ቢቀር ይላሉ ሞት ቢቀር አልወድም
አፈሩም ድንጋዩም <u>ከሰው ፊት አይከብድም</u> /2/
አጠረ ቁመቴ ወዳጆቼን ባይ
እያደሩ ማነስ <u>ለካ እንዲህ ነው ወይ</u> /2/
አኔ አልገዛም ሱሪ ይቅርብኝ ለራሴ
አፈር ስለሆነ <u>የዘላለም ልብሴ</u> /2/
ቤት አልሠራም ይቅር ጣራና ግድግዳ
መቃብር ነውና <u>የኔ ሳሎን ጓዳ</u> /2/
እባክህ አምላኬ ስማ ጸሎቴን
በእንባ ዓለም እጇ <u>የምበላውን</u> /2/
እራሴን አንገቴ አልችለው ብለህ
ሁል ጊዜ ከሰው ፊት <u>ትጥለኛለህ</u> /2/
አይጣል አይጣል እያልን ስንለምነው
ሳናስበው ድንገት <u>ጣለብን ምነው</u> /2/
ግድግዳው ቢረዝም ምንባጡ ቢያምር
የምድር ቤት ነውና <u>መፍረሱም አይቀር</u>/2/
እንግዳው ሞት መጣ ኧረ ወየው ወየው
ለእግሩ ውሃ አሙቄ <u>በርገፍ ሳልቆየው</u>/2/
የሞትን ማረጉን ሁላችሁ እወቁ
ከእርሱ ቤት ይገኛል <u>ብሩም ሆነ ወርቁ</u>/2/
ይኸው የዘራልን በየቀኑ ሰው
አንድም አልበቀለ <u>የታል ቡቃያው</u>/2/
ከአቤል ጀምሮ ነበር የታመነ
አሁን ግን ስናየው <u>ሞት ቀጣፊ ሆነ</u> /2/
አይቼ መጣሁኝ ዛሬስ በእሁድ
ሰው እንደአዝመራ <u>በግፍ ሲታጨድ</u> /2/
በከንቱ ያሙታል እንዲሁ በሐሰት
ሰው በልቶ ጨረሰ <u>እያሉ መሬት</u> /2/
ከምድር እስከ ሰማይ ሰው ቢያስብ ሁልጊዜ
ከሰው አልተለየም <u>ሞትና ትካዜ</u> /2/
ደስታና ሐዘን ጐን ለጐን ሲኼዱ
ይጐራበቱናል <u>ከሁለቱ አንዱ</u> /2/
ሁሉ በሸተኛ ሁሉ ራሴን ባይ
በቤታችን ደህና <u>መጥፋቱ ነው ወይ</u> /2/
እሱን ሞት ሲጠራው በሩቁ ሰምቼ
እኔም ወይ አላልኩም <u>ለራሴ ፈርቼ</u> /2/
ሰው ሁሉ በርስቱ ይጨርሳል ሀብቱን
የኋላ የኋላ <u>ላያጣው መሬቱን</u> /2/
ቀኑን ባሸንፈው ሌት መቶ ታገለኝ
በቶሎ ሞት ናና <u>እባክህ ገላግለኝ</u> /2/

እድሜዬ ዘልዛላ ነው አያልቅ በቶሎ
ከቶ መሞት ላይቀር እንደው ውልውሎ /2/
ከፋኝ ሞቴን ስጠኝ ለማይቀረው እዳ
ደግሞ እንደ ሥጋዬ ነፍሴ እንዳትጐዳ /2/
ወለም ዘለም እያልኩ አለቀ እድሜዬ
ሞት መምጣቱ ላይቀር ወየው መከራዬ /2/

- -

አቦዬ ጻድቁ (አቶ ታፈሰ በገና)

ቅኝት- ሰላምታ
23-1111 11315
113 115 113 242
ገብረ መንፈስቅዱስ አቦዬ ጻድቁ
ኧረ እንዴት ነህ አባቴ ኧረ እንዴት ነህ መድኃኒቴ
ገደልና ግርማ የሚሰነጥቁ (ኧረ . . . .)
ገብረ መንፈስቅዱስ ተከለሃይማኖት (ኧረ . .)
ታላቅ ክብር ያገኙ በክርስቶስ ፊት (ኧረ . .)
ለጌታቸው ታዛዥ ለዓለም አማላጅ (ኧረ . .)
በፈጣሪያቸው ዘንድ በሥላሴ ደጅ (ኧረ . .)
ጻድቃን ሰማዕታት ደናግል በሙሉ (ኧረ .. .)
ሌት ተቀን ሳያርፉ ሰው ያማልዳሉ (ኧረ . .)
ድንጋይ ተንተርሰው ዳዋ እየላሱ (ኧረ....)
በጸሎት ተጠምደው ጤዛ እየላሱ (ኧረ . ... .)
ገብረ መንፈስ ቅዱስ አቡነ ተክልዬ (ኧረ. .)
በእናንተ ጋሻነት ልኑር ተክልዬ (ኧረ . ...)
የዘልዳው ኮከብ ቅዱስ ጊዮርጊስ (ኧረ . .. . .)
ተጨንቀው ሲጠሩህ ፈጥነህ የምትደርስ (ኧረ.)
አቡነ አረጋዊ ታላቁ አባት (ኧረ . . . . . .)
ጻጋ ክብር ያገኙ በሥላሴ ፊት (ኧረ .. . . .)
ሙሽራው ሰማዕት ገብረ ክርስቶስ (ኧረ .. . .)
መንኖ የኼደ ጽድቅ ለመልበስ (ኧረ .. . . .)
ደራጐንን በጦር ወግቶ የገደለ (ኧረ. . . .)
ፈረሰኛው ጊዮርጊስ የልዳው ኮከብ ነው(ኧረ.)
ገብረ መንፈስቅዱስ ታላቁ መናኝ (ኧረ . . .)
ከዚ ዓለም መቅሰፍት ፈጥነው ያድኑኝ (ኧረ.)
ፃድቃን ሰማዕታት አባቶች ሁላችሁ (ኧረ. .)
ኢትዮጵያን ጠብቋት አደራ ተግታችሁ(ኧረ..)

- -

እፎይ ታገስከኝ (ዘርፉ ደምሴ በገና)

ቅኝት -
ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር አምላክ
ሰማያት ወምድር የፈጠርክ አምላክ
አምላክ ሰማይ ወምድር
ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር አምላክ
የፈጠርክ አንተ ነህ የሰማይ መላእክት
አምላክ የሰማይ መላእክት
ሰባቱ ሰማያት የፈጠርክ አምላክ
ስብሐት ለክ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ
ቅዱስ አምላክ ሰማያት
መዓልቱን ሌሊቱን የፈጠርክ አምላክ
ስብሐት ለክ ቅዱስ እግዚአብሔር
አምላክ አንተ ቅዱስ
እፎ ሰቀሉሰ አንተን አንተን ዲበ ዕፅ
ኢየሱስ አምላክ ለአይኑድ ለአሞፅ
ሰቀሉክ አይኑድ አሞፅ
መድኃኒቱም አንቲ ለመበልት
መዝገበ ምህረት ሰአሊለነ ማርያም
እፎ አልበሱክ አንተን ከለሜዳ
ኢየሱስ አምላክ ለአሞፅ ለይኑዳ
አለበሱክ አሞፅ አይኑዳ
እፎ ተአገስክ አንተ መለኮት
ጊዜ ሰቀሉክ አይኑድ ካህናት
ተአገስክ አንተ መለኮት

- -

ሞት እንዴት ሰነበትክ (ዘርፉ ደምሴ በገና)

ቅኝት -

ባንዳንዱ ቀን መልእክት
ባንዳንዱ ቀን
መልእክት ሰው ያማርራል
የኔስ ወንድም ታዞ አባይ
ዳር ይኖራል
ቢታችው ቢሳወር ከእንግዳ ይተርፋል
ቢመሽ ከእኛ አደረ ነገም በእናንተ ያልፋል
ወይ አጭደን አልጣልነው ወይ ከብት አልበላው
ከቶ መቼ ይሆን ያሣር ማለቂያው
ዘመዶቼ ሁሉ አልቃችሁ አልቃችሁ
ወገኖቼ ሁሉ አልቃችሁ
ይኼ መግቢያ የለው ታሰኙኛላችኹ
የኔማ ዘመዶች ምን አጡ በሙሉ
መልካም በቅሎ ነበር ፈረስ ፈረስ አሉ
ምንም በቅሎ ቢያምር ኮርቻው ቢመች
መቀመጥ አይወዱም የኔ ዘመዶች
እጇ አመድ አፋሽ ነው ሞት ይመኛል አሉ
ጨርሼ ሰጥቼው ዘመዶቼን ሁሉ
ሞት እንዴት ሰነበትክ እንዴት ሰንብተሀል
እግዚአብሔር ይመስገን ወዴት ታውቀኛለህ
ለምን አላውቅህም አውቅሀለሁ እንጂ
የእህቴን የወንድሜን ስትዘጋ ደጅ አንተ
ሁል ጊዜ እንግዳ ሰው አጥፊ ነህ እንጂ
ሞት አገኘሁት እንደምን ዋልክ ብለው
አለኝ ደና ሰንብት
ሸኝቼው ተመለስኩ እኔም አላመንኩት

- -

ኪዳነ ምህረት (ዘርፉ ደምሴ በገና)

ቅኝት -
ንኢ ንኢ ንኢ ኪዳነ ምህረት
ሰዓሊ ለነ ማርያም መዝገበ ምህረት
ነአ ነአ ነአ ቅዱስ ሚካኤል
ታወጣለህ አሉኝ ከሞት ከሲኦል
ነአ ነአ ነአ ቅዱስ ገብርኤል
አይደለህም ወይ ዜናዊ ሐዲስ
ነአ ነአ ነአ ቅዱስ ጊዮርጊስ
ትደርሳለህ አሉኝ ፈጥነህ በፈረስ
አዳምን ከሲኦል እሌኒን ከባህር
ነነዌን የወጣህ አምላክ ከእሳት
እኔንም አድነኝ ከዲያቢሎስ ፊት
ሰዓሊ ለነ ማርያም ድረሽ ፅጌ ሃና
ዳዊት ወደሰኪ አንቺን በበገና
ሰዓሊ ለነ ቅድስት ነይ ከደማስቆ
እዝራ ወደሰኪ አንቺን በመሰንቆ
ስንጠራሽ ስሚን አፀደ ገነት
ትንቢቶሙ አንቺ ለአምላክ ነቢያት
ፈጥነሽ ድረሺልኝ ዘመና መሶብ
መድኃኒት ነሽና አንቺ ለያዕቆብ

ንኢ ንኢ ንኢ ኪዳነ ምህረት
ሰዓሊ ለነ ማርያም መዝገበ ምህረት
ነአ ነአ ነአ ቅዱስ ሚካኤል
ታወጣለህ አሉኝ ከሞት ከሲኦል
ነአ ነአ ነአ ቅዱስ ገብርኤል
አይደለህም ወይ ዜናዊ ሐዲስ
ነአ ነአ ነአ ቅዱስ ጊዮርጊስ
ትደርሳለህ አሉኝ ፈጥነህ በፈረስ

- -

የአዋጅ ነጋሪ ቃል

ቅኝት-

የአዋጅ ነጋሪ ቃል በበረሃ አየለ
የእግዚአብሔርን መንግስት አስተካክሉ እያለ
ምሥክርነቱን ዮሐንስ ሲያስረዳን
ልባችሁ ለጌታ መልካም መንገድ ይሁን
የደናግል መመኪያ የነቢያት ገዳም
አውደ ዓመቱን ባርኪልን ድንግል ማርያም

አዝ……
ተራራው ዝቅ ይበል ጠማማውም ይቅና
ካልተስተካከለ መንገድ የለምና
የእግዚአብሔርን መንገድ እንመስርት ሁላችን
ማለፊያ እንዲሆነን ለመጪው ሀብታችን

አዝ……
ከፋትና ተንኮል ከልባችን ይጥፋ
ጽድቅና ርኅራሄ በእኛ ላይ ይስፋፋ
ሥጋና ደምህን በክብር አግኝተናል
ሕይወት እንዲሆነን አምላክ ተማጽነናል

አዝ……
ሁለት ልብሶች ያሉት ከማብዛት ልብስን
ለሌለው ያድለው ሁለተኛውን
ከበደላችንም አንጻን አደራህን
በክፉ እንዳንጠፋ እኛ ልጆችህ

- -

የዓለም መድኃኒት (ሊቀ መዘምራን ኪነጥበብ)

ቅኝት -
የዓለም መድኃኒት የተወለደብሽ
አንቺ ቤተልሔም የተቀደስሽ ነሽ

የአማልክት አምላክ ንጉሠ ነገሥት
ኃያላን በሙሉ የሚሰግዱለት
በጨርቅ ተጠቅልሎ ተኛ በበረት

አዋቂዎች ሁሉ በቅን አሳባቸው
ወዳንቺ ተጓዙ ኮከብ ሲመራቸው /2/

ለተከታይ ትውልድ ምሳሌ ለመሆን
ሰግደው ገበሩለት ወርቅ እጣን ከርቤን/2/

የሚያድለው ጌታ እውቀትን ለሕፃናት
የሚመሰገን ነው በአፈ መላዕክት
ከእንስሳት ጋራ አደረ በበረት

ሥጋ ለብሶ ቢታይ ረቂቅ መለኮት
በአንድ ላይ ዘመሩ ሰውና መላዕክት/2

- -

እወርዳለሁ ቆላ (ሊቀ መዘምራን ኪነጥበብ)

ቅኝት -

እወርዳለሁ ቆላ እወጣለሁ ደጋ
የጭንቅ አማላጂን ድንግልን ፍለጋ

ድንግልን /3/ፍለጋ

አቀበት ቁልቁለቱን አይችልም ጉልበቴ/2/
ምርኩዜ ከሌለች ድንግል እመቤቴ

እመቤቴ /2/ ድንግል እመቤቴ

አንቺ የኖህ መርከብ የህይወት መገኛ/2/
መንግስተ ሰማያት መግቢያችን ነሽ ለኛ
መግቢያችን ነሽ /3/ ለኛ

አልጫውን ዓለም የሚያጣፍው/2/
ስምሽ ማርያም ነው ያለም ሁሉ ጨው
ማርያም ነው /2/ ያለም ሁሉ ጨው

እንደበደላችን እንዳይሆን ቅጣቱ /2/
አማልጂን ከልጅሽ ድንግል አዛኙቱ
አዛኙቱ /2/ ድንግል አዛኚቱ

የእናት አማላጅ የልጅ ተማላጅ /2/
ፊት አያስመልስም ይሁን ይሁን እንጅ
ይሁን /6/ አንጅ

- -

ይህ ቁርባን ከቡር ነው (ሊቀ መዘምራን ኪነጥበብ)

ቅኝት -

ይህ ቁርባን ከቡር ነው ፍፁም ሰማያዊ /2/
እንዳይመስለን ተራ አይደለም ምድራዊ /2/

አዝ….
ዋ ምን አፍ ነው የሚቀበለው
ዋ ምን ጥርስ ነው የሚያላምጠው
ዋ ምን ሆድ ነው የሚሸከመው

ነበልባል ያለበት የሚያቃጥል ነው
በንጽህና ሆኖ ላልተቀበለው
የሚያፍገመግም የሚጐዳ ነው

አምላካችን ሆይ አንተ ይቅር ባይ
እንደ ቸርነትህ በደልን አትይ /2/
አሜን /2/ ብለን ተቀብለናል

በድፍረትም ሣይሆን በፍርሃት ቀርበናል /2/
ማከበር ይገባናል በንጽህና ሆነን
ደፍረን አናቅለው እንዳያቃጥለን /2/

እንደምታዩትም ይህ ቁርባን ፈራጅ ነው
እንደሌላው ሳይሆን የተቀደሰ ነው /2/

ሱራፌል ኪሩቤል ፀወርተ መንበር
ለመያዝ ያልቻሉት ፈርተውት በክብር /2/
እኛ ተመገብነው አገኘን ድህነት
ለነፍስ ለሥጋችን ሆነልን ህይወት /2/

- -

ወላዲተ አምላክ (ማኅበረ ቅዱሳን)

ቅኝት -

ወላዲተ አምላክ የሁሉ እመቤት
ለምኚልን ለኛ ከልጅሽ ምህረት
በአንቺ አማላጅነት በእርሱ ቸርነት
እንዲያወጣን ነፃ ከፍርድ ቅጣት
ድንግል ሆይ ለምኚልን /2/

በበደል ተዳክሞ ፈቃደ ነፍሳችን
በምድራዊ ምኞት ናውዞ ልቦናችን
ፍቅርና ትህትና ጠፍቶ ከፊታችን
ለሞት እንዳይሰጠን ይህ ክፉ ሥራችን
ድንግል ሆይ ለምኚልን /2/

የምስኪኖች ተስፋ የደካሞችም ኃይል
ጠውልገናል እኛ ጥላ ሁኚን ድንግል
እምነት ጨምሪልን ልቦናችን ይጽና
እመአመላክ አብሪልን የመዳንን ፋና
ድንግል ሆይ ለምኚልን /2/
ፍጹም እንዳናዝን እንዳናፍር ኋላ
ተነቅለን እንዳንቀር ከዘላለም ተድላ
በፍቅርሽ መልሺን ከሲኦል ጎዳና
ድንግል መመኪያችን ተስፋችን ነሽና
ድንግል ሆይ ለምኚልን /2/

- -

<u>የመስቀሉ ፍቅር (ይልማ ኃይሉ በገና)</u>

<u>ቅኝት -</u>

የመስቀሉ ፍቅር ሲገባን /4/
እመቤታችንን እንወዳታለን
የመስቀሉ ፍቅር የገባቸው /4/
እመቤታችን አለች ከጎናቸው
አባህርያቆስ አባታችን
የመስቀሉ ነገር ቢገባው
ልቤ አፈለቀ አለ መልካም ነገር
ከእመቤቴ ጋራ ሲነጋገር
ከድንግል ማርያም ጋር ሲነጋገር
የመስቀሉ ፍቅር ሲገባን /4/
እመቤታችንን እናያታለን
ነይ ነይ እምዬ ማርያም
ነይ ነይ ቤዛዊት ዓለም
ለመናኒው ጸሎት ልዩ ዕጣን
የዋሻው ሻማ ነሽ እሙቢርሃን
መዓዛሽ ሸተተኝ ከግሸን
ትናፍቂኛለሽ ምን ልሁን
ትርቢኝማለሽ ምን ልሁን
አዝ
ዳዊት በመዝሙሩ ያነሳሻል
የያዕቆብ ድንኳን ነሽ ይልሻል
የእግዚአብሔር ሀገር የሚልሽ
እመቤቴ ማርያም አንቺ ነሽ /2/
ቤተልሔም ስሔድ አይሻለሁ
ቀራንዮ ስሔድ አይሻለሁ
ፍፁም አትለይም ከልጅሽ
የአንቺስ ልዩ ነው ፍቅርሽ /2/

- -

<u>ተዋህዶ (ይልማ ኃይሉ በገና)</u>

<u>ቅኝት-</u>

ተዋህዶ ተዋህዶ ሰማያዊት
የጸናች እምነት /2/ ሃሌ ሉያ
ተዋህዶ ተዋህዶ መንፈሳዊት
የመንፈስ መብራት /2/ ሃሌ ሉያ
ተዋህዶ ተዋህዶ መለኮት
ንጽሕት እምነት /2/ ሃሌ ሉያ
ባንቺ ቢያምኑ /2/ ቅዱሳን
ድል ነሱት ሰይጣንን /2/ ሃሌ ሉያ
ባንቺ ቢያምኑ /2/ ሰማዕታት
ተፈተኑ በእሳት /2/ ሃሌ ሉያ
እንደወርቅ /2/ ተፈትነው
አበራ ገድላቸው /2/ ሃሌ ሉያ
እንኑር /2/ በእምነታችን
በተዋህዶ መከበሪያችን /2/ ሃሌ ሉያ

- -

<u>በይስሀቅ ፈንታ (ይልማ ኃይሉ በገና)</u>

<u>ቅኝት - ስለቸርነትህ</u>

3322224 3154 4511 3154242 2
332224 3154 451 1 3154 242 2
332222-4 315 45 1544 542 2(በበገና ብቻ)
3322 224 551135 5
3322 224 3332 22 42
በይስሐቅ ፈንታ <u>ኢየሱስ ታረደ</u> /2/
ደሙን ከፈለና <u>አዳምን ታደገ</u> /2/
ተጨነቀ ጌታ ተሰቃየ ጌታ
የኔ መድኃኔዓለም የአዳም ልጅ አለኝታ
እንደሚታረድ በግ ተነዳ ወደ ሞት
ንጹሁ ኢየሱስ በደል የሌለበት
በማመን ሊሸከም የአዳምን መከራ
ስቃይ ተቀበለ ደሙ እየተዘራ
ለሚገርፉት ሁሉ ምህረትን ሲቸር
እርሱ ግን ሲገረፍ ብዙ ተቸገረ
የሰማነውን ድምፅ ማን ሰው እኮ አምኗል
የእግዚአብሔርስ ክንድ ለነማን ተገልጿል
ባየነውስ ጊዜ ህማም ተሸክሞ
ስለበደላችን ተገርፎና ታሞ
እጁ የታሰረው ይስሀቅ ተፈታ
ኢየሱስ ቀረበ በሰው ልጆች ፈንታ
ንፁህ በግ ቀረበ በደል የሌለበት በደለኛ ሆኖ
ሊሰቀል ሊገደል መስቀሉን ተጭኖ
በእውነት ደቂያችንን እርሱ ተቀበለ
በሰው ልጆች ፈንታ በእንጨት ተሰቀለ
እኛ ግን ከሰስነው እንደ ወንጀለኛ
ስለ እኛ ቢሰቀል ሰማያዊው ዳኛ
ለሰው ልጆች ህይወት የታሰበው ሰይፍ
አይተናል ሰምተናል በኢየሱስ አንገት ሲያልፍ
የመስቀሉ ስዕል ኧረ እንዴት ይገርማል
እዩት ንፁህ በግ በአርምሞ ይነዳል

- -

<u>ውሃ አጠጪኝ አላት (ይልማ ኃይሉ በገና)</u>

ቅኝት - ስለቸርነትህ

35-2222-4 313243 3
35-2222-4 313242 3
35-131524 3151 1 35-131524 3132 2 (በበገና)
232 4231 4444-53
232 4231 4444-52

ውሃ አጠጪኝ አላት አፍላጋት የሰራው
እንደ ተቸገረ ውሃ እንደጠማው ሰው
አይሁዳዊ አለችው አወይ አለማወቅ
ሰማያዊው አምላክ እራሱን ቢደብቅ
የእግዚአብሔር ስጦታ ውሃ ቢጠይቅሽ
የሚፈርሰውን ዘር ትልቅ ነገር አርገሽ
አንተ አይሁዳዊ እኔ ሳምራዊ ነኝ
እንዴት ይቻልሃል ውሃ ልትጠይቀኝ
እያልሽ ካለ እውቀት ግንብ እየገነባሽ
ምነው መለያየት መፈረስንስ ፈለግሽ
ትለምኚኝ ነበር የህይወትን መጠጥ
የእኔ አምላክነት በፊትሽ ቢገለጥ

ወልደ እጓለመህያው ውሃ ቢጠይቃት
ዘሩን ጠየቀችው ለመፍጠር ልዩነት
የሁሉን ፈጣሪ መሆኑን ሳታስብ
ይሁዳዊ አለችው በሚፈርስ ገንዘብ
ይህን የዓለም ውሃ የሚጠጣ ሞላ
ሳይጠማ አይቀርም ከእንግዲህ በኋላ
እኔ የምሰጠው አያስጠማም እና
ሰዎችን ጥሪያቸው ይርኩ ይጠጡና
የመንደሩን ሰዎች ወደዚህ ጥሪያቸው
ውሃ እንዳይጠሙ እስከ መጨረሻው
ይህንን ስትሰማ ደነገጠችና
ህሊናዋን ገዛች አገኘች ጥሞና
አለችው ጌታ ሆይ ውሃ እንዳልጠማ ከእንግዲህ በኋላ
እስከ መጨረሻው በህይወት ልሞላ
የሚያስጠማ ውሃ ለዘላለም ቀርቶ
ቃልህ ፍፁም ያድራል ህሊናዬን ሞልቶ

- -

ኃይልህ ሲገለጥ (ይልማ ኃይሉ በገና)

ቅኝት -

ኃይልህ ሰገለጥ በሰማይ /2/
አቤት ማን ይቆም ይሆን ከፊትህ /4/
አቤት ቀንደ መለከት ሲነፋ
አዋጅ ሲታወጅ በይፋ
ጻድቃን ሲጠሩ ለተድላ
ምን ይሆን የእኛ ተስፋ
አቤት መላእክት ሰማዩን ሲያርሱት
ቀድመው ሲሰሙ መባርቅት
ያልታየና ያልተሰማ
ድምፅ ሲሰማ ከራማ
አቤት ሰባቱ ነፋስ ተነጥቀው
ምድርን ሲያውኳት ቀዝፈው
ሲታዘዝ የባህር ሞገድ
ምድሪቱ እንዲቀላት ለፍርድ
አቤት ሲጠሩ ጻድቃን ቅዱሳን
መልካም የሰሩ ብሩካን
በምድር የሰሩ ትሩፋት
ሲያቀርቡ /ሲያሰሙ/ ለአምላክ ስብሐት
አቤት ኃጥአን ግን ለፍርድ ሲጠሩ
በጨለማ ዓለም ሊቀሩ
የማይጠቅም ዋይታ ሆኖ
መዋረድ ይሆናል አዝኖ

- -

ሥላሴን ከሰማይ (ይልማ ኃይሉ በገና)

ቅኝት -

ሥላሴን ከሰማይ እስጢፋኖስ አይቶ
አይኑ በመገረም ቀረ ተሰክቶ
የድንጋዩ ናዳ ቢወርድበት እንኳ
ሥላሴን በማየት እረስቶታል ለካ
ስብሐት ለእግዚአብሔር
የሰው ልጅ በቀኙ ተቀምጦ ነበር
እስጢፋኖስ ሲያየው በሚያስፈራ ክብር
ካህናተ ሰማይ ዙፋኑን ከበውት
ቅዱስ ቅዱስ ብለው ስብሐት ስብሐት
ስብሐት ለእግዚአብሔር
ምስጢረ ሥጋዌ ተገልጾለት በአካል
ሥጋው ቢታመምም ህዘኑን ሸሮታል
ነፍሱ ከጸባኦት ስታመሰጥር
ድንጋይ ይለቅማሉ ያልታደሉ ፍጡር
ስብሐት ለእግዚአብሔር
ለፈሪሳውያን ተሰውሮባቸው የሥላሴ ምሥጢር
ድንጋይ ሰበሰቡ ጻድቁን ለመውገር
እርሱ ግን ከሰማይ ፈጣሪውን አይቶ
ድንጋዩን እረሳው ህሊናው ተነክቶ
ስብሐት ለእግዚአብሔር
የሰማዩ ሥርዓት ልዩ ስለነበር
ምንም አልመሰለው የድንጋዩ ክምር
የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ ተገልጠው
ስቃዩን አስረሱት ህሊናውን ነጥቀው
ስብሐት ለእግዚአብሔር
ልባችሁ ጆሮአችሁ መቼ ተገረዘ
የጠነከረ ነው ለአምላክ ያልታዘዘ
መንፈስ ቅዱስንም ትቃወማላችሁ
እንደገዛ ፈቃድ እየተመራችሁ
ስብሐት ለእግዚአብሔር

- -

የጴጥሮስን እንባ (ይልማ ኃይሉ በገና)

ቅኝት-

የጴጥሮስን እንባ ስጠኝ እልሀለሁ
ኃጢአቴን ልናዘዝ ፍቅርህን እያየሁ
በሞት ጥላ ውስጥ እንኳን ብሄድ ጌታ ሆይ /2/
ልቤን በፍቅር ውሃ እጠበው እባክህ
ቸርነትህ በዝቶ ምህረት ቢያሰጠኝ
እጆቼን ዘርግቼ እማፀናለሁኝ
ደምህ የፈሰሰው ለእኔ ስለሆነ /2/
በኃጢአት ብትወተኝ ልብህ አልጨከነም
ዓለማዊ ምግባር ልቤ ቢከተልም
ከዚህ ሁሉ ማዳን ጌታ አይሳንህም
ኃጢአት እየሰራሁኝ ባስቀይምህም /2/
በሂሶጵ እርጨኝ ጌታ እጠበኝ እባክህ
ዲያብሎስ ያመጣው ጸጸት የውድቀት ነው
የይሁዳ ምሬት የሞት ነው ፍጻሜው
ይህንን መማረር እኔ አልፈልግም /2/
የውድቀት ጉዞ እንጂ ትንሣኤ የለውም
ጴጥሮስ አባ ብሎ የተማፀነበት
ፍቅሩን በንስሀ ስቦ ያመጣበት
ፍጻሜው የሚያምር ንስሀ ስጠኝ /2/
የለቅሶ አምሀ የእንባ ህይወት ስጠኝ

- -

ያ ድህ ተጣራ (ይልማ ኃይሉ በገና)

ቅኝት-

ያ ድህ ተጣራ እግዚአብሔርም ሰማው
ደርሶ ስላንኳኳ ከፀባኦት እንባው
አምላክ በቸርነት በምህረት ጐበኘው
ባለቀሰ ጊዜ ግራ የገባው ሰው
መሻትህ ብቻ ነው የሚፈለግብህ
እግዚአብሔርን ጥራ እመን ትድናለህ
ንገረው ችግርክን የውስጥህን ብሶት
ይሸረዋልና አስፈሪውን ህይወት
ግራ የተጋባው የተከፋው ገጽህ
ይበራል በጸሎት አምላክህን ጠርተህ
ለወገን ለዘመድ ያስቸገረው መላ
ሲቀል ታየዋለህ ካነባህ በኋላ
ሳግና ንዴትህ ይቀራል ይሻራል
በርሱ ፈንታ ሰላም ፍቅር ይከብሃል
በከንቱ መጨነቅ እራስን መጥላቱ
ነውና የኢጋንንት መግቢያ ምልክቱ
ሀዘን በህሊናህ በፈሰሰ ጊዜ
ንገረው ለአምላክህ የልብህን ትካዜ

- -

እውነት ስለሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ (ይልማ በገና)

ቅኝት-

እውነት ስለሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ
ዋለ በአደባባይ ሲሰደብ ሲከሰስ
የሐሰት ዳኝነት አምላክን ወቀሰው
ህይወት ሰጠን እንጂ ጥፋቱ ምንድነው
ኪቃሉ እብለትን ባያገኙበትም
ዝምታውን አይተው አላዘኑሰትም
ባላወቁት መጠን ጠሉት ካለበደል
ጥፋቱ ምን ይሆን የሚያደርስ ከመስቀል/2/
እውነት ስለሆነ .....
የልቡን ትህትና ፍቅሩን ሳያስተውሉ
ቸሩ ጌታችንን አቻኩለው ሰቀሉ
እሩህሩሁን ጌታ ቸንክረው ሰቀሉት
ሞትን አስወግዶ ቢሰጣቸው ህይወት /2/
እውነት ስለሆነ .....
ስለቸርነቱ ስድብን ከፈሉት
ስለርህራሄው የእሾህ አክሊል ሰጡት
ሀሞትና ከርቤ ሆምጣጤ ደባልቀው
መራር አስጎነጩት ጨክኖ ልባቸው/2/
እውነት ስለሆነ .....
ፈውስን ለሰጣቸው ልባቸውን ሞልተው
አሉት ወንበዴ ነው ስቀለው ስቀለው
ከእጁ በረከትን የተሻሙ ሁሉ
ይጮሁ ነበረ ይገደል እያሉ /2/
እውነት ስለሆነ .....

- -

በማዳኔ ቀን ጠራሁህ (ይልማ ኃይሉ በገና)

ቅኝት -

በማዳኔ ቀን ጠራሁህ ይለናል ጌታ
ዛሬ እንመለስ በፍጥነት ሳናመነታ
ነገ ለራሱ አውቆበት የነገው ሰው ነው
የእኛ ቀን ዛሬ መሆኑን ሁሉም ይረዳ
ለንስሀ ነው የሰጠን ይህንን ጊዜ
ነገ ሳይመጣ ታጅቦ በሞት ትካዜ
በሞት መዳፍ ነን ሰዎች ሆይ እንዳንዘነጋ
እንሄዳለን ለፍርዱ እፈጣሪ ጋ
በማዳኔ ቀን ጠራሁህ ይለናል ጌታ...
የነገን ነገር ማን አውቆ ይተማመናል
ዛሬ ነው መዳን በእውነት ኑ ተብለናል
የእግዚአብሔር ጥሪ ካወቅነው እጅግ ኃያል ነው
በፍቅሩ ስቦ ለማዳን እጁ ሰፊ ነው
በማዳኔ ቀን ጠራሁህ ይለናል ጌታ...
ጌታ በረከት በእጁ ሞልቶ ተርፎታል
በእግዚአብሔር ታመን በጽድቁ ልብህ ይረካል
እንደ ወንዞቹ ሰላምህ ተርፎ ይፈሳል
የአምላክ በረከት ሁል ጊዜ ይከተልሀል
በማዳኔ ቀን ጠራሁህ ይለናል ጌታ...

- -

በኃይልና ጥበብ (ይልማ ኃይሉ በገና)

ቅኝት - ዋኔን /ትዝታ/

በኃይልና ጥበብ ትልቆቹን ትቶ
ንጉሥ አደረገው ደሀውን ቀብቶ
በእረኝነት ሜዳ ልቡን መረመረው
እንደልቡ ሆኖ ዳዊትን ቢያገኘው
እንደልቡ ሆኖ ዳዊትን ቢያገኘው
አዝ.....
ምንም ታናሽ ቢሆን አካሉ ቢኮስስ
የተገባ ነበር በእግዚአብሔር ፊት ሊነግስ
የሰው ዓይን ያልሞላው ትንሽ ብላቴና
አባት ሆኖ ነበር በእግዚአብሔር ህሊና
አባት ሆኖ ነበር በእግዚአብሔር ህሊና
አዝ.....
የጌታችን እናት ታላላቅ ቅዱሳን
ይልቁን ጌታችን የሰው ልጆች መድህን
በዓለም ሊወለድ ከዳዊት በሥጋ
ተስፋ ተሰጥቶታል እንዲሁ በጸጋ
እንዲሁ በጸጋ እንዲሁ በጸጋ
አዝ.....
የዋህ ስለነበር ዳዊት በህይወቱ
ከበሩ ሲገባ ፈላለት ዘይቱ
ሳሙኤል አክብሮ በእግዚአብሔር ፊት ቀባው
አምላኩ ቢወደው ታላቅ አደረገው
አምላኩ ቢወደው ታላቅ አደረገው
አዝ.....
የምሥጋና ሀብቱን ከንግሥና ጋራ
አጣምሮ ሰጥቶታል መልካም እንዲሠራ
ሌትና ቀን ሳይል ሲመገብ ምሥጋና
እየደረደረ መሠንቆ በገና
እራዕይ ተሰጥቶት ከላይ ከደመና
ድንግልን አሳየው አንገቱን ሲያቀና
ድንግልን አሳየው አንገቱን ሲያቀና

- -

ሰዓሊለነ ማርያም (ሲሳይ ደምሴ በገና)

ቅኝት -

ሰዓሊለነ ማርያም /2/
ሀበ ወልድኪ ሐር መድኃኔዓለም
ለምኚልን ማርያም /2/
ከቸሩ ከልጅሽ ከመድኃኔዓለም
ለመኑ እነግር ሀዘነ ልብየ
እንበሌኪ ማርያም እግዝእትየ
ወፍጡነ ስምአኒ ጸሎትየ
ለምኚልን ማርያም .....
ለማን እነግራለሁ የልቤን ሀዘን
የጌታዬ እናት ከአንቺ በቀር
ፈጥነሽ ስሚኝ ጸሎቴን
ሰዓሊለነ ማርያም .....
ድንግል ሆይ አሳስቢ ሀዘን መከራሽን
በሄሮድስ ዘመን የደረሰብሽን /2/
ድንግል ሆይ አሳስቢ እረሀብ ጥምሽን
በግብፅ በረሀ የደረሰብሽን /2/
ለጻድቃን ያይደለ ለኃጥአን አሳስቢ
ለንጹሀን አይደል ለአደፉት አሳስቢ /2/
ለምኚልንማርያም .....
ክብሬ ተስፋዬነሽ እናቴ እልሻለሁ
ስምሽን ስጠራ ከጭንቀቴ አርፋለሁ/2/
ውዷ ስጦታዬ ድንግል ሆይ ነይልኝ
ባዶነቴን አይተሽ ጉድለቴን ሙይልኝ/2/
ሰዓሊለነ ማርያም .....
በእንተ ፍቅረ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
ኪንያ እስእለኪ ማርያም በሀሌሉያ
ኃዘና ስምኢ ወብካያ ለሀገሪትነ ኢትዮጵያ
ሰዓሊለነ ማርያም.....

- -

ሰላም ተዋህዶ (ሲሳይ ደምሴ በገና)

ቅኝት -

ሰላም ተዋህዶ ሰላም አርቶዶክስ
በደሙ ያጸናሽ መድኅን ኢየሱስ /2/
የአዳም መመኪያ የሄዋን ሀገር
አንቺ አይደለሽም ወይ የቅዱሳን ክብር/2/
በከንቱ የሞተው የአቤል መስዋዕት
የሄኖክ ሀይማኖት ያዳንሽው ከሞት
አንቺ የኖህ መርከብ የሴም በረከት /2/
በአብርሃም ድንኳን ተወልደሽ ያደግሽ
የይስሀቅ መአዛ ወደር የሌለሽ
ያዕቆብ በህልሙ በቤቴል ያየሽ
የዮሴፍ አጽናኙ ተዋህዶ ነሽ /2/
የሙሴ ጽላት ነሽ የአሮን በትር
የኢያሱ ሀውልት የጌዲዮን ጸምር
የሳሙኤል ሙዳይ የእሴይ ትውልድ
የዳዊት በገና የሰሎሞን ዘውድ
የታተመች ገነት የምስጢር ጉድጓድ /2/
ቡአዴና ህድረት የኬልቄዶን ዘር
ቱሳሄና ሚጠት ውላጤም ጭምር
ያልተቀላቀለሽ ንጽህቲቱ ምድር
ኢሳይያስም አይቶ በሩቅ መነጽር
ስለቅድስናሽ ሆነ ምስክር /2/
በነኤልያስ ቤት የወርቅ መሶብ
ውስጥሽ የተሞላ በምሥጢር መዝገብ
የኤልሳ ማሰሮ የህይወት መዝገብ
ፊራን የምትባይ የእንባቆም ተራራ
ሁሉን የምታሳይ ከቀኝ ከግራ
የህዝቅኤል እልፍኝ ባለአንድ በራፍ
የማትከፈቺው በኬልቄዶን ቁልፍ /2/
የህግ መፍለቂያ የነፃነት ቦታ
የሚኪያስ ሀገር አንቺ ነሽ ኤፍራታ
እፀ ህይወታችን የኤፌሶን ቅርስ
የተፈወሱብሽ እነ አቡን ቄርሎስ
ለተፈወስንብሽ ከኬልቄዶን ቁስል
ተዋህዶ ላንቺ እልል እንበል /2/
አንቺን በማየቱ በብርሃን ተቋም
ደስ አለው ከልቡ ዘካርያስም
በውስጥም በውጪም የሌለሽ እንከን
የህይወት ምግብ ነሽ ተዋህዷችን /2/
ሐዋርያት ይምጡ ያውሩ ያንቺን ዜና
የሚያወቅ ሲናገር ደስ ያሰኛልና
ሰማዕታት ልጆችሽ የፃፉሽ በደም
የህይወት መጽሐፍ ነሽ የጽድቅ የሰላም/2/
አንቺን ለመጠበቅ እስከ ዓለም ፍፃሜ
ቃል እንገባለን ባለንበት እድሜ /2/
እናምናለንና በፈጣሪያችን
እናምናለንና በአምላካችን
ካንቺ እንደማንለይ ምን ጊዜም ቢሆን /2/

- -

ጽኑ ክርስቲያኖች (ሲሳይ ደምሴ በገና)

ቅኝት -

ጽኑ ክርስቲያኖች ልባችን አይውደቅ
የእግዚአብሔርን እቃ ጦሩን እንታጠቅ/2/
ማዕበሉን አይቶ ልባችን አይፍራ
ታማኙ ጌታችን አለ ከአኛ ጋራ /2/
ሰማዕታት ልጆቿ የዓለምን ጣዕም ንቀው
ያላውያንን ዛቻ ፈተናውን አልፈው
ርሃቡን ስደቱን መከራን ታግሰው
ለዚህ አድርሰውታል ተዋሕዶን ጠብቀው
ከህደቱ ቅሰጣው ኑፋቄው ቢነዛ
ሰይፍ ስለቱ ቢያፏጭ ፉከራው ቢበዛ
በድንግል ቃል ኪዳን መሠረቷ ጠብቋል
በቅዱሳን ጸሎት ቅጽሯ በእሳት ታጥሯል፡፡
ጥንተ ጠላታችን ፈተና እያስነሳ
ዙሪያችንን ቢከብብ ተርቦ እያገሳ
መከራን ቢያበዛ ስደት ቢያደርስብን
እስከ ሞት የሚያደርስ ስቃይ ቢያበዛብን
ዓለም ላቆመችው ለጣኦት አንሰግድም
በመከራው ጽናት ሀይማኖት አንክድም
ከሚነደው እሳት አምላክ ያድነናል
ባያድነን እንኳን እሳቱን መርጠናል፡፡
እንደ ግያዝ አንሁን ታውሮ አይናችን
በእሳት ሰረገሎች ተከቧል ዙሪያችን
ሰይፍን የሚያነሱ በሰይፍ ይወድቃሉ
ከእኛ ጋራ ያሉት ከእነርሱ ይበልጣሉ፡፡
የጠሉህን ውደድ በሚል ህያው ቃሉ
ሲያሳድዱህ ጻልይ በሚል ክቡር ቃሉ
በመንፈሳዊው ፍቅር ይጠንክር ልባችን
ይህን ነው ያዘዘን ቅዱስ አምላካችን
ነቅተን ከታጠቅን የጽድቅን ጥሩር
በትጋት ከቆምን በእምነት በፍቅር
በጾምና ጸሎት ስግደት ምጽዋት
በንስሃ ጸድተን ከጸናን በእውነት
በሥጋ ወደሙ በጸጋው ከታተምን
በህይወትም በሞት ከእርሱ ጋር ህያው ነን፡፡
በወደደን በእርሱ ከሁሉ እንበልጣለን በወደደን በእርሱ አሸናፊዎች ነን
ንፋስ ማዕበሉ የማይነቀንቀው
መሰረቷ ጽኑ ቅጽሯም ጠንካራ ነው
የገሀነም ደጆች አይችሏትምና
ጸንታ ትጓዛለች ተዋሕዶ ገና
ጽኑ ክርስቲያኖች ልባችን አይውደቅ
የእግዚአብሔርን እቃ ጦሩን እንታጠቅ/2/
ማዕበሉን አይቶ ልባችን አይፍራ
ታማኙ ጌታችን አለ ከእኛ ጋራ /2/

- -

ክበር ተመስገን (ሲሳይ ደምሴ በገና)

ቅኝት -

ውለታህ ብዙ እግዚአብሔር
ስንቱን ዘርዝሬ ልናገር
ስለማይነገር ሥጦታህ
ክበር ተመስገን ልበልህ /2/
ክበር ተመስገን ጌታችን
ለዚህ ያደረስከን
በአምሳልህ ፈጥረህ አክብረህ
በፍጹም ፍቅርህ ጠብቀህ
የምትመግበን በቸሮታህ
ክበር ተመስገን የኛ ጌታ
ክቡር ገናና ኃያል ነህ
ማንም በምንም አይመስልህ
የዓለማት ገዢ ኤልሻዳይ
የጌቶች ጌታ አዶናይ
መርገም ተጭኖን የኃጢአት እዳ
ሲኦል ስንጋዝ ስናይ ፍዳ
መጥተህ ፈለግኸን በፍቅርህ
ከእቅፍህ ወጥተን እንዳንቀር
ከድንግል ማርያም ተወልደህ
አርአያ ቤዛ ሆነህ
ፍፁም ፍቅርህን ገለጽክልን
ሰላማችንን አወጅክልን

- -

በኪሩቤል ላይ ተቀመጠ (አቤል ተስፋዬ በገና)

ቅኝት -

በኪሩቤል ላይ ተቀመጠ
ምድርና ሠማይ ተናወጠ
ለዚህ ቅዱስ አምላክ ምስጋና
አስር አውታር ባለው በበገና
ክብርና ግርማን ለብሰህ
በላይ በአርያም ያለህ
እልፍኙን በውሃ የሠራህ
ሰውን በአርአያህ የፈጠርህ
ላንተ ቅዱስ ጌታ ምሥጋና
አስር አውታር ባለው በበገና
አቤቱ በጽዮን ከብረሃል
በእሳት መድረክ ላይ ተቀምጠሀል
ጠፈሩን በጥበብ ዘርግተሃል
ቀንና ሌሊቱን ለይተሀል
ላንተ ቅዱስ ጌታ ምሥጋና
አስር አውታር ባለው በበገና
በኃይል በሰማይ ታጥቀሀል
የባህሩን ጥልቀት ለክተሀል
የሞገዱን ጩኸት አናውፅህ
ጠላትን በፍቅር የገዛህ
ላንተ ቅዱስ ጌታ ምሥጋና
አስር አውታር ባለው በበገና
ሰማያት ጽድቅህን ተናገሩ
ያንተን ክብር ዝና መሠከሩ
ፍጥረትን አስውበህ የፈጠርክ
ሁሉን በችሎታህ ያደረግክ
ላንተ ቅዱስ ጌታ ምሥጋና
አስር አውታር ባለው በበገና

- -

ስምሽ ጉልበት ሆኖኝ (አቤል ተስፋዬ በገና)

ቅኝት -

ስምሽ ጉልበት ሆኖኝ ወጣሁት ዳገቱን
ድንግል ባንቺ ምልጃ አለፍኩት ወጥመዱን
ድንግል ማርያም ባንቺ ምልጃ ሠበርኩት ወጥመዱን
አምላክ ቀድሶሻል ከሁሉም አብልጦ
ካንቺ ይወለድ ዘንድ በሥጋ ተገልጦ
ለዓለሙ መዳን ምክንያት የሆንሽው
ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም አንቺ ነሽ
ወጀቡን ልሻገር ባንቺ ተደግፌ
ድካሜ ይወገድ ከጥላሽ ሥር አርፌ
ያላንቺ መሀሪ ከቶ የለምና
ባንቺ ተመገብኩት የሠማዩን መና
ይመስገን ፈጣሪ የነ ዳዊት አባት
ቤቴን ሞልቶልኛል ባንቺ አማላጅነት
አንቺን የተጠጋ በነፍስም በሥጋ
በልጅሽ ይወርሳል የሠማዩን ዋጋ
ዳግም እንዳልራብ ነፍሴ እንዳትጠማ
ከማይደርቀው ምንጭሽ አጠጪኝ እማማ
ከቤትሽ ጉበቼ እረፍት አግኝቻለሁ
እድፌ ተወግዶ አዲስ ለብሻለሁ

- -

ስሜ ዳዊት (አቤል ተስፋዬ በገና)

ቅኝት -
ስሜ ዳዊት የእሴይ ልጅ
እናራለሁኝ በእግዚአብሔር ደጅ
ታዳጊ ነኝ የበጉን መንጋ
በመታገል በጌታ ጸጋ
እረኝነት ነው ግብሬ /2/
አምላክ የሰጠኝ ግብሬ
በጌታ ፊት ይዤ በገና
ስለ ስሙም ላቅርብ ምሥጋና
ጣቴ አያርፍም ሰልፍን ይሰራል
አንደበቴም ቅኔን ይቀኛል
እረኝነት ነው ግብሬ /2/
አምላክ የሰጠኝ ግብሬ
በሳኦል ፊት ቢልቅ ጎልያድ
ህዝበ እስራኤል ልቡ ቢሸፍት
አምላካችን ጌታ ሲከብር
ለጎልያድም በቅቶታል ጠጠር
እረኝነት ነው ግብሬ /2/
አምላክ የሰጠኝ ግብሬ
በአባቴ ፊት ፈልቷል ዘይቱ
ከብላቴናው ጸንቶ ጉልበቱ
ጸጋ እግዚአብሔር ፈሷል በላዬ
ከእረኝነት ጠርቶኝ ጌታዬ
እረኝነት ነው ግብሬ /2/
አምላክ የሰጠኝ ግብሬ
በፍርድ ወንበር አለ በገና
ለሰማይ ንጉስ ሞልቶ ምሥጋና
ከሳኦል ላይ መንፈሱ ይራቅ
ከፈጣሪው ጋር ነፍሱ ትታረቅ
እረኝነት ነው ግብሬ /2/
አምላክ የሰጠኝ ግብሬ

- -

ሞትን በሞት ሸረሀ (አቤል ተስፋዬ በገና)

ቅኝት -

ሞትን በሞት ሸረሀ እንዳልሞት ያረከኝ
ከመቃብር ውጣ ብለህ የጠራኸኝ
አራት ቀን ሞልቶታል ይሸታል ሰው ቢልህ
አልአዛር ሆይ ብለህ ጠራኸኝ በቃልህ
ከሞቱት መካከል እኔን አስነስተህ
በፊትህ አቆምከኝ አይኖቼ እያዩህ
ተስፋ ቆርጠው ሳለ የዋህ ዘመዶቼ
አብሬያቸው በላሁ ከሞት ተነስቼ
ዕድሜዬን በሙሉ ከአልጋ ተጣብቄ
ሞቴን ስጠባበቅ ከወገን ርቄ
የናዝሬቱ ኢየሱስ የኔን መዳን ወደህ
አዲስ ሰው አረከኝ እድፌን አስወግደህ
ነፍሰ ገዳይ ሆኜ ብሰቀል ከጐንህ
በደምህ ምልክት ገባሁኝ ከቤትህ
ጌታዬ ብዙ ነው ያንተ ቸርነት
አለምን አዳንከው ዳግም እንዳይሞት
ጀርባህን በጅራፍ ስለኔ ተገረፍክ
እስከ ቀራንዮ ደምክን አንጠፈጠፍክ
እንዴት ይከፈላል ይህ ታላቅ ውለታህ
ለእኔ ያደረከው በዚያች ጐልጐታ

- -

መች ይረሳል (አቤል ተስፋዬ በገና)

ቅኝት - ስለቸርነትህ
5422 4 2315-1-551 1/2x/
1513-1 2315-1-511 1
1513-1 2315 4222
መች ይረሳል የዋለልን ውለታ
ቸርነቱ እፀብ ፍቅሩ የጌታ
የታተመው በልባችን ጽላት
ሞትን ገድሎ የሠጠንን ህይወት
በጥፋቱ ቢወጣ አዳም ከገነት
ቃል ገባለት ዳግም ሊሠጠው ህይወት
ህያው ጌታ አምላክ ፈጣሪ ሳለ
ስለ ቃሉ በእፀ መስቀል ላይ ዋለ
በአይሁድ እጅ በጽኑ ተንገላታ
የፍቅር አባት ክርስቶስ የእኛ ጌታ
ሥጋው ደክሞ ቅዱስ ደሙ ፈሰሰ
አዳችንን በሞቱ ደመሠሠ
ስንጠላው እርሱ አብዝቶ ወደደን
ስለ ፍቅሩ ሞትን ገድሎ አዳነን
ባርነትን ኃጢአትን ከኛ ጥሎ
ነፃ አወጣን በመስቀል ላይ ተሰቅሎ
ሰላማችን የድንግል ማርያም ፍሬ
ይገባዋል ምስጋናና ዝማሬ
ስለ ፍቅሩ ስላረገልን ሁሉ
ተቀኙለት ፍጥረታት ዝም አትበሉ

- -

የዛሬ ዘመን መኮንን (አቤል ተስፋዬ በገና)

ቅኝት -

የዛሬ ዘመን መኮንን
ይለማመጣል ሎሌውን
ዶሮ ካዘዙ በአንድ ውለታ
አባብሎ አያውቅም ጌታ
ጻድቁ አናፂ ለአንክሮ
መጥረቢያ የለው ሙሽ መሮ
ይህን አዳራሽ ሠራልን
ዓለምን /6/
ቤት ስትሠራ ነፍስ ወይዘሮ
በጣሪያ ማገር ተሸጕርጉሮ
ብዙ እንኳ ነበር ሸንበቆው
ሥጋ ጨረሰችው
ለቀድሞ ሰዎች በህልማቸው
መጪውን ሁሉ ገልፆላቸው
ያላዩት የለም ከሆነው
ሁሉ እንዳለሙት ነው
ሞት ገበሬ ነው ለመሬት
እሰው ቤት ነዋሪ ሲዋትት
ያስደንቀኛል በተግባሩ
አፈራርሶ መኖሩ

እንግዳ አለብሽ አንቺ ነፍስ
ከሥጋ በቀር የማይቀምስ
አብረን እንፈልግ በማለዳ
እስኪ እዚያ ላይ ፍሪዳ
እንግዳው ድንገት ስትደርስ
ሳትሰናዳ ቆየች ነፍስ
ለእንጀራ ብቻ የለው መላ
ዓለምን /4/ አምን ብላ
የወልድ አምላክን እራቱን
ሳላሰናዳ ምናምን
በሥጋ አደረ ትላንትና
ጌታ ሰው ሆኗልና

- -

በደም ሊታጠብ ኃጢአቴ (አቤል ተስፋዬ በገና)

ቅኝት -

በደም ሊታጠብ ኃጢአቴ /2/
በደም ሊታጠብ ኃጢአቴ
ተበጣጥሶ ሊወድቅ እስራቴ
ወጣህ ቀራንዮ ጎልጎታ
በእኔ ተጉበተህ አንተ ጌታ
በወንበዴዎች መካከል
እንደወንጀለኛ ስትሰቀል
ከዋክብትም ረገፉ
ከመሬት ላይ ተነጠፉ
መቃብርን አፈራርሰህ
በስልጣንህ ሞትን ገድለህ
ሲኦልም ባንተ ተበርብራ
ነፍሳት ወጡ በየተራ
ጠላት ሞቷል አይነሳም
ምርኮ ሆኗል በደም ካሳ
ምስጋና ብቻ የለም ሌላ
ሊታደገን ከሞት ጥላ
ዳግም የለም በኛ ሞት
አንዴ ሞቷል ሞት ሊሞት
በክርስቶስ ክርስቲያን ነን
ሞት ከሞተ ህያዋን ነን

- -

ሠላምህ ይብዛላት (አቤል ተስፋዬ በገና)

ቅኝት - ስለቸርነትህ
4231551 422
4231551 42331 45131-4-222
145131 5-4245 5 5 145131 5-4242 2
432451 3211 1 432451 4222
231422 3423 3 14513 42222

ሠላምህ ይብዛላት ምድሪቱ
የሰው ልጅ እንዳይቀር በከንቱ /2/
የሌለንን ሰላም እንሰብካለን
በጎ ነገር ጠፍቶን እንጮሀለን
ጸሎት ልመናችን ከንቱ እንዳይቀር
ሰላምን ላክልን እግዚአብሔር
የካም ልጆች በዝተው በምድር ላይ
ገመናን ገለጡ በአደባባይ
ፍፁምነት ጠፍቶ ከልባቸው
በክፋት ተመላ ጉባኤያቸው
በሰላም ቤት ቆመን ሰላም ጠፍቷል
ታንኳችን በነፋስ ተጨናንቋል
አድነን ጌታ በሆይ እንዳንጠፋ
ገስፀው ማዕበሉን ሁነን ተስፋ
አለም ስለሰላም ቢዘምርም
ምድራችን ከሠላም አርፋ አታውቅም
ሰላማችን አንተን ስንይዝ ነው
እውነተኛ ሰላም ምናገኘው

- -

በደላችንን የተውከልን (አቤል ተስፋዬ በገና)

ቅኝት -
በደላችንን የተውከልን
በመስቀል ተሰቅለህ እራቆትከን
ጐንህን ተወግተህ የእኛ ጌታ
ሞትን ወጋህልን ወደማታ
ሞትን ወጋህልን በጐልጐታ
ጠላት ክንዱን ጭኖብን በላያችን
የእዳ ደብዳቤ በአንገታችን
አስሮ ቢጥለንም ከጉድጓዱ
በደምህ ፈታኸን ከወጥመዱ /2/
በስብራትህ የጠገንከን
አንተ ደክመህ ያጽናናኸን
መስቀል ተሸክመህ ክንድህ ዛለ
ሞታችን በሞትህ ተገደለ /2/
ሲኦል ተበርብራ በሥልጣንህ
ነፍሳት ተመልሰው ወደቤትህ
ሞልቷል ከበረቱ በአንተው መንጋ
ድል ተከፍሎ ለሞት ዋጋ
ደም ተከፍሎ ለሞት ዋጋ
ከዋክብት ረገፉ ስለ ክብርህ
ብርሃናት ጨለሙ ላያሳዩህ
ሙታን ከመቃብር ተነሱና
ምስጋና አቀረቡ እንደገና /2/

- -

ኧረ አንቺ አለም (ዲ.ታደለ በገና)

ቅኝት -
ኧረ አንቺ አለም /4/
አታታይ ተይ ግድ የለም
ማታለልሽ ከቶ ለምን ነው
ካንቺ ጋር ላልሆን እስከ ወዳኛው
የኔስ ሀገሬ በሰማይ ነው /2/
ፍቀድልኝ ግድ የለም
ጉብቼ ልኑር በገዳም
አስቸገረኝ ይሄ ዓለም /2/
ባይጠቅመኝም ሳጠራቅም
ከማይረባኝ ስኝቀዳደም
በከንቱ ቀረሁ ከዚች ዓለም /2/
የዕለት ጉርሴን ካልነፈከኝ
የዓመት ልብሴን ከሰጠሽኝ
ከዚህ በላይ ለኔ ምን አስፈለገኝ /2/
ዓለምን ላልጨርሳት ተስገብግቤ
አንዱን ነጥቆ አንዱን ደርቤ
ዳር አወጣኝ ከንቱ አስቤ
ይሻለኛል እኖራለሁ
ከፍርድ በፊት ሳልሞት ልዳን
ትወቅ ነፍሴ ሕያውነቷን
በሥራዋ ትውረስ መንግሥትህን
ስስቷን ትታ የዚች ዓለምን
ነፍሴ አደራ ተጠንቀቂ
ሞትን ያህል አለ ነጣቂ
የዚያች ሲያል እንዳትወድቂ
የአምላክሽን ሕጉን ጠብቂ
ንስሀ ግቢ ተፀፀቺ
አይጠቅምሽም ይሄ ዓለም ላንቺ
የሞይን ሞት ኋላ እነዳትሞቺ
የጽድቅን ጉዞ መንገድ ናፍቂ
ዕድሜ ጥላ ነው ፈጥኖ ይደርሳል
ሀብት ንብረቱም ከዚህ ይቀራል
ጽድቁን አስቢ እሱ ይበልጣል
ከፃድቃን ጎራ ይመድብሻል
ኮብልዬ ነበር ትዛዝህን ጥሼ
ላለፈው ጥፋት እኔን ወቅሼ
በንስህ ዳኛ ራሴን ከፍቼ
ተቀበለኝ በይቅርታ ተመልሼ

- -

እማዬን አባዬን (ዲ.ታደለ በገና)

ቅኝት -

እማዬን አባዬን ማለቱ ቀረና
አያቴ ቅድመ አያቴ " "
ልጂ ልጂ ሆነ የልቅሶአችን ቃና
ባሳደጉ ፋንታ መጦርን ሲችሉ
ባስተማሩ ፈንታ መደገፍ ሲችሉ
አልቅሶ ቀባሪ እንዴት ይሆናሉ
ደረሰ እያለች እናት ስታይህ
ለወግ መረግ በቃ ብላ ስትገልጽህ
የመቃብር ጉዞ . . .
በልጅ ሊኮራ አባት ሲጠብቅሽ
ወልደሽ ልትስሚለት
ለአቅመ ሔዋን በቅተሽ
ጨርሶ ስንብት ምን ይሆን ያሰኘሽ
በልጅ ሊጦሩ ነበር ምኞታቸው
ጧሪ ቀባሪ አጡ ባዶ አደረግናቸው
ፍቅርን ሳንጨርስ ታይተን ጠፍተናቸው
የወላድ መካኖች ሆኗል ዕድላቸው
የሀገር ባላደራ ተተኪው አንተ ነህ
ባባትህ ተተካህ አላማን ሰንቀህ
የዕቃቃ ጨዋታ እባክህ ይቅርብህ
ታቅፋ አሳድጋህ አዝላ በዣርባዋ
አጉርሳ አስተምራ በድሃ ኑሮዋ
ጥቁር መልበስ ሆነ የእናት ውለታዋ
ያለውን ኹኔታ ጠንቅቀን ስናውቀው
ወገን ተነጥሎ ሲኼድ እያየነው
ከቶ እንደምን ይሆን ልቦና ያጣነው
ተምሮ ጨርሶ ሥራ ያዘ ሲባል
ወዳጅ ዘመድ ሲለው ወገኑን ያኮራል
ሀገር ተረክቦ አደራን ይወጣል
አንድ ዓመት ሳይሞላው መሞቱ ይሰፋል
በራስ የሚመጣው በሽታ ይቅርና
ከፍቶ የመጣውን የጣልያንን ጀግና
መመለስ ተችሏል በራሱ ጐዳና
አንተም ወኔ ታጠቅ ጀግንነት ነውና
ኣምላክ ሳይፈርድብህ አንተው ባንተ ፈርደህ
ያንተን ሕይወት ባንተ እንዴት ታጠፋለህ
ፈጣሪ ያልሸሸህን አንተ ግን ኮበለልህ
አንተው በእጅህ ጭረህ በእሳት ተበላህ
ትሰማኝ እንደሆን ዘዴውን ልንገርህ
መጥፎውን ተውና ከፈጣሪ ታርቀህ
እስከ ወዲያኛው ኑር መልካም ሕይወት ፈጥረህ

- -

ሰቀሉህ (ዲ.ታደለ በገና)

ቅኝት -

ሰቀሉህ ወገሩህ ምንም ኃጢኣት ሳይኖርብህ
ይስቀሉ ይውገሩኝ ሐሰት በቃልህ ሳይገኝ
ቀራንዮ እንዴት ዝም አልሽ
ጐልጐታ እንዴት ጨቀንሽ
ኣምላክ ሲሰቀል አስቻለሽ ተሰቃየህ ኣምላክ ሆይ
ተወጋህ ቸሩ ሆይ እንደ ተራ ሰው ባደባባይ
እየተመታ በአይኑድ ወገን
ጋራውን ወጣ ተራራውን
መስቀሉን ይዞ ቢጫኑትም
ያለም ፈጣሪ የሁሉ ጌታ
ላደረገልን ሳይል ውለታ
በፈጠረው ነው የተንገላታው
አዝ . . . . . .
ምድር ታልቅስ ወዮ ትበል
በሠራችው በዚያ በደል
ከፊት ወድቃ ከዚያ መስቀል
ምድር ሆይ ስሚ ጉሮሮ ሰጥተሽ
አትዘናጊ ግፍን ረስተሽ
በደም ያነፃሽ ከበደልሽ
ከመስቀሉ ነው መድኃኒትሽ
በሰውነቱ ክፋት ሳይኖረው
በቃሉ ሐሰት ጭራሽ ሳይወጣው
ጌታ ሰቀሉት አይኑድ ወንጅለው
አዝ . . . . . (በለሆሳስ)

- -

ገዳመ ቆሮንቶስ (ዲ.ታደለ በገና)

ቅኝት -
አርባ ሌሊት መዓልት ሳይቀመጥ ቆሞ
ጾምን አስተማረ በፈቃዱ ጾሞ
ሥራትንም ሰጠ እራሱ ፈፅሞ
ይመስገን ከሁሉ አስቀድሞ
አምነዋለው የሚል የሚወድ ጌታውን
ይፁም የጸመውን ጾሞ ያሳየውን
ለሕጉ ይገዛ ከፍቶ ልቦናውን
በቃሉ ይከተል አምላኩን
እምነት ያለው ቢኖር ሥራ የሌለው
እንደማይድን ይወቅ ተስፋ እንደሌለው
ክብር አይሰጠውም ዘላለማዊው
በጸጋ አምላኩን ሊያየው
ቆሞ የጸለየው ኃጢኣት ሳይኖርበት
ሥርዓትን ሊሰጥ ነው ለፈጠረው ፍጥረት
ጾሞና ጸልዮ መንግሥቱን . . .
በበረሀው ገብቶ በቆሮንቶስ ገዳም
40ሌሊት መዓልት ደከመኝ አላለም
ከቆመበት እግሩ ጭራሽ አልታጠፈም
ሲያዝን ነው በንፅህና እንድንጾም
በንጽህና ሆኖ ጾሞ የጸለየው
እርሱ ነው ኣምላክን በነፍስ ዐይኑ ያየው
በሥራው ለመዳን አምኖ ያልዘገየ
ተስፋውን ከፍቅሩ ያልለየ
ለሥጋችን እንድትሆን ምድርን ባረካት
ምግበ ነፍስ ሠጠ ጾምንና ጸሎት
ፍቅርና ትህትና እንዲሁም ስግደት
ሊሆነን ሰማያዊ ሀብት

- -

ድንግል (ዲ.ታደለ በገና)

ቅኝት -

ድንግል እለምንሻለሁ በውዳሴሽ ዜማ
ድንግል ሰላም ለኪ ስልሽ ድምጼ እየተሰማ
የፈጣሪዬ እናት ሆና እያለች
ኼደች በበረሀ ውሃን ተጠማች
ወይ ልጇ እያለች እግሯ ሳይሰለች
አምላክን ታቅፈሽ ስትወርጂ በረሃ
ምንም እንደሌለው እንደ ምስኪን ደሃ
አንቺ ያህል እናት እንዴት ይጥማሽ ውሃ
ፈጣሪ በዕውነት ከሁሉም መርጦሻል
ፍጹም ሰው ለመሆን በማህፀንሽ አድሯል
ከድንግልና ጋር እናቱ ሆነሻል
በነቢያት ትንቢት የተነገረልሽ
ብርህይት ልቦና ድንግል አንቺ ነሽ
እንኳን በሰው ፍጡር በውሻም ያልጨከንሽ
ስምሽን እጠራለሁ እያልኩ ድንግል ማርያም
እመቤቴ ካላልኩ ውስጤ አይታደስም
ስምሽን ለጠራ እመቤቴ ብሎ
በልጅሽ ቃል ኪዳን ትደርሻለ ቶሎ
ከነፍስሽ ነፍስ ነስቶ ከሥጋሽ ሥጋን
እናቱ አደረገሽ ሰውን ለማዳን
በዚህ ገለፀልን ታለቅ ክብርሽን
ይሄ ነው ያሰጠሽ ማማለድ አንቺን
ከብዙሀን መርጦ ኣምላክ የሰጠን
የፃድቃን ክብራቸው እመ ብዙሀን
ለኛ ግን አንቺ ነሽ አማላጃችን
የንጹሀን አክሊል የኃጥኣን መመኪያ
የፈጣሪሽ እናት ሆነሻል ማደሪያ
ባዶ አቁማዳ ይዤ ስምሽን ስጠራ
ይሄ መልካም ስምሽ ሆኖኛል እንጀራ
አልፈዋለሁ ያን ሁሉ መከራ
እመሰክራለሁ ያን ሁሉ አማላጅነትሽ
በስምሽ አድጌ እንዴት ልርሳሽ አንቺን
አቁማዳዬን ሞልቶ ያበላኝ ስምሽ
ሁሌ እጠራዋለሁ አይደክመውም አፌ
ውሻው ሲያባርረኝ ያን ሁሉ ስደክም
ድንግል ካንቺ ሌላ ስንቅ አልነበረኝም
በልቼ አድር ነበር እያልኩ ስለ ማርያም
አይለየኝ ድንግል በረከትሽ ዛሬም
ዛሬም ደካሞች በስምሽ ነው ያሉት
ስለ ድንግል ማርያም አትርሱን እያሉ
የለት ጉርሳቸውን ባንቺ ይበላሉ
አለብኝ ውለታ ምከፍለው ለልጅሽ
ንጹህ አገልግሎት ለእናትነትሽ
ወገቤን ታጥቄ እናቴ ልበልሽ

- -

እንደ ክቡር ዳዊት (ዲ.ታደለ በገና)

ቅኝት -
እንደ ክቡር ዳዊት እኔም በበገና
ስማኝ ስማኝ እያልኩ አለቅሳለሁና
እባክህ ተቀበል የውስጤን ልመና /2/
ዛሬም በምድር ላይ ነገም በሰማይ
እባክህ ኣምላኬ ስቃይ እነዳላይ
የፀባኦት ጌታ እርዳኝ አዶናይ /2/
በገናዬ ድምጹን ወዳንተ ሲያሰማ
አይኔም እያነባ ውስጤም እየደማ

ዝማሬዬን ቁጠር ከቅዱሳን ዜማ ካባቶቼ ዜማ
ሰማይና ምድር በቃልህ ያቆምህ
ባህር ውቅያኖስን በእጅህ የሰፈርህ
በእምነቴ አድነኝ ልቦናን ሰጥተህ ጌታዬ ስልህ
ያላንተ የሆነ ምንም ነገር የለ በጣም ያስገርማል
ሲነጋ ሲጨልም ወቅቱ ሲፈራረቅ በጋው አልቆ ሲዘንም
ጥበብህን መርምሮ የደረሰው የለም
በጐልዳፋው አፌ እንኳን በእኔ አቅም
ጠበብትነን የሚሉ ተናግረው አልቻሉም
መርምረው አልቻሉም
የበላይ የሌለህ የንጉሦች ንጉሥ እኛ ብንበድልህ ብንወድቅም በበደል
ቀድመህ ያዘዝከንን ትዕዛዝህን ብንጥስ
አንተ ነህ ያዳንከን ሥጋችንን በመልበስ /2/
ዛሬም አወድሼ ከንቱ እንዳልሆን
ከመንፈስ ርቄ እንዳልፈተን
እባክህ አድለኝ ንፁህ ሕሊናን /2/
መቼም አልልህም አትፈትነኝ
ብቻ የዚያን ጊዜ ጸሎቴን ስማኝ
የለበስኩት ሥጋ እንዳያስጥለኝ /2/
ጨካኝ ሆነህ ሳይሆን እንዲህ የምልህ
አንተም አዝዘኸኛል . . . ብለህ
ከበርህ ቆሚያለሁ ፈውሰኝ ልልህ
እንደ ፃድቁ እዮብ ይዩኝ ዐይኖችህ /2/
ብቸኝነት ከብዶኝ ውስጤ ተርበትብቷል
ጠላት በውድቀቴ ይሳለቅብኛል
የሚጽናናኝ የለም ሐዘኑ ከብዶኛል
ካንተ በቀር ለኔ ማን ይደርስልኛል /2/
ጸንቷል በሽታዬ ካልጋ ወድቄአለሁ
ሰው እንደ ማይረዳኝ አረጋግጫለሁ
እንደ ረሔል እንባ ወዳንተ መልሼያለሁ /2/
ልቦናዬ ካንተ ብዙ ነገር ይሻል
ያላንተ የሚሆን ምን ነገር ይገኛል
የኔም መሻት ባንተ ሁሉም ይፈፀማል
አዎ ይፈጸማል
እኔማ በራሴ ብዙ አስቤ ነበር
ከቁሙቴ ስንዝር አንዳችም ላልጨምር
ይበቃኛል ገናስ በራሴ መፎከር
ስያዝ ተረዳሁኝ ጌታ ያንተን ነገር
አምላክ ያንተን ነገር

- -

ኖኅተ አንቲ (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ)

ቅኝት

ኖኅተ አንቲ ለፀሀየ ጽድቅ ለፀሀየ ጽድቅ ምሥራቁ /2/
እንተ ባቲ ሰረቀ ለብርሃነ ዓለም ጽድቁ /2/
የተዘጋቸው በር የምሥራቋ ደጃፍ
የታተመች ገነት የአዲስ ዘመን ምዕራፍ
ሌቱ ያለፈብሽ የተስፋ ማለዳ
በልጅሽ ተፋቀ መርገም እና ፍዳ /2/
ኖኅተ አንቲ ለፀሀየ ጽድቅ .....
ጨለማን የሻረ የጽድቅ ጐህ ፋና
የአዲስ ታሪክ ቀለም የዕረፍታችን ዜና
ሥጋሽ ሰውነቱ ነፍስሽ ነፍሱ ሆነ
ድል አድራጊው ልጅሽ ጠላትን በተነ /2/
ኖኅተ አንቲ ለፀሀየ ጽድቅ .....
የእምነት ምንጭ ነሽ የደስታ መፍሰሻ
የኃያሉ ንጉሥ መንበር መናገሻ
ንጽህና ተውበሽ በቀኙ ስትቆሚ
ባዶ የሚሞላ ድምፅሽን አሰሚ /2/
ኖኅተ አንቲ ለፀሀየ ጽድቅ .....
ማዘን መጨነቁ በምድር ሲበዛ
ከልጅሽ አሳስበሽ አድርጊልን ጤዛ
የተስፋ ወጋገን ምህረትን አሳይን
በብርሃንሽ ፀዳል ለምሥጋና አብቂን /2/
ኖኅተ አንቲ ለፀሀየ ጽድቅ .....

- -

በባዕድ ሀገር (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ)

ቅኝት -

በባዕድ ሀገር አመልከሀለሁ
ፊቴን በምሥራቅ እመልሳለሁ
በምኞት ቤቴም አስብሃለሁ
ምትክ የለህም ይህን አውቃለሁ
አዝ
ጠላት ቢነሳ በነፍሴ ላይ
የምታድነኝ ነህ በሰማይ
የአንበሳ ጉድጓድ ቢሆንም ቤቴ
ታዳጊዬ ነህ ቸር መድኃኒቴ
አዝ
በምድር ጣኣታት አትረክስም ነፍሴ
አንተ አምላኬ ነህ ይሄ ነው መልሴ
የመርገም ሰዎች ቢነሱብኝ
አምናለሁ ባንተ በማትተወኝ
አዝ
ማዳን የእግዚአብሔር ያንተ ብቻ ነው
ከእጅህ ሊነጥቀኝ የሚችል ማነው
አንበሳው ትራስ ምኞት ሆኖኛል
ሰላም አምሽቼ ያው ነግቶልኛል
አዝ
ለሞት ብባልም አለሁ በሕይወት
በርሱ በአምላኬ በርሱ ቸርነት
አንተን ያመነ ማነው ያፈረ
ስምህ ቅዱስ ነው የተከበረ

- -

ከበለሷ ፍሬ (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ)

ቅኝት -

ቢፈልግባትም መልካሙ ገበሬ
አልተገኘባትም ከበለሷ ፍሬ /2/
.....
ለስልሶላት ነበር ሃይማኖት መሬቱ
ተቀጥሮላት ነበር አጥር ሥርዓቱ
ተለቅሞላት ነበር ድንጋይ ፈተናዋ
ፍሬ ግን ታጣባት በመጨረሻዋ
አዝ
ፍሬ የሌለባት ቅጠል ስለሆነች
ተካይዋን በምግባር ስላላስደሰተች
መልካሙ ገበሬ ሊቆርጣት ተነሳ
ሌሎች እንዳይጠፉ በርሷ የተነሳ
አዝ
ለንስሀ ሚሆን ዕድሜ እንዲሰጣት
ጠባቂ መልአከዋ ተማፀነላት
ምክርና ተግሳፅ ይጨመርላት
ታፈራ ከሆነ ላመት እንያት
አዝ

ልመናውን ሰምቶ ጌታውም ፈቀደ
ጥቂት እድሜ ሊሰጥ ሊታገስ ወደደ
ዳግመኛ ሲመጣ ፍሬ ካላፈራች
ተቆርጣ ወደ እቶን እሳት ትጣላለች
- -

ታምኜህ ወጣሁኝ (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ)

ቅኝት -

ከካራን ስወጣ ወደ አዲሱ መንገድ
አላውቅም ነበር ወዴት እንደምሄድ
ያንተ ቃል ነውና በማመን ወጣሁኝ
በረከት አግኝቼ ዘሬን አበዛሁኝ
አዝ
ሲሰማኝ ምሬቱ የቀድሞ ኑሮዬ
ረገምኩ ታሪኬን ጨለመኝ ኋላዬ
ታራ ያስተማረኝ ተስፋ ቢስ ሕይወት ነው
ስትጠራኝ አየሁት የነገ ክብሬን ነው
አዝ
ከቶማን ሆኜ ነው እንዲህ ያከበርከኝ
ከአህዛብ ለይተህ ከፍ ከፍ ያረከኝ
አብርሃም ሆይ ያልከኝ የወደድከኝ አምላክ
ልግዛ ላምልክህ ለክብርህ ልንበርክክ
አዝ
ህዝብህን ታደገው በረከት አይጥፋ
መሆንክን ይወቀው የዘለዓለም ተስፋ
አለማመን ይራቅ ጥርጥር ይወገድ
ልጆችህ ይጓዙ በአንዲቱ መንገድ
- -

ሕሙም ስለአዳነ (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ)

ቅኝት -

ሕሙም ስለአዳነ በእጆቹ ዳስሶ
ሙትን ስላስነሳ በእጆቹ ዳስሶ
ይህ በደል ሆኖበት ለአምላክ ኖላዊ ሐር
በእጸ መስቀሉ ላይ ዘርግቶ በፍቅር
ቀኝ እጁን በሳዶር ግራውን በአላዶር
ተቸነከረልን ጌታ በሁለት ችንካር
አምንስቲቲ ሙኬርያ አንቲ ፋሲልያሱ
ቤተ ቤቅደስ ምኩራብ በተመላለሱ
ባህር ላይ በሄዱ ልክ እንደ በየብሱ
ለአምላክ ቤዛ ኩሉ ይህ ወንጀል ሆኖበት
በዕጸ መስቀሉ ላይ ተላልፎ ለመሞት
ሁለቱን በአንድ ላይ እግሮቹን በዳናት
ተቸነከረልን አምላክ የእኛ ህይወት
አምንስቲቲ ሙአግያ አንቲ ፋሲልያሱ
በልቡ አስቦ ድህነት የሚያመጣ
ከበጎ ልቦናው በጎ የሚወጣ
ይህ ወንጀል ሆኖበት አምላክ መድኅን ዓለም
በእጸ መስቀሉ ላይ ተዘርግቶ ለዓለም
ልቡን በአዬራ ደረቱን በሮዳስ
ተቸነከረልን ወልደ አምላክ ክርስቶስ
አምንስቲቲ ሙዳሱጣ አንቲ ፋሲልያሱ

- -

የአንተ ዜማ (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ)

ቅኝት -
ልቦና የሚመስጥ አጥንት አለምላሚ
ምድራዊ አይደለም ምንጩ ሰማያዊ
ሄደህ የሰማኸው ከመላእክት ከተማ
ምንኛ ጥዑም ነው ያሬድ የአንተ ዜማ
አዝ
ከትንሽ አንስቶ እስከ ግዙፎቹ
አምላክ እንደሰራው በስነ-ፍጥረቱ
ያልነገርከው የለም በዜማ ድርሰትህ
ከመንፈስ ቅዱስ ቃል ነውና እውቀትህ
አዝ
ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ የሆነውን
መገረፍ መሰቀል መሞት መነሳቱን
እናስታውሰው ዘንድ አመልክተህ ጽፈህ
አበረከትክልን ከዜማው አስማምተህ
አዝ
ለፀሐይ እናቱ ለብርሃን መውጫ
ለድንግል ማርያም ውዳሴ እንዲገባ
በምልዐት በስፋት በምሥጢር በአንክሮ
ያቀረብከው ዜማ ዛሬም አለ ከብሮ
አዝ
ጸጋ በረከትህ ይደር በሁላችን
ሊቀ ተዋህዶ ያሬድ አባታችን
ጠፍተው እንዳንባክን የአንተን ዜማ ዓዋቂ
አምላክ ያስነሳልን ሊቃውንት ጠባቂ
- -

ያቺን የተሰፋ ምድር (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ)

ቅኝት -
ያቺን የተሰፋ ምድር እናፍቃታለሁ
ኢየሩሳሌምን ሁሌም እመኛለሁ
በመሻቴ ብቻ እንዳይሆን አውቃለሁ
ሕግና ፍርድህን ከልቤ ጽፌያለሁ
አዝ
መንገዷ ልዩ ነው ለሥጋ አይመችም
ያለብዙ ድካም በከንቱ አይገኝም
በሰፊው ያላችሁ ከዚህ ተመለሱ
የአባቶቼን ሀገር ከኔ ጋር ውረሱ ከኔ ጋር ውረሱ
አዝ
የይሁዳ መንገድ የዴማስ ጎዳና
ከቤት አያደርስም አያዘልቅምና
ጴጥሮስ ዮሐንስን አሳዩኝ በልና
ወንድሜ ተመለስ ከኢየሩሳሌም ና ከኢየሩሳሌም ና
አዝ
በግብፅ የምትኖሩ ወዲህ ተሰብሰቡ
በይሁዳ ያላችሁ ወደ ጽዮን ግቡ
ከባቢሎን ሸሹ መዝገቧንም ዝጉ
ኢየሩሳሌምን መጠጊያ አድርጉ መጠጊያ አድርጉ
- -

ወንጌሉን ያመኑ (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ)

ቅኝት -

ይትበሃሉን እና ቃሉን አነበብነው
ሐተታውን እና ምሥጢሩን ተማርነው
በቅዱሳን ሕይወት ወንጌሉን አየነው
በቅዱሳን ሕይወት ወንጌሉን አየነው
አዝ
አጋንንትን ገዝተው በእሳት ውስጥ ሲያልፉ
ሞትን በሞታቸው ደግመው ሲያሸንፉ
እባቡን እረግጠው አንበሳውን ሲያዙ
ደመናውን ጠቅሰው በአየር ላይ ሲጓዙ 2x
አዝ
ወንጌል ትምህርት ብቻ አይደለችም ብለው
የተነገረውን በሕይወት ለውጠው
አምላክ ዘበጸጋ ሆነው አየናቸው
ወንጌሉን በገቢር ተማርን ከገድላቸው 2x

አዝ
የወንጌሉ ቅኔ ገድሉ ይፈታዋል
ፊደሉን ንባቡን ይተረጉመዋል
ይሆናል ተብሎ የተማርነውን
ቅዱሳን በገድል ሆነው አሳዩን 2x
አዝ
ፍልስፍና አይደለም የወንጌል ትምህርቱ
ዕውቀት ብቻ አይደለም ሕጉና ትንቢቱ
በሕይወት የሚታይ በእውነት የሚኖር
መሆኑን አሳዩን ቅዱሳን በግብር 2x

- - - - - - - - - - - - - - - - - - -

የመድኃኒት እናት (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ)

ቅኝት -

የመድኃኒት እናት ሕመምተኛ ልጅሽ
ምህረትን ፍለጋ ቆሜአለሁ ከደጅሽ
ጸሎት ልመናሽን ታምኜአለሁና
ከቤትሽ መልሽኝ ዳግም እንደገና
አዝ
የደካሞች ብርታት የምስኪናን ተስፋ
ለዓለም አልተውሽኝም በከንቱ እንድጠፋ
የህይወቴ ጥበብ እረፍቴ ሠላሜ
አማልጂኝ እላለሁ ከመቅደስሽ ቆሜ
አዝ
በፍቅርሽ ብርሃን ነው ልጅሽን ያየሁት
ባዶ ማድጋዬን ጋኔን የሞላሁት
አልጫ ኑሮዬ ዛሬ ተለውጧል
በደልና ኃጢአቴ በምልጃሽ ተፍቋል
አዝ
ብርሃን ወጥቶለታል ጨለማ ሕይወቴ
ዛሬም ጥላ ሁኚኝ እናቴ እመቤቴ
ፍቅር ውለታሽን ዘወትር አውጃለሁ
ከእእላፍ መካከል እቀኝልሻለሁ
አዝ
በረከት ረድኤትሽ ይኑር ከእኔ ጋራ
ምሥራቅ ቤተልሔም የሲና ተራራ
መናን ያቀርብሽው ለተራበው ዓለም
ድንግል ዘለዓለም የሚመስልሽ የለም

- - - - - - - - - - - - - - - - - - -

ናቁርብ ለከ (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ)

ቅኝት -

በደለኞች ሳለን ምህረትን ሰጠሽን
ስለዚህ ስምህን እናወድሳለን
ዘለዓለማዊ ነህ አልፋና አሜጋ
ስምህን እንጠራለን በተሰጠን ጸጋ
ለከ ሃይል ክብር ወስብሐት
ንዜምር ለከ አምላከ አማልክት (2x)
አዝ
ሰማያትን ከፍተህ ብትወርድልን ምነው
አድነን ታደገን ብለን ያነባነው
የምህረት አባት ነህ ዛሬ አቅንተኸናል
ሊነገር የማይችል ክብርን ሰጥተኸኛል
ቅዱስ አንተ ገባሬ ዓለማት
ንሴብሐከ አምላከ አማልክት (2x)
አዝ
የጠፋውን ፈለገህ በመስቀል አዳንከው
ለምሥጋና ቢቃ በክብር ከለለከው
ቤዛና ተስፋችን መድኃኔዓለም
በምድር በሰማይ የሚመስልህ የለም
ለከ ሃይል ክብር ወስብሐት
እግዚአብሔር አምላከ አማልክት (2x)
አዝ
በእሳትና ውሃ ረድተህ አሳለፍከን
ከድካም አድነህ እረፍትን ሰጠኸን
በመከራችን ቀን ረድተኸናልና
ከፊትህ ቆመናል ዛሬም ለምሥጋና
ለከ ሃይል ክብር ወስብሐት
ንዜምር ለከ አምላከ አማልክት (2x)

- - - - - - - - - - - - - - - - - - -

የተወደደ ስምሽ ማርያም (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -

የተወደደ ስምሽ ማርያም
እንዳንቺ ንጹህ በዓለም የለም
አሳስቢልን እንዲምረን መድኃኔዓለም
አዝ
በንጽህናሽ በመመረጥሽ
ድንግል በእውነት እፀ-ብ ድንቅ ነሽ
አሳስቢልን እንዲምረን መድኃኔዓለም
አዝ
ፍጥረታት አንቺን ይማፀኑሻል
ከሲያል ዓለም አውጪን ይሉሻል
አሳስቢልን እንዲምረን መድኃኔዓለም
አዝ
አስራትሽን ኢትዮጵያን
ጠብቂልን ድንግል ህዝቧን
አሳስቢልን እንዲምረን መድኃኔዓለም

- - - - - - - - - - - - - - - - - - -

ወንበዴ የነበርኩኝ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -
ወንበዴ የነበርኩኝ ሀገር ያሰለቸሁ
በመስቀል ላይ ሆኖ ታሪኬን ለወጠው
አስበኝ ስላልኩት በኋላ ስትመጣ
ገነትን ለማየት የመጀመሪያው ሰው ሆንኩኝ ባለዕጣ
አቤት ፍቅሩ የእግዚአብሔር የእግዚአብሔር
ግሩም ፍቅሩ የእግዚአብሔር የእግዚአብሔር
አስበኝ ስላልኩት አሰበኝ ጌታዬ
ወንበዴ የነበርኩኝ ስርቆት ነው ሞያዬ
በመስቀል ላይ ሆኖ ህዝቡን ያስብ ነበር
እኔስ አላየሁም (2) እንዲህ ያለ ፍቅር
ግሩም ፍቅሩ የእግዚአብሔር የእግዚአብሔር
ኃያል ፍቅሩ የእግዚአብሔር የእግዚአብሔር
አልታይም ብዬ ኃጢአትን ስሰራ
ተመለስ ይለኛል ስሜን እየጠራ
እንዳልሞትበት ነው በኃጢአት ታስሬ
ፍቅሩን አልዘለቀውም (2) እንደዚህ ዘርዝሬ
አቤት ፍቅሩ የእግዚአብሔር የእግዚአብሔር
ግሩም ፍቅሩ የእግዚአብሔር የእግዚአብሔር
ኃያል ፍቅሩ የእግዚአብሔር የእግዚአብሔር
መከራ ሲከበኝ መጥቶ ያጽናናኛል
በህዘኔ ጊዜ እግዚአብሔርም ያዝናል
አይኑ ከእኔ አይርቅም ጥበቃው አይከፋም
ስሙን እጠራለሁ (2) በጌታዬ አላፍርም
ግሩም ፍቅሩ የእግዚአብሔር የእግዚአብሔር
ኃያል ፍቅሩ የእግዚአብሔር የእግዚአብሔር

- -

አ ጌታ ሆይ ተሰቀልክ ሆይ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -

አ ጌታ ሆይ ተሰቀልክ ሆይ (2)
ምድር አለቀሰች እያለች ዋይ ዋይ
አ ጌታ ሆይ ተሰቀልክ ሆይ
ኮረብቶች ደንግጠው መድረሻ ጠፋቸው
ከዋክብትም ፈርተው ጨለማ ዋጣቸው
እጅግ አይደንቅም ወይ ጌታ መሰቀሉ
የጌቶቹ ጌታ ችንካር ላይ መዋሉ
አ ጌታ ሆይ ተሰቀልክ ሆይ...
ሰማይና ምድርን በፈጠረበት
ጨለማና ብርሃን ባደረገበት
ችንካር ተከሉበት መቱት በህብረት /2/
አ ጌታ ሆይ ተሰቀልክ ሆይ...
ድንግል አለቀሰች እንባዋ ፈሰሰ
ስደተኛ ልጇ መከራ ቀመሰ
ህማሙን ሳስበው አለቅሳለሁኝ
የስቃዩን ነገር አስባለሁኝ
አ ጌታ ሆይ ተሰቀልክ ሆይ...
እንባዬን ጠራርጐ እረሀቤን ተካፍሎ
ሞተልኝ ጌታዬ ስለሞቴ ብሎ
እኔ ልሙትልህ ሲለኝ ሰማሁት
እንዲህ የወደደኝ ምን አረኩለት

ይበላሃላ /አለሙ በገና/

ቅኝት-ሰላምታ
142-45 142-22 /2/
142-45 13132 31513 242-22
ይበላሃላ/4/
አንተንም አፈር ይበላሃላ እንደሚኝ ሰው እንደተላላ
አሊ ሲሞት ያለብኝ አሳር
በአንድ እጇ ዶማ በአንድ እጇ ምሳር
አሊ ሲሞት መብሌ ጉበት
ከአሊ በፊት እኔ ልሙት
አሊ ሲሞት መጠጤ አተላ
አንተንም አፈር ይበላሃላ
እኔንም ጎንደር ይሸጡኛላ
በላው አፈር በላው አፈር
ያንን አንገት ያንን እግር
አንቺንም አፈር ይበላሻላ
እንደሚኝ ሰው እንደተላላ
በላው አፈር በላው አፈር
ያስተማረህን ያንን ምሁር
በላው መረፊ በላው መረፊ
ያንን የዋህ ሰው ያንን ገበሬ
አንተንም አፈር ይበላሃላ
እንደሞኝ ሰው እንደተላላ
በላው አፈር በላው አፈር
ያንን ታሪክ ያንን ዘመን
ያንን ባህል ያንን ፍቅር
በላው አፈር በላው አፈር
አንተንም አፈር ይበላሃላ
እንደሞኝ ሰው እንደተላላ

ዋኔን (አለሙ በገና)

ቅኝት- ሰላምታ
444445 1145 1113
444445 1115
23113፣ 231 23113፣ 242
ምን ያጣላችኋል ዋኔን በመሬት ጉዳይ ዋኔን
አሁን ዘር ሲጠፋ ዋኔን ይቀር የለም ወይ ዋኔን/2/
ምድርን ጠላ መጥመቅ ዋኔን ማን አስተማረው ዋኔን
እይጠራ አጠጣው ዋኔን ያንን ሁሉ ሰው ዋኔን/2/
በል እድር ጆሮዬ ዋኔን ነገ እቆርጥሀለው ዋኔን
ባንተም ክፉ ነገር ዋኔን ሰምቼብሀለው ዋኔን/2/
ወይ አላሳጨድነው ዋኔን ወይ ከብት አልበላው ዋኔን
ከቶ መቼ ይሆን ያ ሳር ማለቂያው/2/
ብላጨው አመመኝ ዋኔን ብሰራው ከፋኝ ዋኔን
አንድ ራሴ እኮ ነው የሚያስጨንቀኝ/2/
የኩዳዬውስ ጾም ዋኔን ምንም አላለው ዋኔን
ሰው ሁሉ ያለቀው ዋኔን በህማማቱ ነው ዋኔን/2/
በባላገር ነበር ዋኔን ኑሮስ የሚሻል ዋኔን
ከተማ ሰው ጉበቶ ዋኔን ምን ምን ሰው ይሆናል ዋኔን

ወንድሜ ጠፍቶ

ቅኝት- ሰላምታ
42222 45 4442 42 42332 45 4442 42
42222 45 1545131 11113 11113 242 42
31555 131 11113 11113 242 42
3155555 15 15 15 444542 42
ወንድሜ ጠፍቶ ስሄድ ነብር አግኝቶኝ ከመንገድ
አልተመለስኩም ወዲያው ሄድኩኝ እኔን ይብላኝ እያልኩኝ/2/
የቀድሞ ዘመን ስህተት በፆም ቀን አሳ መብላት
ያሁን ዘመን ሰው አያውቅ መላ በፆም ሽሮ ነው የሚበላ/2/
የኛ መድኃኒት አይነቶች በብዙ አሉ ቅመሞች
ነገር ግን እኔ ሳስበው ስራስሩ መልካም ነው/2/
ያባቶቻችን ውሃ ዋና ላይ ላዩን ነበር በጤና
የዛሬ ልጆች ይበልጣሉ ውስጥ ለውስጥም ይሄዳሉ/2/
ኮሶ ተጣብቶኝ ትላንትና መድሀኒት ስሻ ዋልኩና
ድንገት ሰማሁኝ አንድ ዜና የወዲያ ሰዎች ህግ ደንብ
አይከለክልም ምግብ
የኛ ስርአቱ ከባድ እንዲያው በባዶ ሆድ/2/
የጌታችንን ፀባይ ያለኔ የሚያውቅ አለ ወይ
ማታ ለግብር መልካም ሰው ቀን ሲቆጣ ክፉ ሰው/2/
አያሳስትም ሰአት ቀጠሮ ያከብራል ሞት
ሽማግሌ አይል ህፃን ሞት ጠያቂ ነው ሁሉን
አሁን ይመጣል በእውነት ሞት ብሎ አይቀርም ሞት/2/
እሁድ ቅዳሜ ቢሆን እበላ ነበር ምሳዬን
እንዲህ በፆም ቀን የምዞረው ለጊዜ ማግረሻ ነው/2/
ትንሽቤት ሰራሁ እንደአቅሞኛ ሁለት ሶስት ሰው የምታስተኛ
አላስገባ አለች እርሷው ጠባ ሰው በሰው ላይ እየገባ/2/
ከታች ጉርጓዱ የጠለቀ ከላይ ጉበኑ የጠበቀ
እንዲህም አድርገው ቢሰሩት መፍረሱ አይቀርም ሞት/2/
የዛሬ ዘመን ሰው ስራ ሳሩም ቅጠሉም አያኮራ
እውቀቱስ ያንተ መሰለኝ በአብነትህ አድነኝ/2/
አባቶቻችን ካህናት ሲጠመጥሙ ከጠንት
ለስልጣናቸው ለክህነት መለያ ነበር ምልክት
አሁንማ ጠምጣሚዎቹ ሹሞቹና ጠበቆቹ/2/
ይህቺ በቅሎዬ ምን ሆነች አጉል መጥፎ አመል ለመደች
የጎረቤቷን እያየች ጭነት መግልበጥ አመጣች/2/
የሰሞኑ ጋብቻ ድንቅነቱ ከቀድሞ እጅጉን መለየቱ
መሆኑ ቀርቶ እስከ ሞት ተጀመረ ተጧሪ ፈቶ ወጣት ማግባት/2

አዝላው ወረደች(ይልማ በገና)

ቅኝት- ስለቸርነትህ

3-5 ነ54 3332 2 42 35 ነ54 4444 4/2/
445ነ5 ነ3 ነ555-524 4231 242/በበገና ብቻ/
33 444-ነ 555ነ 42 35 ነ54 3332 2 42
አዝላው ወረደች ወደ ግብፅ/2/
ስደተኛዋ የአምላክ እናት ይህ አለም ለሷ መች ተገባት
አለም በምሉአት አስተናግዳት የፍቅር ምንጯ ተሟጦባት
እነ ኮቲባን እየላከች የአምላክን እናት ተሳደበች
እነ ሄሮድስን እየላከከች ህፃኑን ልትገል አሳደደች
የከብርን ጌታ ተሸክማ ውርደት ለበሰች እንደሸማ
የሀብቱን ጌታ በጀርባ አዝላ ሰው ተዘከራት ተቸግራ
በቃሉ ትዕዛዝ ምድርን ሰርቶ ተንከራተተ ማደሪያ አጥቶ
ጌታ ሲወለድ የምስራች በረት ሰጠችው አለም ታጋች
ግና መላእክት በሰማያት ሀሌሉያ አሉ በፍርሀት
ወልድን ከአብ ቀኝ ከላይ አይተው ደግሞ በምድር ከድንግል ክንድ
ከላይም ሳይነል ተመልክተው ከላይም ሳይነል ተመልክተው
አለም በምሉአት አስተናግዳት የፍቅር ምንጯ ተሟጦባት
እነ ኮቲባን እየላከች የአምላክን እናት ተሳደበች
እነ ሄሮድስን እየላከከች ህፃኑን ልትገል አሳደደች
በቃሉ ትዕዛዝ ምድርን ሰርቶ ተንከራተተ ማደሪያ አጥቶ
ጌታ ሲወለድ የምስራች በረት ሰጠችው አለም ታጋች

አልዓዛር ይነሳ(ይልማ በገና)

ቅኝት-

አልዓዛር ይነሳ መግነዙን ፍቱለት
በፅድቅ አደባባይ ይመላለስበት
ተስፋ ላለው ህይወት ልቡ ይነቃቃ
ነፍሱ እንዳትወሰድ በኢጋንንት ተሰርቃ
የበደል እስራት አይቶ ይመላለስ
አዲሲቷን ምድር በንስሐ ይውረስ
ሞት መሻሩን አውቆ ከሞት በላይ ይሁን
በእግዚአብሄር ቸርነት ልቦናው ይታመን
በደሉ ቢበዛ ልቦናው ቢከብድም
ከአምላኩ ቸርነት በሚዛን ይበልጥም
ሐጥያቱን ተናዞ ንስሐ እንዲገባ
መንፃትን አሳዩት የፍቅርን እንባ
የሚያስደንቅ ብርሀን አይቶ ይመላለስ
አዲሲቷን ምድር በንስሐ ይውረስ
ካህናት አፅናኑ ህዝቡን በፍቅር ቃል
ሞት ህይወት አይደለም በቃሉ ተሸሯል
በአምላክ ብርሀን ይመላለስ አይቶ
ንስሐ ይጠበው እንዲታይ አብርቶ
ንፁህ ልብስ አልብሱት ነፍሱ ሀሴት ታድርግ
እርሱም ህያው ይሁን በሰዎች መአረግ
ከመቃብር ይውጣ ጌታ እየጠራው ነው
ከህይወት እንጀራ ማነው የሚያግደው
ብርሃን ክርስቶስ ለሱ ተሰውቷል
ስጋው ለእርሱ እኮ ነው ማን ይመገበዋል
ብርሀን ክርስቶስ አልዓዛር ይለዋል
መቃብሩን ሽሮ አዲስ ፍጥረት ሆኗል
ማነው ሙት የሚለው ከእንግዲህ በኋላ
ተጠርቷል በጌታ ወደ ፍፁም ተድላ